# ቾል ልትለው አይገባህም!

በቤተሰብ ውስጥ ያለ ጥቃትና እንግልት፤
በእስራኤል ለሚገኝ መሲሓዊ ማኅበረሰብ የተዘጋጀ የመረጃ ቅጽ።

መሓሴ – በቀውስ ውስጥ ያሉ ቤተሰቦችን ተንከባካቢ አላትራፊ ድርጅት።
//እዚህጋ የድርጅቱ ምልክት መደረግ አለበት።//

ጽሑፍ፣ አርትኦትና የምንጮች ስብስብ – ዳና ሐሦን

ሥነ መለኮታዊ ምክር – እንድሪያስ ዮሐንሶን፣ ሜኖ ካሊሸርና ያዴድ ሾሻኒ

የመጀመሪያ ኅትመት በ2015

ባለመብቱ በጽሑፍ ካልፈቀደ በቀር በእዚህ ቅጽ ማንኛውም ዐይነት ንግድ ነክ እና/ወይም ማስታወቂያም ነክ ግልጋሎት መጠቀም አይፈቀድም።

2015 © የመሓሴ አላትራፊ ድርጅት ሙሉ መብት የተጠበቀ ነው – በቀውስ ውስጥ ያሉ ቤተሰቦችን የሚንከባከብ አላትራፊ ድርጅት።

የቋንቋ አርትኦትና የገጽ አወቃቀር፦ “ኦት” የኅትመት አገልግሎት
ከአዲስ ኪዳን የተወሰዱት ጥቅሶች ሁሉ የተወሰዱት ከአዲሱ ትርጒም ነው።

© አዲሱን ትርጒም ባስመለከት ሙሉ ባለመብት የእስራኤል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ነው።
በእስራኤል የታተመ።

# ይዘት

መቅድም……………………………………………………………………………..5
ቤተሰባዊ መድብል……………………………………………………………..7
ቅዱሳን መጻሕፍት በቤተሰብ ውስጥ የሚሆን ጥቃትንና እንግልትን ይከለክላሉ………9
እንደ ቅዱሳን መጻሕፍት የሆነ ተፈላጊ የቤተሰብ ኹነት………………………………13
በጋብቻ ሕይወት እንደ ቅዱሳን መጻሕፍት የሆነ የተፈላጊ አኳኋን አጽንዖቶች……...17
ጥቃትና እንግልት በቤተሰብ ውስጥ…………………………………………………23
ጥቃት በትዳር ጓደኞች መካከል…………………………………………………..27
ለጥንድ ዳንስ፥ ሁለት የመሆኑ ጒዳይ እርግጥ ነውን?..............................................33
ሰው አይለየው………………………………………………………………………35
ጥቃት እና/ወይም እንግልት በልጆች ላይ…………………………………………39
መንፈሳዊ እንግልት በቤተሰብ ውስጥ……………………………………………..59
ተጨማሪ የጥቃት ዐይነቶች በቤተሰብ ውስጥ……………………………………..61
በጥቃት ለተጎዱ ወዲያውኑ የሚደረግ ከለላ…………………………………………67
በጉዳት አድራሹ ላይ የሚደረግ የውንጀላ ክንዋኔ…………………………………73
የጉባኤ ለተቃውሞ ምክንያትነት……………………………………………………79
የጉባኤ ተሳትፎ ኀይል…………………………………………………………………95
በቀውስ ውስጥ ላሉ ቤተሰቦች የሚሆን የገንዘብ ዕገዛ……………………………..107
ፍትሕ በቅዱሳን መጻሕፍት ውስጥ………………………………………………...109
በቤተሰብ ውስጥ ያለን ጥቃትና እንግልትን ባስመለከተ የጉባኤ ቃለ ስምምነት……….113
ዋቢ መጻሕፍት…………………………………………………………………..115

==========================================================================

“ቸል ልትለው አይገባህም።” የሚለው ትዕዛዝ “እንዲህም በወንድምህ በጠፋበት ነገር ሁሉ… ፤”(ዘዳ 22፥3) የሚለውን ጥቅስ ተከትሎት መጥቷል። ለነገሩ ትዕዛዙ የሚናገረው ስለ ቁሳዊ ጥፋት ነው፤ ይሁን እንጂ የመንፈስንም ሆነ የነፍስን ጥፋት ስለመግለጹም ጥርጥር የለውም።

በአካባቢያችንና በመካከላችን ማን ወደ ጥፋት እየሄደ እንደሆነ፣ ምስሉን፣ መንገዱን፣ አምላኩን… ያጣም ማን እንደሆነ ልብ ማለት አለብን። ቸል ልንል አንችልምና!

==========================================================================

# መቅድም

በቤተሰብ ውስጥ ያለን ጥቃት ስንዘራ ለማጥፋት የሚደረገው ሙከራ ቤተሰቡን ጭምር ሊያጠፋ እንደሚችል ሁሉ፣ ቤተሰቡን ለመጠበቅ የሚደረገውም ሙከራ ጥቃት ስንዘራውን ባለበት እንዳለ ሊተወው ይችላል፤ ይህ ደግሞ በቤተሰብ ውስጥ ያለን የጥቃት ስንዘራም ሆነ የእንግልት ሁኔታን የመቋቋም ጉዳይ የበለጠ ውስብስብ ያደርገዋል። ቤተሰብን ሳያጠፉ ከቤተሰብ ውስጥ የጥቃት ስንዘራ ሁኔታን ለማስወገድና ቤተሰብን ያለ አንዳች ጥቃት ለመጠበቅ ደግሞ የጥቃትን እጅግ አውዳሚነትና የቤተሰብን በጣም አስፈላጊነት መረዳቱ ይጠቅማል። ነገሩ የነቀርሳ እባጭን ከአስፈላጊ ብልት ላይ ከማስወገድ ጋር ይመሳሰላል፤ ብልቱን ሳያበላሹ እባጩን ለማስወገድ ብዙ ጥንቃቄ ያሻልና።

ቤተሰብ በዐይነተኛ አወቃቀሩ እርስበርስ በደም፣ በማደጎ ወይም በጋብቻ ትስስር ያላቸው የሰዎች ስብስብ ይዘት ነው። ቤተሰብ ከውስጥ ሲታይ፥ የተካተተውን ግለሰብ ሁሉ ያድግ፣ ይዳብር፣ ይቀረጽና ለወደፊት አዲስ ቤተሰብን ያቋቁም ዘንድ የሚያስችል መሠረት ነው። ቤተሰብ ከውጪ በኩል ሲታይ ደግሞ አጠቃላይ ማኅበረሰቡ የሚታነጽበት የመሠረት ድንጋይ ነው። ቤተሰባዊው መድብሎች ከሌሉ፣ ሕብረተሰብ ሕልውና አይኖረውም፤ ቤተሰባዊው መድብሎች ከተንኮታኮቱ ወይም እንደሚገባው ካልሠሩም የቤተሰቡ ደኅንነት ጉዳይ ጥያቄ ይፈጠርበታል።

የቤተሰብ እንደሚገባ ያለመሥራት ሁኔታ ከመጀመሪያው ዘመን አንሥቶ በዓለማችን የነበረ ነገር ነው፤ በዋናነት የመነጨውም ከሃይማኖታዊ ወግ ጠባቂነት አስተሳሰብ ሲሆን በማዕቀፉም ውስጥ አብዛኞቹ ወንዶች የተሰጣቸውን ኀላፊነት በመጥፎ መልኩ ተጠቅመውበታል። ሴቶችንና ልጆችን እንደ ግል ንብረትና ከእነርሱ በታች የሆኑ ሰዎች አድርገው በመቁጠር ክብራቸውን ረግጠው፣ ለፍላጎታቸውም ማሚያ አድርገው፣ በብርቱ ክንድ ገዝተዋቸዋል።

በመጨረሻዎቹ መቶዎችም ሴቶች (በተለይ በምዕራቡ ዓለም) ታግለው ዕውቅናን አገኙ። ዛሬ ከወንዶች እኩል የስብእና ዋጋ ያላቸው ባለ ነጻ ፈቃድና በማኅበረሰባዊ፣ በዜጋዊና በፖለቲካዊ ስፍራም እኩል ባለ መብት ሆነዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘም ይህ ጠቃሚ የሴቶች ትግል በጊዜ ሂደት፥ ተፅዕኖ ወዳላቸው በርካታ እንስተኝነት እንቅስቃሴዎች ዳብሮ - ለምሳሌ የሴት - ግላዊ ሕልውናን ለሚባለው ፅንሰ ሐሳብ የማሰናከያ ድንጋይ የሆነውን ቤተሰብን እንደ ቅንጁ የኀይል ተዛምዶ መዋቅር አድርጎ አስተዋወቀ።

እንዲህ ባለና በሰዎች የምርጫ ቅደም ተከተል ላይ ከባድ ማመናታትን በፈጠረ ሁኔታ ማንነቶችና የሥራ ድርሻዎችም እንዳዲስ ተወሰኑ። የማታ ማታም እንደ ጎንዮሽ ውጤት ሆኖ ከወንዶች ጭቆና ነፃ የመውጣቱ ንቅናቄ፥ የግለሰብ ከግዴታዎች፣ ከቤተሰብና ከትዳር "እስራት" ነፃ መውጣት ለሚባለው ሐሳብ ምክንያታዊነትን አጎናጸፈ።

ለነገሩ አሳፋሪው የወንዶች ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን የመመዝበር ጉዳይም ሆነ በዚህ ሳቢያ የተደረገው የሴቶች ትግል ሕዝባዊውን ውይይት ወደ ሕግ ድንጋጌ፣ ወደ ፍርድ፣ ወደ መገናኛና ብዙኀን፣ ወደ ግንዛቤ አምጥተውት ሴቶችን በወንዶች ላይ ወንዶችንም በሴቶች ላይ በማስነሣት ለጸብ መንደርተኝነት አብቅተውታል። ቤተሰብ ለግለሰብ፣ ለሰብአዊው ማኅበረሰብና ከሁሉም በላይ ደግሞ ለአምላክ እጅግ ጠቃሚ ነገር ሆኖ ሳለ፣ ውይይቱ ቤተሰብን ወደ ጎን ለሚገፉ የጾታዎች ጦርነት ዳርጓቸዋል።

እንደ ቅዱሳን መጻሕፍት መሠረት ወንድና ሴት የተፈጠሩት በአምላክ አምሳል ነው። እርሱም አንዱ በአንዱ ተጣብቆ አንድ ሥጋ ይሆኑ ዘንድና ልጆችን እየወለዱ በምድር ላይ ሕይወታቸውን በጋራ ኀላፊነት እንዲመሩ ነው። ወንድና ሴት አንድ ሥጋ ሲሆኑ ራሱን እንደ ቤተሰብ ማለትም የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ቤተሰብ አድርጎ ለሰው ልጆች ሊያስተዋውቅ የመረጠበትን የአምላክን ሕልውናና አንድነት ያንፀባርቃሉ። ቤተሰብ ለአምላክ የፍጥረቱ አክሊል ስለሆነ አይደለም።

ስለሆነም የሁነኛ ማኅበረሰብ ምሥረታ የሚወሰነው በብርቱ ወንዶች፣ በብርቱ ሴቶች ወይም በብርቱ ልጆች ሳይሆን እንደሚገባ በሚሠሩና በጸኑ ብሎም የሁነኛ ማኅበረሰብን ደኅንነትና ሕልውና በሚያስገኙ ጤናማ ቤተሰቦች ላይ ነው። ወንዶች፣ ሴቶች ወይም ልጆች በሚኖራቸው በርካታ መብቶች ሁሉ ሊደሰቱ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ መብቶች በራሳቸው ጸንተው በቀጠሉ ልክም ለጽኑ ጥፋት ምክንያት ይሆናሉ። መብቶች የወግንም ይሁን የእንስተኝነትን ባሕሪይ የያዙም ቢሆኑ ከቤተሰባዊው መድብል ይዘት የተገነጠሉ ይሆኑና ትርፋቸው ወደ ኪሳራ ይለወጣል፤ በዘመናችን እየታየ ባለው የቤተሰባዊ መድብል ሕልውና እጦት አለያም የነበረውን ቤተሰባዊ መድብል የማፍረስ ኪሳራ።

የቤተሰባዊው መድብል ሕልውና እጦት የሚገለጸውም ቤተሰብ ከመመሥረት ይልቅ ግላዊ ሕልውናን፣ ተጠያቂነት የለሽ ግንኙነትንና የማይፈለግ እርግዝናን በማበረታታት ነው። ቤተሰባዊውን መድብል ማፍረስ የሚገለጽበት መንገድ ደግሞ ፍቺ ሲሆን ለትዳር ጓደኛ ባለመታመን፣ ቤተሰብን ከመገንባት ይልቅ የሥራ ዘመንን ማስቀደምና በቤተሰብ ውስጥ የጥቃትና የእንግልት መኖር ሁኔታንም ይጨምራል።

አብዛኛውን ጊዜ በተለይም ጥቃትና እንግልት ባለበት ሁኔታ፥ አንድ ቤተሰባዊው መድብል ውስጥ ውስጡን እየፈራረሰ በውጪ ፍጹም መስሎ ሊታይ ስለሚችል ዘወትር ማሰብ ያለብን ነገር ለቤተሰባዊ መድብል ጥንካሬው ሰላሙ እንጂ ሙሉነቱ የግድ ምልክቱ አለመሆኑን ነው።

# ቤተሰባዊው መድብል

ቤተሰብ የአምላክ የፍጥረቱ ፍሬ ነው። አምላክ አዳምን የፈጠረው ይዳብር ዘንድ እንዳለው ሰብአዊ መድብል በቤተሰብ ውስጥ መኖር እንዲችል ነው። የቤተሰብን የሕይወት ዑደት ጅማሬ በጋብቻ መበየን ይቻላል፤ ተከታዩ ደረጃም በወሊድና በልጆች ዕድገት የሚታነጽ ቤተሰባዊ አንኳር ነው። ከልጆችም ጋብቻ በኋላ ቤተሰቡ እየሰፋ ይሄዳል፤ ከዚያም የእርጅና ወቅት ይመጣና የቤተሰቡ መጠን እየቀነሰ ይሄዳል።

ቤተሰብ ቢያንስ ሁለት ጾታዎችንና ሁለት ትውልዶችን ያካተተ ኅብርና ተዋረዳዊ ግንኙነት ያለበት የኑሮ ሥርዐት ነው። ቤተሰብ ለትውልድ መቀጠልና ለሰው መሠረታዊ ፍላጎቶች አቅርቦት፣ ለዕድገቱ፣ በእርሱና በማኅበረሰቡ መካከልም ለሚሆነው ነገር ድልድይ የመሆን ኀላፊነት አለበት። ቤተሰብ ለሰው የመጀመሪያ ማንነቱን አስጨባጭ፣ ከቁሳዊውና ስሜታዊ ነገር አኳያም መተማመን አስራጭና የስሜትና የገንዘብ ድጋፍ አድራጊም ነው።

ቤተሰብ በመያያዝ፣ በጓደኝነት ሂደቶች፣ በሰዎች ግንኙነት፣ በተሳትፎ፣ በአጸፋዊ ድግግፍ፣ በተለያዩ የግንኙነት ዐይነቶች (በቃልና በቃል አልባ) ድርሻውንና ኀላፊነቱን በስኬታማነት ሊያሟላ ይችላል።

ቤተሰባዊ እንቅስቃሴ ሁሌም ቢሆን ድርብርብ ነው። ምክንያቱም አንዱ የቤተሰብ አባል ከሌላኛው ጋር በሚኖረው ግንኙነት ለውስጣዊ ውጥረት የተዳረገ ሲሆን፣ ቤተሰቡ የኑሮ መንስኤዎች ሳቢያ ደግሞ ለውጫዊ ውጥረት የተዳረገ ነው። ሌላውን ቤተሰብ የሚመስል ቤተሰብም ሆነ ፍጹም የሆነን ቤተሰባዊ መድብል መመሥረቻ ቀመር የለም።

አብዛኛዎቹ የቅዱሳን መጻሕፍት ክፍሎች በቤተሰብ ውስጥ፣ በወንድማማቾች መካከል፣ አባቶችና እናቶች ከልጆቻቸው ጋር ስላላቸው ግንኙነት፣ በወንድና በሴትም መካከል ስላለው ግንኙነት ማተታቸው እንዲያው አይደለም። ቅዱሳን መጻሕፍት በተለያዩ ቀውሶች ውስጥ የነበሩትን የተለያዩ ቤተሰቦች ለበርካታ አዎንታዊና አሉታዊ ምሳሌነት ይጠቀሙባቸዋል። በዚህም አግባብ በቤተሰብ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች ስለ እርስበርሳቸውም ይሁን ስለ ድርጊቶቻቸው ለክፉም ሆነ ለደግ ያላቸውን የተፅዕኖ ኀይል ቅዱሳን መጻሕፍት ያስተምራሉ።

ቅዱሳን መጻሕፍት ራሳቸውም የሚያስተምሩን የአምላክ ጸጋ ከሰብአዊ ስህተቶቻችን በላይ በመሆኑ በኑሯችን ቤተሰባዊውን ግንኙነታችን እንድናጠናክር እየረዳን ካልሆነ በቀር ፍጹም የሆነ ቤተሰብ አለመኖሩን ነው።

ይህም እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሆነ ሁሉ የተፈጠረለትን ሙሉ ዐላማ እውን ያደርግ ዘንድ ለማስቻል ነው፤ ይህም አምላክን በፍጹም ልቡ፣ በፍጹም ነፍሱና በፍጹም ኀይሉ ይወደው ዘንድ ነው። ፍቅርም ራሱ በቅዱሳን መጻሕፍት ውስጥ በሙሽራና በሙሽራዪቱ፣ በወላጅና በልጆቹ፣ በበኲርና በወንድሞቹ ባለ ፍቅር ተመስሏል።

==========================================================

**ፍጹም የሆነ ቤተሰብ የለም።**

- በማንኛውም ቤተሰብ ውስጥ ከጊዜ ጊዜ ቀውሶች፣ ጩኸቶች፣ ድብድብ፣ ጸቦች፣ አለመግባባቶች፣ ውጥረቶች፣ ቅያሜዎችና ቁጣዎች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ በጤናማ ቤተሰብ ዘንድ ይህ ዐይነቱ ሁኔታ አይዘወተርም።
- በማንኛውም ቤተሰብ ውስጥ ስህተት ይሠራል፤ ሆኖም ጤናማ ቤተሰብ የሠራውን ስህተት አምኖ በመቀበል ስህተቱን ተጋፍጦ ለማረም ይችላል።
- ጤናማ ቤተሰብ በውስጡ ያቀፋቸውን ግለሰቦች ሁሉ በራሳቸው ልዩ የመሆናቸውን ስሜት እንዲሰማቸው ያስችላቸዋል። እንዲህ ባለው ቤተሰብ ዘንድ ደግሞ ስሜትን መግለጽ ይፈቀዳል፤ ተቀባይነትም አለው፤ የቤቱ ሰዎች በነፃነት ትኩረትን መጠየቅም ሆነ መስጠትን ይችላሉና።
- በጤናማ ቤተሰብ ውስጥ ወሰኖች አሉ፤ ደንቦቹም ግልጽና ቋሚዎች ሆነው የመለዋወጣቸው መጠን እንደ መንሥኤው ተለዋዋጭነትና ለግለሰቡ ፍላጎቶች እንዲስማማ የተደረገ ነው።
- በጤናማ ቤተሰብ ውስጥ ወላጆች በልጆቻቸው ላይ ዕድሜአቸውን የማይመጥን ኀላፊነት ሳይጥሉባቸው፣ ለልጆቻቸው የሚያስቡና ልጆቻቸውን የሚንከባከቡ መሆናቸውን ማመን ይቻላል።
- በጤናማ ቤተሰብ ውስጥ ልጆች ወላጆቻቸውን፥ ወላጆችም ልጆቻቸውን ያከብራሉ። እርስበርሳቸው አይፈራሩም።
- በጤናማ ቤተሰብ ውስጥ ፍጹምነት የለም፤ ሰላም እንጂ።

==========================================================

# ቅዱሳን መጻሕፍት
# በቤተሰብ ውስጥ የሚሆንን ጥቃትና እንግልት ይከለክላሉ።

ቅዱሳን መጻሕፍት ስለ ቤተሰቦች በተነገሩ ታሪኮችና ምሳሌዎች ብቻ የተሞሉ ሳይሆኑ፥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሁነኛ ስለሆነው ቤተሰባዊ ግንኙነት የተሰጡትን ትዕዛዛትና ብያኔዎችንም የሚገልጹ ናቸው።

በጥቅሉ በሰው ልጆች ላይም ሆነ፣ በተለይ በሴቶችና በልጆች ላይ የሚሰነዘረው ጥቃት በቅዱሳን መጻሕፍት መሠረት ተገቢነት የሌለው መንገድ መሆኑንም ጭምር መማር ይቻላል። ይህን ደግሞ እንስሶችን፣ ወንዶች ባሪያዎችን፣ ሴቶች ባሪያዎችን፣ ደንገጡሮችንና ባልንጀሮችን ስለ መምታት ተደንግገው ከሚገኙት ክልከላዎችና ቅጣቶች መረዳት ይቻላል።

==================================================================

## በእንስሶች ላይ ስለሚሰነዘረው ጥቃት የተከለከለ ክልከላ።

ቅዱሳን መጻሕፍት እንስሳትን መግደል "እንስሳን እስኪሞት ድረስ የሚመታ ሕይወት በሕይወት ፋንታ ካሣውን ይክፈል።" ዘሌ24፥18 ወይም ደግሞ ለሞት የሚያደርስን ምት መምታት፦ "እንስሳውንም የሚገድል ካሣ ይተካ፤ ሰውንም የሚገድል ይገደል።" ዘሌ 24፥21 ሲሉ ይከለክላሉ። እንግዲህ እንስሳን እስኪሞት ድረስ መምታት ከተከለከለ፣ የሴትና የልጆችን ሕይወት ዐደጋ ላይ የሚጥል ምት መምታትማ እንዴት አብዝቶ ይከለከል።

## በወንዶች ባሪያዎችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ ስለሚሰነዘረው ጥቃት የተከለከለ ክልከላ።

ቅዱሳን መጻሕፍት በወንዶች ባሪያዎችና በደንገጡሮች ላይ የሚደረገውን እንግልት ይከለክላሉ። ባሪያውን እስኪሞት ድረስ በኀይለኛ ጭካኔ የመታ ጌታ እንዲህ ያለው ቅጣት ይጠብቀው ነበር፦ "ሰውም ወንድ ባሪያውን ወይም ሴት ባሪያውን በበትር ቢመታ፥ ቢሞትበትም፥ ፈጽሞ ይቀጣ።" ዘፀ21፥20

ጌታው ወንድ ባሪያውን ታምሞ ለመተኛት የሚያደርስ ምት ቢመታው፣ ጌታው ሊክሠው አያስፈልገውም ነበር፤ ምክንያቱም ወንድ ባሪያው ንብረቱ ሆኖ ቀርቷልና እንዲህም ያተርፍ የነበረውን ትርፍ በባሪያው መቁሰል ሳቢያ ያጣዋልና "የተመታው ግን አንድ ወይም ሁለት ቀን ቢቈይ ገንዘቡ ነውና አይቀጣ።" ዘፀ21፥21

ጌታው ወንድ ባሪያውን ጉዳት ቢያደርስበት ጌታው አርነት ሊያወጣው ግዴታ ነበረበት፦

"ሰውም የባሪያውን ወይም የባሪያይቱን ዓይን ቢመታ ቢያጠፋውም፥ ስለ ዓይኑ አርነት ያውጣው። የባሪያውን ወይም የባሪያይቱን ጥርስ ቢሰብር፥ ስለ ጥርሱ አርነት ያውጣው" ዘፀ21፥26-27

በቅዱሳን መጻሕፍት መሠረት ሴትና ልጆች፣ ከወንዶች ባሪያዎችና ከሴቶች ባሪያዎች የበለጠ ጠቃሚዎችና ውዶች ናቸው። ተዋጊ በሬን ባስመለከተ በተበየነው ፍርድ (ዘፀ21፥28-36) ባሪያው ወይም ባሪያይቱ በእርሱ ጉዳት በደረሰባቸው ጊዜ በሬው ይወገራል፤ (30 ሸቄል) የገንዘብ ካሣም ይቀበላሉ። በአንጻሩም ሴት ወይም ልጆች በበሬው ጉዳት በደረሰባቸው ጊዜ በሬው ይወገራል፤ ባለቤቱም ይገደላል (አለያም ስለነፍሱ ዋጆ ይሰጣል)።
ስለሆነም ወንዶች ባሪያዎችና ሴቶች ባሪያዎችን መምታት፣ አካላቸውን ማጉደልና መጉዳት ክልክል ከሆኑ፣ የሴትንና የልጆችን አካል ማጉደልም ሆነ በእነርሱ ላይ ጉዳት ማድረስማ በፍጹም የተከለከለ ነው።

## ጾታዊ ጥቃት የሥቃይ እና/ወይም የግድያ ያህል ነው።

ቅዱሳን መጻሕፍት ጾታዊ ጥቃትን (ደፈራን) የሚቆጥሩት እንደ ምንዝር ወይም እንደ ግብረገብ መጓደል አድርገው ብቻ ሳይሆን እንደ ሥቃይና ግድያም ጭምር ነው። ያልታጨችን ድንግል መድፈር የተገለጸው "እንደ ሥቃይ" ነው፦ "አስነውሮአታልና" ዘዳ22፥29። በመሆኑም የመድፈርን ድርጊት የፈጸመውን ሰው የደፈራትን ድንግል ሊክሣትና የዕድሜዋን ዘመን ሁሉ ሊያስተዳድራት ያስፈልገዋል። የታጨችን ልጃገረድ መድፈር ደግሞ "ሰው በባልንጀራው ላይ ተነሥቶ እንደሚገድለው ይህ ነገር ደግሞ እንደዚሁ ነውና፤"ዘዳ22፥27 ይህን ለፈጸመው እንደሚሆነው ቅጣት እንዲሁ የደፈራውም ቅጣቱ ሞት ነው።

## በሰውና በባልንጀራው መካከል ስለሚሰነዘረው ጥቃት የተከለከለ ክልከላ።

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አረዳድ ባልንጀራ - የሚያውቁት ሰው እና/ወይም የማኅበረሰብ አባል ነው። ቅዱሳን መጻሕፍት ባልንጀራውን መትቶ ላቆሰለ ሰው የሚሰጠውን ፍርድ ያብራራሉ፦ በድንጋይ (ወይም በማንኛውም ነገር) ወይም በቡጢ ለተመታና ለዐልጋ ቁራኛነት ለተዳረገ ሰው፤ ጉዳት አድራሹ ሰው ካሣ እንዲከፍል በኦሪት ተወስኖበታል።

"ሁለት ሰዎችም ቢጣሉ፥ አንዱም ሌላውን በድንጋይ ወይም በጡጫ ቢመታ፥ ያም ባይሞት ነገር ግን ታምሞ በአልጋው ላይ ቢተኛ፥ ተነሥቶም በምርኩዝ ወደ ሜዳ ቢወጣ፥ የመታው ንጹሕ ነው፤ ነገር ግን ተግባሩን ስላስፈታው ገንዘብ ይከፍለው ዘንድ፥ ያስፈውሰውም ዘንድ ግዴታ አለበት።" ዘፀ21፥18-19

ጎጂው በባልንጀራው ላይ ባደረሰው የአካል ጉዳት ሁሉ እርሱም ሊጎዳበት የግድ ነው።

ሰውም ባልንጀራውን ቢጐዳ፥ እርሱ እንዳደረገ እንዲሁ ይደረግበት። ስብራት በስብራት ፋንታ፥ ዓይን በዓይን ፋንታ፥ ጥርስ በጥርስ ፋንታ፥ ሰውን እንደ ጐዳ እንዲሁ ይደረግበት ዘሌ2419-20

ቅዱሳን መጻሕፍት ባልንጀራውን መትቶ ያላቆሰለን ሰው ፍርድ ባያብራሩም፤ ዳኛው ከፈረደበት የግርፋት ቁጥር በላይ መግረፍን ግን ይከለክላሉ። (የጽኑ ግርፋት ቁጥር 40 ነው።) በዘዳ25፥3 ላይ እንደተጻፈው ባልንጀራውን እንዳያቃልለው ወይም እንዳያዋርደው ሲባል በግርፋቱ ቁጥር ላይ አንድ ምት እንኳን እንዳይጨመር አሪት ይከለክላል።

"ግርፋቱም አርባ ይሁን፤ ከዚህ በላይ ጨምሮ ብዙ ግርፋት ቢገርፈው ወንድምህ በፊትህ ነውረኛ ይሆናልና ከዚህ በላይ አይጨመርበት"

የተፈቀደለትን መቺ በዳኛው ከተወሰነው ቅጣት በላይ (ከ40 ያልበለጠ) እንዳይጨመር አምላክ ከከለከለ፤ ያልተፈቀደለትን፣ ኀጢአት ያልሠራውንማ እንዴት አብልጦ አይከለክል።

በተጨማሪም ቅዱሳን መጻሕፍት በሚያቆስልም ሆነ በማያቆስል በማንኛውም ምት፣ ባልንጀራን በስውር መማታት ይከለክላሉ። "ባልንጀራውን በስውር የሚመታ ርጉም ይሁን" ዘዳ27፥24። ይህም የሆነበት ምክንያት በስውር የሚማታውን ስለ ድርጊቱ በኀላፊነት መጠየቅ ባለመቻሉ፤ በስውር የተመታውም ሰው ፈጣን ከለላ ሊያገኝ ባለመቻሉ ይመስላል።

ሰው ለሚስቱና ለልጆቹ ያለው ኀላፊነት ከፍተኛ ነው፤ ስለሆነም ባልንጀራን ስለ መምታት የተነገሩት ክልከላዎች ቤተሰብን በተመለከተም ይሠራሉ። ይህ ጥቃት የሚሰነዘረው አብዛኛውን ጊዜ ከእይታ ሁሉ በተሰውረ ሁኔታ በድብቅ መሆኑ መጥቀስ አስፈላጊ ነው።

**በቤተሰብ ውስጥ ኀፍረተ ሥጋን ስለ መግለጥ የተከለከለ ክልከላ።**

ቅዱሳን መጻሕፍት በዘመዳሞች መካከል ኀፍረተ ሥጋን መግለጥ ወይም ግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምን በግልጥ ይከለክላሉ፦ ሰው ከእናቱ ጋር፣ ከአባቱ ሚስት ጋር፣ ከእኅቱ ጋር፣ ከልጅ ልጆቹ ጋር፣ ከአክስቶቹ ጋር፣ ከአጎቱ ሚስት ጋር፣ ከልጁ ሚስት ጋር፣ ከወንድሙ ሚስት ጋር፣ ከምራቱ እናት ጋር፣ ከሚስቱ ልጅ ጋር፣ ከሚስቱ እኅት ጋር፣ ከሚስቱ እናት ጋር (ዘሌ18፥6-18 ያለውን ይመልከቱ) ።

ክልከላው ሴቶችን አይጠቅስም ነገር ግን ከላይ ከተዘረዘሩት ነገሮች ተገላቢጦሽ ሴትም የሚከተሉትን ዘመዶች ኀፍረተ ሥጋ መግለጥ መከልከሏን መረዳት ይቻላል። ሴት ከአባቷ ጋር፣ ከእንጀራ አባቷ ጋር፣ ከልጇ ጋር፣ ከእንጀራ ልጇ ጋር፣ ከወንድሟ ልጅ ጋር፣ ከአያቷ ጋር፣ ከባሏ ወንድም ልጅ ጋር፣ ከባሏ አባት ጋር፣ ከባሏ ወንድሞች ጋር፣ ከሴት ልጇ ባል ጋር፣ ከእኅቷ ባል ጋር።

በእርግጥ በሰውና በወንድሙ ሴት ልጅ ወይም በእኅቱ ሴት ልጅ መካከል ኀፍረተ ሥጋን ስለ መግለጥ ቁርጥ ያለ ክልከላ ባይኖርም (በሴትና በዘመዶቿ መካከል) ወይም በዘመዶቿ ልጆች መካከል ከተነገረው ተጋላቢጦሽ በዘሌ 18፥6 "ከእናንተም ማንም ሰው ኃፍረተ ሥጋውን ይገልጥ ዘንድ ወደ ዘመዱ ሁሉ አይቅረብ፤" ተብሎ ተጽፏል። ስለ ሴት ልጅም በግልጽ የተከለከል ክልከላ ባይወሳም ሴቲቱንና ሴት ልጇን ማግባት ግን ክልክል መሆኑን ደግሞ ከዚህ መማር ይቻላል።

በወንድ ዘመዳሞች መካከል ኀፍረተ ሥጋን ስለመግለጥ የተጠቀሰ ክልከላ ባይኖርም፣ ከወንድ ጋር ስለ መተኛት ራሱን የቻለ ክልክል እስካለ ድረስ፤ በወንድ ዘመዳሞች መካከል ያለውንም ኀፍረተ ሥጋን መግለጥን ማካተቱ አይቀሬ ነው።

ከወንድ ለወንድ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ክልከላም፣ የሴት ለሴት ግብረ ሥጋ ግንኙነትን ክልከላን መጠቆም ይቻላል። በመሆኑም ሴት ልጅ ከሴት ዘመዶቿ ጋር ኀፍረተ ሥጋን መግለጥ ተከልክሏል ማለት ይቻላል።

**በቃል የሚሰነዘር ጥቃት የግድያ ያህል ነው**

እየሱስ አካላዊውንና በቃል የሚሰነዘረውን ጥቃት አነጻጽሯል ይህም ቃላት ከምቶች ያላነሰ ጉዳት ያስከትላሉ ከሚለው መረዳት በመነጨ ነው። እየሱስ የገዳዩንና በወንድሙ ላይ ያለ ምክንያት የተቆጣውን ሰው ቅጣትም አነጻጽሯል፦ "በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤" ከዚህም ይብስ "ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤" ባጭሩ በቃላት አማካይነት ራሱን ዋጋ ቢስነት እንዲሰማው አድርጎታልና። እየሱስ በከንቱ ወንድሙን የሚወነጅል ሰው ቅጣቱ እጅግ ጽኑ መሆኑን ያስተምራል። "ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል።" (ማቴ5፥21-26) ያለውን ይመልከቱ

===============================================================

# እንደ ቅዱሳን መጻሕፍት የሆነ ተፈላጊ የቤተሰብ ኹኔታ

ቅዱሳን መጻሕፍት ስለ ጥቃት ክልከላ ብቻ ሳይሆን በባልንጀሮችና በእምነት ወንድሞች መካከል ስላለ ተፈላጊ ኹኔታም ጭምር የሚገልጹ መጻሕፍት ናቸው። ይህም ኹኔታ በትዳር አጋሮችና በቤተሰብ መካከል ላለው ግንኙነት መሠረት ጣይ ነው፤ እንግዲህ ከምናውቃቸው፣ ከጎረቤቶቻችን፣ ጓደኞቻችን፣ ከሕዝባችንና በእምነት ወንድሞች ከሆኑት ጋር ግንኙነታችን በተወሰነ መልኩ እንዲሆን ከታዘዝን፥ ሥጋችን ለሆኑትም ይልቁኑ እንዲሁ መሆን አለበት።

==========================================================================

**ቤተሰቦቻችን እንደ ራሳችን መውደድ አለብን፤ ለእኛ እንዲሆኑልን እንደምንፈልገውም እኛም ለእነርሱ እንሁንላቸው።**

- ነገር ግን ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ (ዘሌ19፥18)
- እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ ምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና።(ማቴ7፥12)
- እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።(ዮሐ13፥34)
- ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤(ዕብ10፥24)
- ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ።(1ጴጥ1፥22)
- እርስ በርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ።(1ጴጥ4፥8)

**ቤተሰቦቻችንን ማክበር አለብን።**

- በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፤ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ፤(ሮሜ12፥10)
- ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ።(ኤፌ5፥21)
- ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፥(1ጴጥ5፥5)

**ቤተሰቦቻችንን ማገልገል፣ መርዳትና መደገፍ አለብን።**

- ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ።(ገላ5፥13)
- እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ አንዱም አንዱም ሌላውን ያንጸው።(1ተሰ5፥11)
- በእያንዳንዱ ቀን እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ፤(ዕብ3፥13)
- ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤(ያዕ5፥16)
- እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤(1ጴጥ4፥10)

**ከፍርድ፣ ራስን ከፍ ከፍ ከማድረግ፣ ፀብን ወይም ንትርክን ከሚቀሰቅስ ነገር ሁሉና ቤተሰብን ከሚያሰናክል ነገር መራቅ አለብን።**

- እርስ በርሳችን እየተነሣሣንና እየተቀናናን በከንቱ አንመካ።(ገላ5፥26)
- እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ እርስ በርሳችን አንፈራረድ፤ ይልቁን ግን ለወንድም እንቅፋትን ወይም ማሰናከያን ማንም እንዳያኖርበት ይህን ቍረጡ።(ሮሜ14፥13)

**በቀውስና በችግር ሁኔታዎች ውስጥ ቢሆን በቤተሰባችን ላይ ስለሚሆን ቁጣ፥ ራሳችንን መግዛት ይኖርብናል።**

- መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚበራ አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅ ታደባለች፤ ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው፥ አንተ ግን በእርስዋ ንገሥባት። (ዘፍ4፥7)
- ተቈጡ፥ ነገር ግን ኃጢአትን አታድርጉ፤(መዝ4፥4)
- ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ፤በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት።(ኤፌ4፥25-32)
- አሁን ግን እናንተ ደግሞ ቍጣንና ንዴትን ክፋትንም፥ ... እነዚህን ሁሉ አስወግዱ፤ (ቈላስ3፥8-16)

- እርስ በርሳችሁ አትተማሙ። (ያዕ4፥11)
- እርስ በርሳችሁ አታጉረምርሙ፤(ያዕ5፥9)

**ቤተሰቦቻችን ቢጎዱንም እንኳን መበቀል ሆነ፥ በእነርሱ ላይ ቂም መያዝ እንደሌለብን አጥብቀን መረዳት አለብን።**

- በሕዝብህ መካከል በሸንጋይነት አትዙር፤ በባልንጀራህም ደም ላይ አትቁም፤ (ዘሌ19፥16)
- ራሳችሁ አትበቀሉ፥ ለቍጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፤ ... (ሮሜ12፥17-21)
- ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤(ሮሜ12፥17-21)
- መራርነትና ንዴት ቁጣም ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ።(ኤፌ4፥25-32)
- ክፉን በክፉ ፈንታ ወይም ስድብን በስድብ ፈንታ አትመልሱ (1ጴጥ3፥9)

**ቤተሰቦቻችን በፍቅርና በጥበብ መገሠጽ/ማረም/ አለብን።**

- ወንድምህን በልብህ አትጥላው፤ በባልንጀራህ ምክንያት ኃጢአት እንዳይሆንብህ ገሥጸው። (ዘሌ19፥17)
- በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ፤(ቈላስ3፥8-16)

**ቤተሰቦቻችንን ይቅር ማለት አለብን።**

- እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፥ (ኤፌ4፥25-32)
- ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ፤ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ፤(ቈላስ3፥8-16)

**ቤተሰቦቻችንን መታገሥ አለብን።**

- እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ። (ሮሜ15፥7)
- እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ፤(ኤፌ4፥2)
- እርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ (ቈላስ3፥8-16)

**ቤተሰቦቻችንን ዘንድ ሰላምን መከታተል አለብን።**

- እርስ በርሳችሁም ተስማሙ።(ማር9፥50)
- ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ።(ሮሜ12፥17-21)
- የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይግዛ፤ (ቈላስ3፥8-16)

==================================================================

ቅዱሳን መጻሕፍት ለጥቃት ክልከላና ለሁነኛ ሁነት እኛ ከሌሎች ጋር ማለትም ከበታቾቻችን ከእኩዮቻችንና ከባለ ሥልጣናት ጋር ለሚኖረን ግንኙነት የሚሰጡት ማብራሪያ በቤተሰብ ውስጥ ይሠራል።

ይልቁኑ በቤተሰባችን ውስጥ እንደ ቅዱሳን መጻሕፍት ሐሳብ ለመመላለስ መቸገራችን ጥርጥር የለውም፤ ይህ የሚሆነውም በቤተሰባችን ዘንድ ለማስመሰል ስለማንሞክር ወይም ለአኳኋናችን ስለማንጠነቀቅ ነው። በመሆኑም ነገሩ የበለጠ ይጎዳንና ክፉና በጎ ስሜቶቻችን ይገዝፋሉ።

ይህ ችግር ግን የእግዚአብሔርን መመሪያዎች ላለመተግበር ማቃለያነት አይሆንም። እንዲያውም በቤተሰብ ውስጥ በበለጠ በምንቸገርበት ነገር በፍቅር፣ በክብር፣ እርስበርስ በመታገሥና በመቻቻል፣ ቁጣችንን መመቆጣጠር፣ ያለ ፀብም በፍቅር በመተራረምና ሰላምን በመከተል እንደ ቃሉ ለመኖር አጋጣሚን ማግኘት አለብንና።

# በጋብቻ ሕይወት እንደ ቅዱሳን መጻሕፍት ሐሳብ ለሆነ ተፈላጊ ሁነት የተሰጡ አጽንዖቶች

አዳም ከተፈጠረ በኋላ እግዚአብሔር የፈጠራቸውን እንስሳት ተመልክቶ አብሮት ምድርን የሚገዛና የአምላክንም ትዕዛዛት ከእርሱ ጋር የሚፈጸም እንደርሱ ያለ ፍጡር አላገኘም ነበረ። (ዘፍ1፥28፤2፥19-20) አዳምም በእርሱ ዘንድ የሚገኙትን ፍጡራን ብቻ መግዛት እንደሚችል ተገነዘበ፤ ስለዚህም አምላክ ለሰው በተጣለበት የሥራ አደራ ዐጋዥ የምትሆነውን ተጓዳኝ ረዳቱን ሄዋንን ሰጠው። (ዘፍ2፥20) ተጓዳኙን ማለትም አቻውን፣ እኩያውን ትይዩውንና ከጎኑ የምትሆንለትን ማለት ነው። ዕቅዱም ሴቲቱ ከአዳም ጋር ኀላፊነት ተካፍላ፣ የተሰጠውን ሥራ በማከናወን ዓለምን አብራ እንትገዛ ነው። ጋብቻና ቤተሰባዊው መድብል የአምላክን አንድነት ብሎም በተወሰኑ ስብእናዎች መካከል ያለውን ሐሳባዊ መጣጣም፥ የበለጠ ጥሩ በሆነ ሁኔታ ለመግለጽ የተወሰኑ ናቸው። አምላክ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ነው፤ በግንኙነት ማዕቀፍ ውስጥ ስላለው የሥራ ክፍፍል በመካከላቸው ፍቅር፣ መከባበር፣ ከነጻ ፈቃድ የሆነ መስተጋብር ሰፍኖበታል። በአንድነት እንደ አንድ በመሆን በትዳርና በቤተሰብ ማዕቀፍ ውስጥ የአምላክን ባሕሪይ እንዲያንጸባርቁ፥ አምላክ ሰውን በመልኩ እንደ ምሳሌው፣ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጥአቸዋል።

በአዳምና ሔዋን መካከል ያለው ግንኙነት መስተጓጎል፥ የማታ ማታ በሰው ዘር ሁሉ ላይ ተፅዕኖ ወዳሳደሩት ጥፋታዊ ሐቆች - በኀጢአት ወደ መውደቅ፣ ወደ ቅጣት እና ከዔደን ገነት ወደመባረር አድርሷቸዋል። ሴት ከተረገመችው ርግማኖች አንዱ በዘፍ3፥16 "ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፥ እርሱም ገዥሽ ይሆናል።" የሚለው ነው። ለሴት ወንድ ያስፈልጋታል፤ እርሱም ይነግሥባታል። ያም ማለት ለእርሷ ራስ በመሆን፥ ኀላፊዋ ይሆናል ማለት ነው። ፀሐይና ጨረቃ በቀንና በሌሊት እንደሚሠለጥኑ፤ ቃየልም ኀጢአትን ንግሥባት እንደተባለው ዐይነት ማለት ነው።

ባጭሩ በዘፍጥረት በሆነው ቀውስ ሳቢያ ሴት ወንድ የሚያስፈልጋትና የእርሱ ጥገኛ ለመሆን በቅታለች። ይህ ርግማን ወንድ በሴት ላይ የፈቀደውን ያደርግባት ዘንድ አለማስቻሉ እርግጥ ነው፤ ጥቃት ይሠነዝርባት ወይም ያንገላታት ዘንድማ ፈጽሞ አይፈቅድም፤ ዳሩ ግን ቀውሱ የፍጥረትን ሥርዐት ለወጠው።

በአዳም፣ በሄዋንና በአምላክ መካከል ያለው ግንኙነት መስተጓጎልና፥ በወንዱና በሴቲቱ ላይ የመጡት ርግማኖች፥ በተለይም ወንድ የሴት ገዥ ይሁን የሚለው ርግማን በሰዎች ውስጥ ሌላውን የመግዛትን ፍላጎት አሠረፁባቸው።

የመቆጣጠሩ ሁኔታ የሚሆነው አንዳንዴ በማስገደድና በምዝበራ ነው፤ በተለይ ደግሞ በትዳር አጋርነት ማዕቀፍ ውስጥ። ሽኩቻዎቹ የጋብቻ ኪዳንን ማቃለያና ቤተሰባዊውን መድብል መናጃ ሰበብ የመሆናቸው ነገር የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነበረ። መጽሐፈ መክብብ ይህንን በደንብ ገልጾታል፦

“ይህን ሁሉ አየሁ፥ ከፀሐይም በታች ወደ ተደረገው ሥራ ሁሉ ልቤን ሰጠሁ፤
ሰው ሰውን ለመጉዳት ገዢ የሚሆንበት ጊዜ አለ።” (መክ 8፥9)

እየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት አምላክ እየደጋገመ በወንድና በሴት መካከል የጋብቻ ኪዳንን ማለትም “ሚስት ባልንጀራና የቃል ኪዳንህ ሚስት” (ሚልክ2፥14) መሆኗን ጠቃሚነት አጽንኦት ሰጥቶበታል።

እየሱስ በመጣም ጊዜ በወንድና በሴት መካከል የሚሆንን የጋብቻ ኪዳን ከጥንት ጀምሮ ወደተወሰነለት፥ ወደ ሁለቱ ዋና ተልእኮነት ቦታ መለሰው። አዳም ገና በኀጢአት ከመውደቁ በፊት፣ ሕግም ከመሰጠቱ በፊት፣ ሚስቶችን ማብዛት ከመጀመሩና ከፍቺዎችም በፊት ወደ ነበረውና በምድር ላይ የአምላክ መልክ፣ የአምሳሉና የባሕሪይው ነፀብራቅ ወደ ሆነው ወደዚያው ተልእኮ መለሰው።

ከዘፍጥረት ከሆነው ርግማን በታች ባለ ዓለም ውስጥ የምንኖር በመሆናችን፣ በጾታዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማንሠራራት ዋስትና ከመስጠት ረገድና በወንድሞች መካከል ሊሆን የሚገባው የሁነት መሠረቶችን ባስመለከተ፥ ቅዱሳን መጻሕፍት በትዳር ማዕቀፍ ውስጥ፥ በወንድና በሴት መካከል መኖር በሚያስፈልግ በተወሰነ ሁነት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። እርሱም በመጀመሪያ ከነበረው የሰብአዊ ጥንድነት ግንኙነት መስተጓጎል እንደተገለጠው ሁሉ በወንዱውም ጾታ ተበራክተው የሚገኙትን ድካሞች በሁለተኛውም ጾታ ዘንድ እንዳለ በማወቅ ነው።

==============================================================

## የወንድን(የባልን) ሁነት ባስመለከተ የተሰጠ ትኩረት።

**ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደ ወደዳት እንዲሁ፣ ባልም እንደ ገዛ ሥጋው አድርጎ ሚስቱን መውደድ አለበት።**

- “ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት፤” (ዘፍ2፥23)
- “ባሎች ሆይ፥ሚስቶቻችሁን ውደዱ መራራም አትሁኑባቸው” (ቈላስ3፥19)
- “ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ። እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤ ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፥ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል ይከባከበውማል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ። ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲሁ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፥ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ።” (ኤፌ5፥25-33)

==================================================================

እየሱስ ቤተ ክርስቲያንን የወደዳት እንዴት ነው? መብቱንና ሕጋዊነቱን ሁሉ በመተውና የአዳም ዘርን የኀጢአት ዳፋዎች በመሸከም በትሕትና፣ በትዕግሥትና በታዛዥነት ራሱን ስለ እነርሱ መስሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ነው።

ፍቅርስ ምንድን ነው? "ታጋሽና ቸርነትን አድራጊ"፣ "የማይመካና የማይታበይ"፣ "የማይገባውን የማያደርግ" (በጠማማ መንገድ)፣ "የራሱን የማይፈልግ" (ራስ ወዳድ ያይደለ/ የማይመቀኝ)፣ "በደልን የማይቆጥር" (የማይጮኽ የማያስጨንቅ የማያንገላታ ጥቃት የማይሰነዝር)ና "በዓመፃ ደስ የማይለው" ነው።(1ቆሮ13፥4-7)

==================================================================

**ባል ከሚስቱ ጋር መጣበቅና ለእርሷ ታማኝ መሆን አለበት።**

- ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል፤(ዘፍ224)
- ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ፥ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል።(ሚልክ2፥15-16) ሰው መንፈሱን መጠበቅ አለበት፤ መክዳትም የለበትም። መክዳት ማመንዘር በሚለው መረዳት ብቻ አይደለም ኪዳንን ማፍረስ በሚለውም እንጂ።

**ባል በሚስቱ መደሰት አለባት።**

- ከጕብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ።...በፍቅርዋም ሁልጊዜ ጥገብ። (ምሳ5፥18-20)

**ባል በሚስቱ ላይ ማንኛውም ዐይነት ምሬት ሊኖርበት አይገባም።**

- ባሎች ሆይ፥ ሚስቶቻችሁን ውደዱ መራራም አትሁኑባቸው። (ቈላስ3፥19)

**ባል ሚስቱንና ፍላጎቷን በመረዳት ተሰባሪነቷንና ወንዳወንድ ኀይሉን በእርሷ ላይ ሳይጠቀም፣ ሰው ለተሰባሪና ውድ ለሆነ ዕቃ በሚኖረው የበለጠ ስሜትና ጥንቃቄ መንከባከብ ይኖርበታል። (አካላዊ እና/ወይም መተዳደሪያ ነክ ኀይሉን ወዘተ)**

- እንዲሁም፥ እናንተ ባሎች ሆይ፥ ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው።(1ጴጥ3፥7)

**ባል ከመሪዎች እንደሚጠበቅ ሁሉ ትዕግሥተኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ ሉሰኛ ወይም ጥቃት ሰንዛሪ ያልሆነ መሆን አለበት።**

- ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው። እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ የማይነቀፍ፥ የአንዲት ሚስት ባል፥ ልከኛ፥ ራሱን የሚገዛ፥ እንደሚገባው የሚሰራ፥ እንግዳ ተቀባይ፥ ለማስተማር የሚበቃ፥ የማይሰክር፥ የማይጨቃጨቅ ነገር ግን ገር የሆነ፥ የማይከራከር፥ ገንዘብን የማይወድ፥ ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፥ የእግዚአብሔርን ቤት ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል? በትዕቢት ተነፍቶ በዲያቢሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ፥ አዲስ ክርስቲያን አይሁን። (1ጢሞ3፥1-6)

=============================================================

=============================================================

## የሚስትን ሁነት ባስመለከተ የተሰጠ ትኩረት።

**ሚስት ባሏን ማክበር እንጂ ማሳፈር የለባትም።**

- ሞገስ ያላት ሴት ክብርን ታገኛለች፥ (ምሳ11፥16)
- ልባም ሴት ለባልዋ ዘውድ ናት፤ አሳፋሪ ሴት ግን በአጥንቱ ውስጥ እንደ ቅንቅን ናት። (ምሳ12፥4)
- ሚስቱም ባልዋን ትፍራ። (ኤፌ5፥33)

**ሚስትም ወደ ሮሮና ወደ ክስ የሚመሩ ጠቦችን፣ ልዩነቶችንና ንትርኮችን ከመቀስቀስ መታቀብ አለባት።**

- ጠበኛም ሚስት እንደማያቋርጥ ነጠብጣብ ናት። (ምሳ19፥13-14)
- ከጠበኛ ሴት ጋር በአንድ ቤት ከመቀመጥ በውጪ በቤት ማዕዘን ላይ መቀመጥ ይሻላል። (ምሳ21፥9)
- ከጠበኛና ከቍጡ ሴት ጋር ከመቀመጥ በምድረ በዳ መቀመጥ ይሻላል። (ምሳ21፥19)
- በዝናብ ቀን የሚያንጠባጥብ ቤትና ጠበኛ ሴት አንድ ናቸው፤ (ምሳ27፥15)

**ሚስት ለባሏ መገዛት አለባት።**

- ሚስቶች ሆይ፥ በጌታ እንደሚገባ ለባሎቻችሁ ተገዙ። (ቈላስ3፥18)
- ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤…ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ። (ኤፌ5፥22-24)

- እንዲሁም፥ እናንተ ሚስቶች ሆይ፥... ተገዙላቸው። ... በውጭ የሆነ ሽልማት አይሁንላችሁ፥ነገር ግን ... የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ።(1ጴጥ3፥1-6)

==========================================================

## ስለ መገዛት ጥቂት ቃላት

በሚስት፣ በባል ወይም በቤተክርስቲያን ዘንድ "መገዛት" የሚለው ፅንሰ ሐሳብ ግንዛቤ ዕጦት በተለይም ሚስት ጥቃት በሰፈነበት የግንኙነት ማዕቀፍ ውስጥ ያለች እንደሆነ ከባድ ጫና ሊያመጣባት ይችላል። ጥቃት በሰፈነበት የግንኙነት ማዕቀፍ ውስጥ ያለች ሚስት ባሏ ጨካኝ ሆኖ በዐደጋ ላይም ብትሆን ሊገዛት የተገባ እንደሆነ አድርጋ ልትረዳ ትችላለችና። "መገዛት" የሚለው ቃል "የሆነን ሰው በቁጥጥር ስር ማዋል" የሚል ትርጉም ሲይዝ፣ የጥቃቱ ዑደት እያየለ ይመጣና ወንድ ሴትን የመግዛቱ ጉዳይ እንዲቀጥል ሁኔታን ያመቻቻል። ስለሆነም "መገዛት" የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ "በራብ ሚሊም" መዝገበ ቃላትና ከታች በብሉይ ኪዳን በተነገረው መሠረት መረዳቱ እጅግ ጠቃሚ ነው።

*መገዛት፦ ማለት የሌላውን ሥልጣን ወይም የበላይነት በትሕትናና በተዋረደ መንፈስ መቀበል፤ ፍልሚያን ወይም ተቃውሞን ማቆም ወይም በጠላት ድል መነሣትን መቀበል አብዛኛውን ጊዜ በይፋ የሚደረግ ነው።*

> ትዕቢተኛውንም ሁሉ ተመልክተህ አዋርደው። ትዕቢተኛውንም ሁሉ ተመልከት፥ ዝቅ ዝቅም አድርገው። (ኢዮብ40፥11-12)
>
> አክዓብ በፊቴ እንደ ተዋረደ አየህን? በፊቴ የተዋረደ ስለ ሆነ በልጁ ዘመን በቤቱ ላይ ክፉ ነገር አመጣለሁ እንጂ በእርሱ ዘመን ክፉ ነገር አላመጣም ... (1ነገሥ20፥29)
>
> የተናገርሁትን ሰምተህ በእግዚአብሔር ፊት ተዋርደሃልና፥ ልብስህን ቀድደሃልና፥ በፊቴም አልቅሰሃልና... (2ነገሥ22፥19)
>
> አባቱም ምናሴ ሰውነቱን እንዳዋረደ በእግዚአብሔር ፊት ሰውነቱን አላዋረደም፤ (2ዜና33፥23)
>
> በአምላኩም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ፤ በእግዚአብሔርም አፍ በተናገረው በነቢዩ በኤርሚያስ ፊት ራሱን አላወረደም። (2ዜና36፥12)
>
> ሰውነቱንም ባዋረደ ጊዜ የእግዚአብሔር ቍጣ ፈጽሞ እንዳያጠፋው ከእርሱ ዘንድ ተመለሰ፤ (2ዜና12፥12)
>
> በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ (2ዜና7፥14)

*በተጨነቀም ጊዜ አምላኩን እግዚአብሔርን ፈለገ፥ በአባቶቹም አምላክ ፊት ሰውነቱን እጅግ አዋረደ፥* (2ዜና33፥12)
*ራስህን አዋርደሃልና፥ ልብስህንም ቀድደህ በፊቴ አለቅሰሃልና* (2ዜና12፥6)

*የእስራኤልም መሳፍንትና ንጉሡ፦ እግዚአብሔር ጻድቅ ነው ብለው ሰውነታቸውን አዋረዱ።* (2ዜና13፥18)

*ነገር ግን ከአሴርና ከምናሴ ከዛብሎንም አያሌ ሰዎች ሰውነታቸውን አዋረዱ፥ ወደ ኢየሩሳሌምም መጡ።* (2ዜና30፥11)

*በመጻሕፍት በጥቂት ቦታዎች መገዛት የሚለው ቃል ስርወ ቃሉ በውትድርና እንደሚታወቀው ያለ ሽንፈትንና በጠላት ድል መነሣትን ለማመልከት ተጠቅሷል።*

*ጠላቶቻቸውም ግፍ አደረጉባቸው፥ ከእጃቸውም በታች ተዋረዱ።* (መዝ106፥42)

*ሰልፍ ሆነ፤ ገደለ።* (2ዜና20፥4)

***መደምደሚያ፦*** *ሁላችንም፥ አንዳችን ለሌላው እንድንገዛ ታዝዘናል፤ ማለትም በትሕትናና በመከባበር። ሚስት ከባሏ ጋር የሚኖራት ግንኙነት በትሕትና መንፈስ እንዲሆን የተለየ ትኩረት ተሰጥቶበታል፤ ምክንያቱም የዕቡይ ሚስት ትዕቢት የሰው ዘርን ሊጎዳና ሊለግጥ ይችላልና። ከላይ እንደተጠቀሰው የባል ግዴታ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳት እርሱም ሚስቱን እንዲወድና ራሱን ስለ እርሷ አሳልፎ እንዲሰጥ ነው። በመሆኑም በዚህ ለማለት የተፈለገው እንደ ውትድርና ደንብ ሚስት በባሏ ሥልጣንና የበላይነት ሥር መሆን አይደለም።*

***ሊስተዋል የሚገባው፦*** *በባል ላይ የተጣለው ግዴታ የሚገለጸው በራሱ አማካይነት ብቻ ነው። በአንጻሩም በሚስት ላይ የተጣለው ግዴታ የሚገለጸውም በራሷ አማካይነት ብቻ ነው። ሚስት ባሏ እንዲወድዳት ታደርግ ዘንድ አልታዘዘችም፤ በዚሁ መንገድ ሚስት ለባሏ እንትገዛ ታዝዛለች። ባልም ሚስቱ እንዲያስገዛ አልታዘዘም። ባል ከእርሱ እንደሚጠብቅበት፥ ፍቅር ከሌለው ሚስትም እንደሚጠብቅባት ትሕትና ካላሳየች፥ ይህ እንዲኖራቸው ማስገደድ የማይቻል ነው። ይህም ጉዳዩ ውስጣዊና የልብ ዝንባሌ በመሆኑ ነው። ለእነርሱ መጸለይ፣ ለልባቸው መናገር፣ እነርሱን ማስታረቅ፣ እንዲነጋገሩ ማድረግ ብሎም ሁለተኛው ወገን የሚጠበቅበትን ያሟላ ዘንድ ሊያበረታታ በሚችል መንገድ ሁሉ በግድ ሳይሆን በፈቃደኝነት ማስረዳት ይቻላል።*

# ጥቃትና እንግልት በቤተሰብ ውስጥ

በቤተሰብ ግንኙነት ማዕቀፍ ውስጥ አኳኋናችን እንዴት መሆን ወይም አለመሆን እንዳለበት ቅዱሳን መጻሕፍት ይመሩናል። እነዚህን ምሪቶች የመሳቱ ሁኔታ ደግሞ ወደ ትዳር ቀውስና ወደ ጥቃት ሊያሸቀለቁል ይችላል።

ከዚህ ሁኔታ የተጠበቀ አንድም ቤተሰብ የለም። በየትኛውም የኅብረተሰብ ደረጃ ቢሆን፣ በማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ እርከን ሁሉ፣ በምሁርነት ደረጃ ሁሉ፣ በየትኛውም ሃይማኖት ወይም እምነት ዘርፍ ያሉ ቤተሰቦች፥ ለቤተሰብ ጥቃትና እንግልት የተጋለጡ ናቸው።

========================================================================

ጥቃት ምንድን ነው? እንግልትስ ምንድን ነው?

- **ጥቃት፦** አንድ ሰው ሌላውን በጉልበት ያለ ፈቃዱ የሚያስገድድበ ድርጊት ሁሉ ነው።

- **እንግልት፦** የሚያሠቃዩ ወይም ለሥቃይ የሚዳርጉ፥ በጭካኔ የተሞሉ ተከታታይ ድርጊቶችና/ ወይም ዛቻና/ ወይም ማዋረድ ነው። አንዳንዴም አንዴ ብቻ የሆነ ድርጊት(??) እግልት ሊያስከትል ይችላል።

**የትኞቹ የቤተሰባዊ ግንኙነት ማዕቀፎች ናቸው በጥቃትና በእንግልት ሊሠቃዩ የሚችሉት?**

- (በተጋቡ/በተፋቱ) የትዳር ጓደኛሞች መካከል ያለ ግንኙነት፦ ሚስቱን በሚመታ ባል ወይም ባሏን በምትመታ ሚስት መካከል ያለ ግንኙነት።
- በወላጆችና በልጆች (በወለዷቸው ልጆች/በእንጀራ ልጆች/በማደጎ ልጆች) መካከል ያለ ግንኙነት፦ ልጁን በሚመታ ወላጅ ወይም ወላጁን በሚመታ (የደረሰ ልጅ) መካከል ያለ ግንኙነት።
- በወንድማማቾች መካከል ያለ ግንኙነት።
- በጎልማሶች ልጆችና በአዛውንቶች ወላጆች መካከል ያለ ግንኙነት።

**የትኞቹ የቤተሰባዊ ግንኙነት ማዕቀፎች ናቸው በጥቃትና በጾታዊ እንግልት ሊሠቃዩ የሚችሉት?**

- በትዳር ጓደኛሞች መካከል ያለ ግንኙነት፦ ከትዳር ጓደኛሞች አንዱ ሌላውን ለሩካቤ ሥጋ ሲያስገድደው።
- በወላጆችና በልጆች (በወለዷቸው ልጆች/በእንጀራ ልጆች/በማደጎ ልጆች) መካከል ያለ ግንኙነት፦ አባት/እናት ወንድ/ሴት ልጁን ወይም ልጇን ለሩካቤ ሥጋ ሲያስገድዱ።
- በወንድማማቾች መካከል ያለ ግንኙነት፦ታላቅ ወንድምና ታናሽ ወንድም ወይም መንትያ ወንድማማቾች።
- በአጎት ልጆች መካከል ያለ ግንኙነት፦ የዕድሜ ልዩነት ባላቸው ወይም ደግሞ በዕድሜ እኩያሞች በሆኑ ወንድማማቾች መካከል አንዱ ሌላውን ለሩካቤ ሥጋ ሲያስገድደው።
- በወንድ አያትና በወንድ/በሴት የልጅ ልጅ መካከል ያለ ግንኙነት፦ የወንድ አያት የወንድ/የሴት የልጅ ልጁን ለሩካቤ ሥጋ ሲያስገድደው።
- በአጎትና በወንድም ወይም በእኅት ወንድ/ሴት ልጆች መካከል ያለ ግንኙነት፦ አጎት የወንድሙን ወይም የእኅቱን ወንድ/ሴት ልጅ ለሩካቤ ሥጋ ሲያስገድደው።

==============================================================

==============================================================

## በቤተሰብ ውስጥ የጥቃት ስንዘራና የእንግልት መገለጫ መንገዶች

- አካላዊ ጥቃት ስንዘራ፦ መማታት
- ልቦናዊ ጥቃት ስንዘራ፦ ስድብን እና/ ወይም ማጣጣልን እና/ወይም ዛቻን እና/ወይም የስሜት ምዝበራን በመጠቀም።
- ጾታዊ እንግልት፦ያለ ስምምነት ወይም የበላይነት በመጠቀም ለሩካቤ ሥጋ ማስገድደው።
- አለመንከባከብ (በአብዛኛው ልጆችን በሚመለከት ነው)፦ ምግብ፣ ልብስ፣ ንጽሕና እና ሕክምናን ለመሳሰሉት ለአካላዊ ፍላጎቶቻቸው ግድ ባለመስጠት፤ ወይም ደግሞ ለስሜታዊ ፍላጎቶቻቸው ፍቅር፣ ትምህርት፣ አስተዳደግና ዕድገት ደንታ ቢስ በመሆን።
- ኢኮኖሚያዊ ጥቃት ስንዘራ(በአብዛኛው ሚስቶችን በሚመለከት ነው)፦ሙሉ ጥገኝነትን በመፍጠር፣ የገንዘብ ንክኪን በመንሣት፣ አስቀድሞ ውሱን የበጀት መጠን በመስጠት፣ ወጥቶ መሥራትን በመከልከል፣ በአባካኝነት።
- ማኅበረሰባዊ ጥቃት ስንዘራ(በአብዛኛው ሚስቶችን በሚመለከት ነው)፦ መንጓለል፣ የውሎ ቦታቸውን እና/ወይም ከሰዎች ጋር የሚዞሩት ዙረት በመቆጣጠር።
- ዜግነት ነክ የጥቃት ስንዘራ(በአብዛኛው ሚስቶችን በሚመለከት ነው)፦ ሚስትየው እስራኤላዊት ያልሆነች እንደሆነ፣ በትዳር ዘመን ሆን ተብሎ የሚደረግ ዜግነትን ያለማስተካከል ጉዳይ።
- መንፈሳዊ እንግልት፦ ልክ ነኝ እያሉ መንፈሳዊ ማስረጃዎችን በአብዛኛው ከመጻሕፍት መብትን ያላግባቡ ለመጠቀም እና/ወይም ከተጠቀሱት ለአንዱ ወይም ከዚያም በላይ ለሆኑ የጥቃት ስንዘራዎች እንደ ማስረጃነት በመስጠት።

**የጥቃት ስንዘራ ዑደት**

አብዛኛውን ጊዜ በቤተሰብ ውስጥ ያለ የጥቃት ስንዘራ የዑደት ይዘት ኖሮት ይታያል። ይዘቱ በውጥረቶች መጠራቀም ይጀምርና እስከ ጥቃት ስንዘራ ድረስ ይደርሳል፤ ከዚያም በኋላ ወደ እርቅና ይቅር ወደማባባል ደረጃ ይደረስና፣ ወደ መረጋጋትና ፀጥታ ይመለሳል - ማለትም እስከሚቀጥለ የቁጣ ጡፈት ጊዜ ድረስ።

አብዛኛው የጥቃት ስንዘራ ዑደት፦ የውጥረቶች መጠራቀም ውጤት ነው ማለትም ጥቃት ሰንዛሪው ሰው መናደድ ይጀምራል በሂደቱም እጅግ ይጎዳሉ > ጥቃት ስንዘራው ይከሰታል > ጥቃት ሰንዛሪው ሰው እንዲህ ላለው ጥቃት ወደ መሰንዘር ያደረሰው ተጎጂው ራሱ እንደሆነ አድርጎ ይወነጅለዋል እናም/ ወይም እንግልት ከነመደረጉም ይክዳል እናም/ ወይም የጥቃቱን ብርቱነት ያቃልለዋል እናም/ ወይም ይቅርታ ይጠይቃል እናም/ ወይም ይህ ሁኔታ ዳግም እንደማይሆን ቃል ይገባል >  መረጋጋት ይሆናል፤ ከዚያም ጥቃት ሰንዛሪው ሰው በአኳኋኑ ጥቃት እንዳልተሰነዘረ ዐይነት ይሆናል፣ ጥቃት አይሰነዝርም፣ ቃሉንም ይጠብቃል > እንደገናም ውጥረት ይጠራቀምና ሁኔታው ይደገማል።

በጥቃት ስንዘራ ግንኙነት ውስጥ ዑደቱ መቶ ጊዜ ሊደጋገም ይችላል፤ በግንኙነት ማዕቀፍ ውስጥ እያንዳንዱ ደረጃ ለተለያየ የጊዜ ገደብ ሊቀጥል ይችላል። ሙሉው ዑደትም ከሰዓታት እስከ ዓመታት ሊቀጥል ይችላል።

ሊዘከር የሚያስፈልገው ነገር - ቤተሰባዊ እንግልት ሁሉ ከላይ በምሳሌነት ከተጠቀሰው ዑደት ጋር የግድ አይጣጣምም። እንዲሁም አንዳንዴ በጊዜ ሂደት የእርቁና የእርጋታው ደረጃ ጨርሰው ይጠፋሉ።
============================================================

# ጥቃት በትዳር ጓደኞች መካከል

በትዳር ጓደኞች መካከል ያለ የጥቃት ስንዘራ ዐይነት ለበርካታ ድብድብ የመጋበዝና የጨቋኝነት ሁነቶችን ያካትታል፤ ከፊሉ አካላዊ ጉዳት ያለበት፥ ከፊሉም የሌለበት፣ የተወሰነው ወንጀል ነክ የሆነ፥ የተወሰነውም እንደዛ ያልሆነ ነው። ይሁን እንጂ ሁሉም ሆን ተብሎ የወንድ/የሴት ትዳር ጓደኛን በሥነ ልቦናዊ ቁጥጥር ስር ለማዋል የታለሙ በመሆናቸው፥ ሥነ ልቦናዊ ፍራቻን ያሳድራሉ።

ጥንዳዊው የጥቃት ስንዘራ በወንድ ጥቃት ሰንዛሪነትና በሴት የጥቃት ሰለባነት የሚያበቃ አይደለም። ሴቷም ጥቃት ሰንዛሪ የምትሆንበትና ሴትም ሆነች ወንድ የጥቃት ሰለባና ተጎጂዎች የሚሆኑባቸው ሁኔታዎች አሉና።

======================================================================

## ወንዶች በሴቶች ላይ የሚሰነዝሯቸው የጥቃት መንገዶች።

- አካላዊ እንግልት፦ በመማታት፣ በግፊያ፣ በጥፊ፣ በድብደባ፣ በእሳት ማቃጠል፣ የሰውነት ክፍሎችን በመጠምዘዝ፣ በማነቅ፣ ፀጉርን በመንጨት፣ ወደ መውጫው በር እንዳይደርሱ በመከልከልና መሣሪያ በመጠቀም ነው።
- ስሜታዊ ወይም ልቡናዊ እንግልት፦ የማሰብ ችሎታዋን፣ የሴቷ ምክንያታዊነትን፣ ሊሰማት መቻሏንና ክህሎቷን፥ በማቃለልና በማጣጣል በማስፈራራት ጉዳት ማድረስ ነው። ሴት ስለ ራሷ ያላትን ግምት ዘዴያዊ በሆነ ሥላቅ ፍቅርን እየነሡ በማንጓጠጥ በማጣጣል በዛቻ ባለማነጋገርና ባለማዳመጥ፤ ውሎዋንም ሁሉ መጨረሻ በሌለው ንዝነዛ በመነዝነዝ፤ ከልክ ባለፈ ቅናት ከጓደኞቿ ማራቅ ወይም በሴቶች ጉዳይ ከመሳተፍን በመከልከልና በጊዜ በመወሰን መጉዳት ነው።
- ፆታዊ እንግልት፦ ሴትን ያለፍላጎቷ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ወይም ወሲባዊ ድርጊቶችን እንድትፈጽም ማስገደድ። በሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ጊዜም በጉልበት መጠቀምና ማስፈራራት በብልግና የወሲባዊ ስድብ መሳደብ።

- ገንዘብ ነክ እንግልት፦ ሚስት ገንዘብ ነክ በሆነ ጉዳይ ላይ እንዳትወስን መከልከል፤ ሚስት ተገቢ በሆነ ወጪ ሁሉ ላይ ተስማሚ እንድትሆን መጠየቅ፣ በገንዘብ ነክ ችግሮች ላይ እርሷን ጥፋተኛ ማድረግ፣ ገንዘብ ነክ መረጃዎችን መንሣት፣ ከቤት ውጪ እንዳትሠራ መከልከል።
- በንብረት ላይ ጥፋት ማድረስ፦ የሚስትን የግል ዕቃዎች ወይም የቤተሰብ ንብረቶችን፣ የቤተሰቡ የሆኑ የቤት እንስሶችንም እንኳን ሳይቀር ማውደም።

## ባል በሚስት ላይ የሚሰነዝረው የጥቃት ተፅዕኖዎች።

- ማጣጣል፦ ሚስት ስለ ራሷ ያላትን ግምት ማጥፋት፥ በተለይ ደግሞ በሌሎች ፊት የሚያጣጥላት ከሆነ።
- ከቁጥጥር ውጪ መሆን፦ሚስትን በመደበኛነት ከተለመዱ ሥራዎችንና ሁነቶችን በውሳኔ ማስቀረት። በዚህ የሚስትየው የመወሰን ችሎታ ይጎዳል።
- ማድከም፦ እንዳትቃወም ወይም አማራጭ እንዳትፈልግ አካላዊ እና/ወይም ልቦናዊ ጉልበቷን ማዳከም።
- ከንቱ ተስፋ፦ ሚስት ባሏ አኳኋኑን ሊቀይር እንደሚችል፥ ነገሩም በእርሷ እንደሚወሰን ማለትም አኳኋኗን ከቀየረች አልፎ አልፎ የተሻለ አቀራረብ ሊኖረው እንደሚችል ማመን ትጀምራለች።
- ጥገኝነት፦ ሚስት ደረጃ በደረጃ ጊዜዋን፣ ግብአቶቿን፣ ምርጫዎቿንና በመጨረሻም አስተሳሰቧንና ሐሳቧን መቆጣጠር ይሣናታል።

## ሚስቶች ርዳታ ለመጠየቅ የሚቸገሩት ለምንድን ነው?

- ጥቃታዊ ምላሽን በመፍራት፦ ብዙውን ጊዜ ሚስት ባሏ እንዳያገኛት ለመሸሽ፣ ለፖሊስ ወይም ለሌሎች አካላት ለማሳወቅ ትሠጋለች። ሥጋቷ የሚመጣው ይህ እርምጃዋ ተጨማሪ የጥቃት ሰንዘራና በሕይወቷ ላይ የሚደረግ ዛቻን ያስከትላል ከሚል አስተሳሰብ ነው።
- ውርደት/ሀፍረት/የጥፋተኝነት ስሜት፦ ሚስት በእርሷና በበሏ መካከል የሚሆነውን ለማጋለጥ ታፍራለች።
- እንደሌለ አድርጎ በመካድ ሁኔታው ይሻሻላል ብሎ ማመን፦ ሚስት ባሏ እንደሚቀየር እና/ወይም ቀድሞ እንደነበረ እንደሚሆን ተስፋ ታደርጋለች። ይህ የሚሆነው ደግሞ በተለይ ከጠፊ ግልፍተኝነት በኋላ ባል ተፀፅቶ፥ ይህ ዐይነቱ አኳኋን እንደማይደገም ቃል በሚገባበትና የእርጋታ ፋታ በሚያገኙበት ወቅት ነው።

- የአካባቢ ዝግነት፡- አንዳንዴ ይልቁንም ቤተክርስቲያንና ቤተሰብ በሚስት ላይ ጫና ያከብዳሉ፣ እርሷን በመደገፍና በመርዳት ፈንታ የቤተሰባዊው መድብል ሙሉነት ጠቃሚነት ላይ በማተኮር፥ ሚናዋን ይተቻሉ።
- ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት፡-ሚስት ሁልጊዜ ከትዳር ማዕቀፍ ውጪ የኢኮኖሚያዊ ድጋፍ ምንጮች የሏትም፤ በመሆኑም የባሏ ጥገኛ ነች፤ ራሷን እና/ወይም ልጆቿን ማስተዳደር አትችልም።
- ከሀገር መባረር፡- በሀገር ውስጥ ሚስት ቋሚ የዜግነት መብት ከሌላት የምታካሂዳቸው ጉዳዮች ከትዳር አጋሯ አለያይቶ ከሀገር ሊያስባርሯት ይችላሉ።
- የቤተሰብ ሙሉነት፡- ሚስት በውስጣዊ ግጭት ትሆንና ከለላ ለማግኘት የምትወስዳቸው የማሳወቅ ወይም ርዳታን የመጠየቅ የመሳሰሉ እርምጃዎች ልትከላከልለት የምትፈልገውን ቤተሰባዊ መድብልንም ይበታትነዋል ብላ ትሠጋለች።
- መንፈሳዊ ችግር፡- ሚስት የቤተሰባዊው መድብል መበታተን የአምላክን ትእዛት ያፈርሳል ብላ ትሠጋለች።

## በትዳር አጋሮች መካከል ያሉ የጥቃት ስንዘራዎች በልጆች ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖዎች።

ጥቃት ሰንዛሪው የትዳር አጋር በሁለተኛው ወላጅ ላይ ልጆችን በልዩ ልዩ መንገድ በመሣሪያነት ሊጠቀምባቸው ይችላል።

- ልጆች በችግር ላይ ሲሆኑ ሁለተኛው ወላጅ እንዳያረጋጋቸው በመከልከል።
- በልጆች ፍላጎት ላይ ትኩረት ማድረግ እስከማይችል ድረስ ሁለተኛውን ወላጅ ማዳከም።
- በሁለተኛው ወላጅ ላይ የሕመምን ስሜት ለመፍጠር ልጅን በኀይለኛ ግትርነት መቅረብ።
- ልጅ ሁለተኛውን ወላጅ እንዲከታተለው ማዘዝ።
- ልጁ በሁለተኛው ወላጅ ላይ ጥቃት እንዲሰነዝርበት ድረስ በመፍቀድ ልጅን ለማሾፍ መጠቀም።
- ሆን ብሎ ልጁን ላደጋ ማጋለጥና ከዚያም መንጠቅ።
- ልጅ ወላጁን እንዲያስታርቅ በእርሱ ላይ ጫና ማሳደር።

- ጥቃት ስንዝራ በሰፈነበት ቤት የሚኖሩ ልጆች ሁሉ፥ በቤት ውስጥ ለሚሆነው ነገር፥ ተጨማሪ ሰለባዎች ይሆናሉ ለሁኔታው የተጋለጡ በመሆናቸውም የበለጠ ተፅዕኖ ያድርባቸዋል።

**ልጆችም የተለያዩ ሥነ ልቦናዊ ጉዳቶች ሊጎዱ ይችላሉ፤ በጤና ሁኔታዎች የሚከተሉትን የመሳሰሉ የስሜትና የዕድገት እክሎች ሊደርስባቸው ይችላል።**

- እንቅልፍ ማጣት
- ለመተኛት መፍራት
- ቅዠቶች
- ወደ ትምህርት ቤት የመሄድ ፍራቻ
- ከእናት የመለየት ፍራቻ
- የተጋነነ የመቁሰል ወይም የዐደጋ ጭንቀት
- ከሌሎች ጋር መጣላት
- ጥቃት ስንዝራ የሰፈነባቸው ጨዋታዎች
- በሌሎች ልጆች ላይ ወይም እንስሶችን ላይ ጉዳት ማድረስ
- ግልፍተኝነት
- ሌሎች ሰዎችን ወይም ከክንዋኔዎች መራቅ
- የመገለልና የመለየት ስሜት
- ራስን የማጥፋት ሙከራዎች
- የኀይለኝነት አኳኋን ማሳየት አለያም ግሩም የሆነ አኳኋንን ማዳበር
- የተጋነነ ስኬታማነት
- የወላጅ ኀላፊነትን መውሰድ (ለተጎዳው ወላጅ ለመከላከል ከመፈለግ የተነሣ)
- ጭንቀት
- የሆነ ዐይነት ችግር የመኖሩን ሁኔታ መካድ
- ከተደባዳቢው ጋር መወገን

**ወንድ የትዳር ጓደኛ ጥቃት ሰንዛሪ ስለመሆኑ የሚመሰክሩ ምልክቶች፦**

- በሴት የትዳር ጓደኛው ላይ ችክ ማለት
- ሽኩቻ መፍጠር፣ በየጊዜውም በመደወል ሴት የትዳር ጓደኛው ያለችበትን ለማወቅ መነዝነዝ፤ በስልክ ካላገኛትም ያለ ዕረፍት ደጋግሞ መደወል፣ ከዚያም ብዙ መልእክቶች መተው፣ በውሎዋ የትና ምን እንዳደረገች አብዝቶ መጠየቅ፣ ይህንንም ያለማቋረጥ እንድታሳውቀው መጠባበቅ።

- በተለይም ስትዘገይ ወይም በስልክ ሳያገኛት ሲቀር ከሌላው ጋር ተኝታለች ብሎ መጠርጠር።
- ስለ እርሷ እርሱ እንዲህ መሆን አለበት ይላል ይወስናል በስሚም ይናገራል የምታደርገውን የምትለብሰውን ይወስናል። ለምታደርጋቸው ነገሮችም ሆነ ለሥራዎቿ ከእርሱ ፈቃድ እንድትቀበል ያስገድዳታል።
- የትዳር ጓደኛውን ከቤተሰብ እና/ወይም ከጓደኞቿ ለመለየት ይሞክራል። ብዙውን ጊዜም አብረዋት የሚሆኑትን እና/ወይም ቤተዘመዶቿንና ሌሎቹን፥ ከእርሱ ሊያስቷትና በመካከላቸውም ያለውን ግንኙነት ሊጎዱ እንደሆነ አድርጎ በመጥፎ መልኩ ያነሣቸዋል።
- እርሱ በአካባቢው ሳይኖር ሚስቱ ከሴቶች ጓደኞቿ ጋር እና/ወይም ከቤተዘመዶቿን ጋር መዝናናቷን በጥሩ ዐይን አያየውም፤ይህን ለእርሱ እንዳለመታመን ይቆጥረዋል፤ ከእርሱም ይልቅ እነርሱን እንደምትወድና ጊዜውንም እንደተሻሙት አድርጎ ያወራል።
- በቃላት፣ በአኳኋኑ፣ በእንቅስቃሴዎቹ አማካይነት ሚስቱን ያስቀይማል ሥራዎቿንም ያጣጥላል ያፌዛል ይሣለቃል፤ ንግግሯንም ያቋርጥባታል፣ ፍሬ ቢስ ንግግር እንደሆነም በገጽታው አኳኋን በማሳየት በግልም ይሁን ከሰዎች ጋር ሆና አላናግር ይላታል።
- ሚስቱን ወደ ሥራ ወይም ወደ ትምህርት ወደ ማኅበረሰባዊ ጉዳዩች እንዳትሄድ ይከለክላታል።
- ተለዋዋጭ ጠባይ ያላቸውማ የሚቀያየሩት በፍጥነት ነው፤ የሚመሰሉትም በከፍታና በረባዳ ዑደት ዐይነት ነው።
- አሁንም አሁንም ቱግ፣ ግልፍ ይላል።
- ሚስቱን ይሳደባል።
- ዕቃዎችን ይወረውራል፤ ያወድማልም።
- ያለ ሴቷ ፈቃድ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን ወይም ወሲባዊ ድርጊቶችን ማድረግ ይፈልጋል።
- ሚስቱን ይመታል፣ ይገፋታል፣ በጥፊ ያጮላታል ወዘተ።
- ጥሏት እንደሚሄድ ወይም በሌላ ቅጣት እንደሚቀጣት በቃልና ቃል አልባ በሆነ መንገድ ሚስቱ ላይ ይዝታል።
- በተለይም ሚስቱ ጥላው የሄደች እንደሆነ ራሱን እንደሚያጠፋ ይዝታል።
- ሚስቱ ከተለወጠች ብቻ እርሱ እንደሚለወጥና ሁሉ ሰላም እንደሚሆን ያምናል።
- የትዳር ጓደኛው የማይቻላትን ጥያቄ ይጠይቅና ሳይሆንላት ሲቀር ይቀጣታል።
- በመካከላቸው ስላለው ግንኙነት ወይም በራሱ ችግሮች ሚስቱን ይተቻል፤ ይወነጅላልም።

- ትክክል ያልሆኑ ሁኔታዎችን በነገር ይሰነጣጥቃል።
- በራሱ ኀላፊነት በሆኑ ችግሮች ሚስቱንና አካባቢውን ይወነጅላል።
- ለሚስቴ ቅናት ፍቅር አለኝ በሚል ሰበብ ድርጊቱንና ቁጣውን ያጸድቃል።

### ሴት በጥቃት ስንዘራ የምትሠቃይ ስለመሆኗ ሊመሰክሩ የሚችሉ ምልክቶች፦

- የባሏን ምላሽ ትፈራለች።
- ባሏን እንዳታስቆጣ ወይም እንዳትጎዳ ስትል ተራ ነገሮችን ሳይቀር ማድረግ ትፈራለች።
- የሚያስፈልጓትን ነገሮችና ፈቃዱን በማይገባ መልኩ ትተዋለች።
- ለተራ ድርጊቶች እና/ወይም ለመሠረታዊ ነገሮች በተደረጉ የገንዘብ ወጪዎች የባሏን ፈቃድ ትጠይቃለች።
- ታስረዳለች፣ ይቅርታ ትጠይቃለች፣ ትከራከራለች።
- "ልክ አይደለሁም" የማልጠቅምና ደካማና ዋጋ ቢስ ነኝ በሚል የጥፋተኝነት ስሜት የተመላች ነች።
- ከባድ ቀን ስላሳለፈ ነው በደንብ ስላልተኛ ነው ወዘተ በማለት የባሏን አኳኋን ትሸፋፍንለታለች።
- ከሌሎች በመለየት ብቸኛ ትሆናለች።
- ሰበብ አስባብ የምትሰጥባቸው እና/ወይም ቃል ትንፍሽ የማትልባቸው የድብደባ ምልክቶች አሉባት።
- በራሷ ለመወሰን ትቸገራለች።

### ሴቶች በወንዶች ላይ የሚሰነዝሯቸው የጥቃት መንገዶች።

በዘመናችን በትዳር ጓደኞች መካከል ስላለው ጥቃት ሁኔታን፥ አጠቃላይ ሕዝባዊ ውይይት ትኩረት የሚያደርገው ወንድ ሴትን የማንገላታት ጉዳይ ላይ ነው። በቤተሰብ ከሚሆነው ጥቃት እንደ አንዱ ክፍል ተደርጎ፥ ስለሚደበደቡ ወንዶች በመገኛ ብዙሐንም ይሁን በጥናት ወይም በማኅበረሰባዊ ጉዳይ ሠራተኞችም ሆነ በሕግ አስከባሪ አካላት ዘንድ ምንም የሚነገር ነገር የለም።

ሴት ወንድን የምታንገላታበት ሁኔታዎችም አሉ። ከሴት በኩል የሚሰነዘረው ጥቃት ግን አብዛኛውን ጊዜ የሚገለጸው ንግግራዊና አእምሯዊ እንግልት ነው፤ ይሁን እንጂ የአካላዊ ጥቃት ስንዘራ ሁኔታዎችም አሉ።

ሆኖም ስለ ጉዳዩ ገና በቂ ግንዛቤ ባለመኖሩ ወንዶች ስለዚህ ነገር እንዲናገሩ ማበረታታት ያስፈልጋል።

==============================================================

# ለጥንድ ዳንስ፥ ሁለት የመሆኑ ጉዳይ እርግጥ ነውን?

## የጥቃት ሰንዛሪ ግንኙነቶች እንቅስቃሴ

*"በቁጥጥር ሥር ማድረግና በቁጥጥር ሥር መሆን አንድ ሥነ መለኮታዊ ገጽታን ይፈጥራሉ፤ አንዱም የለሌላው ሙሉ አይሆንም" (ዊኒኮት)*

በተንኳይና-ተተንኳይ ግንኙነት ውስጥ እኛ የለመድነው፥ እነዚህን ጎራዎች ተተናኳይና ተተንኳይ፣ አሸናፊና ተሸናፊ ብሎ መከፋፈል ነው። ሊስተዋል የሚገባው ነገር ግን ተጨባጩ ሁኔታ የበለጠ ውስብስብና አብዛኛውን ጊዜም በሁለቱ ሰዎች መካከል ያለው እንቅስቃሴ በአንደኛው ውስጥ ተንኳይነት በሌላኛውም ውስጥ ተተንኳይነትን የሚያነሣሣ መሆኑን ነው። በተተናኳዩና በተተንኳዩ መካከል የተፈጠረው ንጽጽራዊ ክፍፍል፥ በሂደቱ ውስጥ ድርሻቸውን ይወስንና ከወንጀይነት ወደ ተጠያቂነት የሚኖረውን የሁኔታ ለውጥ/ሽግግር ይከለክላል። አንዳንዴ ተተናኳዩና የተተንኳይነት ስሜት ይሰማዋል፤ ተተንኳዩም እንዲሁ የተተናኳይነት ስሜት ያድርበታል። <u>ስለሆነም ተተናኳዩ በትንኮላ ድርጊቶቹ ላይ መሥራት እንደሚያስፈልግ ሁሉ እንዲሁ ተተንኳዩም የሚጎዳውን ሽኩቻ ስለሚያባብሱት የገዛ አኳኋኖቹ ኀላፊነት መውሰድ አለበት።</u> በቤተሰብ ጥቃት ስንዘራና እንግልት ሁኔታዎች ውስጥ የወንዶችና ሴቶች ግንኙነት እጅግ ውስብስቦች ናቸው። ተተናኳዩ ወገን በከባድ የጥቃት ስንዘራና አዋራጅ አኳኋን ውስጥ እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ነው፤ በመሆኑም ሁኔታውን በትዕግሥትም ሆነ በመረዳት ማለፍ ክልክል ነው። ይህ ሲሆን ግን ይህን ሰበብ በማድረግ የተተንኳዩን አኳኋን አስቺጋሪነት ቸል ለማለትም አይደለም።

አብዛኛውን ጊዜ የተተንኳዩ አኳኋን ራሱን እስይ የሚያሰኝና ዝም ብሎ የሆነ ሽንፈታዊ አኳኋን ነው። ይህ ደግሞ የተተናኳዩን ጥቃት ስንዘራ ኀይለኝነት እያበረታታና እያደፋፈረ ሁኔታ ውን ለማባባብስ ምክንያት ይሆናል። እንዲህ ያለው የተተንኳዩ ራስን ሙሉ ለሙሉ የመጣል ሁኔታም የተተናኳዩን ራስ ወዳድነትና ኀይለኝነት ያበረታዋል። አንደኛው ጎን ብቻ ሙሉ ኀላፊነት በሚወስድበት ግንኙነት ውስጥም ሁለተኛው ጎን ያን የማድረግ ዕድል ፈንታ ይነሣል። ከሁለቱም በኩል ኀላፊነት ከሌለ ደግሞ - ዐደገኛ የሆነ አጋራዊ ጥገኝነት ይፈጠራል።

ስለሆነም በቤተሰብ የጥቃት ስንዘራና የእንግልት ሁኔታዎች ውስጥ፣ ሰለባው ተተናኳዩ ዘንድ ችግር እንደሌለ ለማስመሰልና እርሱን ደስ ለማሰኘት ሲል ስለተተናኳዩ ውድቀቶች ኀላፊነትን መውሰድ የለበትም። የተተናኳዩን ቁጣ ግልፍተኝነት ማስወገድም ቢሆን የሰለባው ድርሻ አይደለም።

ከግልፍተኝነት ሥጋት የተነሣ የተተንኳዩ ዝም ብሎ መጠቃት፥ ትክክለኛ የሆነውን ተጨባጭ ሁኔታ ከተተናኳዩ ዐይን ይሰውረዋል። ይህም ተተናኳዩን በድርጊቱ የሚያጸና አጥፊ ሁኔታ ነው።

ሁለቱም አንዱን ሜዳ ለጨዋታ መጋራቱን ተስማምተውበታልና፣ ተጠቂውም ጎን ማለትም ሰለባው፥ አጥቂው በሆነው በተተናኳዩ ድርጊቶች ውስጥ ይሳተፋል። ሁለቱም የጥቃት ስንዘራ ሰለባዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ ሁለት ገጽታ ወዳለው የመተነኳኮል ግንኙነት ተለውጠዋል። ምክንያቱ ይህ ብቻም አይደለም አንዱ ለገዛ ራሱ ተተናኳይነትን መፍቀዱ ብቻ ሳይሆን ሁለተኛውም ለዚሁ ድርጊት ታማኝ ወኪል በመሆኑ ነው እንጂ።

በዚህ መሠረት በቤተሰብ የጥቃት ስንዘራና የእንግልት ሁኔታዎች ውስጥ የተተናኳዩን አኳኋን መሉ በሙሉ ማውገዝና የተተናኳዩን ትንኮሳ አዘል አኳኋኖችን እንዳለ እንዲቀጥል የሚያደርጉትን የገዛ ራሱን ጠባዮች፥ ሊለውጣቸውም የመቻሉን ጉዳይ ተተንኳዩ እንዲረዳ ማገዝ ነው።

# ሰው አይለየው

በትዳር አጋሮች መካከል ያሉትን የጥቃት ስንዘራና የእንግልት ሁኔታዎች ቤተክርስቲያን መፍትሔ ለማግኘት ከምትቸገርበት ነገሮች አንዱ ይህን ማድረጉ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የቅዱሳን መጻሕፍትን በሚተላለፍ መልኩ መለያየትን እና/ወይም ፍቺን ሊያስከትል ይችላል ከሚል ፍራቻ ነው። ቢሆንም በቤተሰብ ያሉትን የጥቃት ስንዘራና የእንግልት ሁኔታዎች ባስመለከተ ለመፍትሔ ሲሠራ መለያየትና ፍቺ የሚለውን ርእስ ግምት ውስጥ አለማስገባት ያስቸግራል።

መለያየትና ፍቺ ስለሚለው ርእስ በብዙ የሥነ መለኮት ተመራማሪዎችና የሃይማኖት ሰዎች ዘንድ ሰፋ ያለ ውይይት ነበረ አሁንም አለ። ይህ ቅጽ በቤተሰብ ያሉ ጥቃት ስንዘራና እንግልት የሚለውን ርእስ በጥቂቱ የሚነካ በመሆኑና አጠቃላዩን የጋብቻ፣ የመለያየትና የፍቺ ርእስን የሚዳስስ ባለመሆኑ፣ የመለያየትና የፍቺ ዐይነት ከጥቃት ስንዘራና እንግልት ጋር በተያያዘ በጠለቀ የውይይት መልክ ሳይሆን ጠበብ ካለ እይታ ረገድ በመቀጠል ይቀርባል።

ከኢየሱስ በፊት ሙሴ፥ ባል ሚስቱን የእፍረት ነገር ስላገኘባት ወይም በፊቱ ሞገስ ባታገኝ እንዲፈታት ፈቅዷል(ዘዳ24፥1-4) በዚህም መሠረት የተፈታችውን ሚስት ሌላው ሊያገባት ይችላል።

እየሱስ ይህን ሲገልጽ ሙሴ ስለ ሰዎች ልብ ጥንካሬ ይህን ፈቀደ እንጂ፣ ከቀድሞ የአምላክ ዕቅድ ለሰዎች ይህ እንዳልነበረ ተነግሯል።

“ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ ስለ ልባችሁ ጥንካሬ ይህችን ትእዛዝ ጻፈላችሁ። ከፍጥረት መጀመሪያ ግን እግዚአብሔር ወንድና ሴት አደረጋቸው፤ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤ ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም።” (ማር10፥5-8)

እየሱስ የመጣው፥ የጋብቻን ኪዳንና ቤተሰባዊውን መድብል ሊያድስና የፍጥረትን ሥርዐት ወደ ነበረበት ሊመልስ ነው። ቤተሰባዊውን መድብል ለመበታተንም ምንም ዐይነት ማጽደቂያ መንገድ እንደሌለና በአምላክ ፊት የጋብቻን ኪዳን ለማፍረስ ማጽደቂያ ምክንያት “በዝሙት ምክንያት” ብቻ እንደሆነም አስረዳ። በዚህ አገባብ “በዝሙት ምክንያት” ለሚለው ፅንሰ ሐሳብ የተለያዩ ማብራሪያዎች መኖራቸውንም ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ይህ ምክንያት የተጠቀሰው ደግሞ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 19፥9 ብቻ??(ከማርቆስ10፥9-12 እና ከሉቃስ16፥18 ለመለየት) መሆኑንም ማስታወስ ያስፈልጋል።

የሚጠቅሰውም ሴቲቱ በፈጸመችው (እንጂ በተገላቢጦሹ ያልሆነ) "ዝሙት ምክንያት" ባል ሚስቱን መፍታት መቻሉን ብቻ ነው።

የትዳር አጋሮች "ያለ ዝሙት ምክንያት" ከተለያዩና ከሌሎች ጋር የግንኙነት ማዕቀፍ ከፈጠሩ አመነዘሩ ማለት እንደሆነ አስተምሯል።

"እኔ ግን እላችኋለሁ፥ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፥" (ማቴ19፥9)

የዚሁኑ ሳንቲም ሌላውን ገጽታ ስናይ ደግሞ የትዳር አጋሮች ከተለያዩና በአንድነት የማይኖሩ ከሆኑ ወይም ደግሞ ከሕግ አንጻር እንደተፋቱ ሆኖ ከተቆጠረ፤ ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት እስካልመሠረቱ ድረስ በአምላክ ፊት የጋብቻን ኪዳን አላፈረሱም ብሎ መደምደም ይቻላል።

በእርግጥም ይሆን ዘንድ ታስቦ የሚደረገው ጥረት የትዳር አጋሮች እንደ "አንድ ሥጋ" ሆነው እንዲሠሩና አምላክ ያጣመረውን እንዳይለዩ ነው።

ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤ ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው። (ማር10፥8-9)

'እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው' የሚለው የእየሱስ ትእዛዝ፤ አትፍረዱ፣ በሐሳባችሁ አታመንዝሩ፣ ሰዎችን አትፍሩ ከሚሉት ከሌሎቹ ትእዛዛት አይለይም። እንዲህ ያሉ ግልጽ ትእዛዛት እያሉን አብዛኛውን ጊዜ እንፈርዳለን፣ በሐሳባችን እናመነዝራለን፣ ሰዎችንም እንፈራለን። እንዲሁም ሰው እግዚአብሔር ያጣመረውን ለመለያየት ብዙ ያደርጋል።

ይህ ነገር አግባብ ያለው ባይሆንም በተወሰኑ አጋጣሚዎች የሚታየው ተጨባጩ ሁኔታ ግን ይኸው ነው፤ ስለ እነዚህ ሁኔታዎችም ቅዱሳን መጻሕፍት ይናገራሉ፦ በ1ቆሮ7፥10-15 ወንድም ሆነ ሴት እንዳይለያዩ ታዝዘዋል፤ ነገር ግን በዝሙትም ምክንያት ባይሆን መለያየት ሊከሰት የሚችልበት ተጨባጭ ነገር መኖሩንም ይናገራሉ። በእነዚህ አጋጣሚዎች በተጻፈው መሠረት የትዳር አጋሮች አኗኗን "ሚስትም ከባልዋ አትለያይ፥ ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር ወይም ከባልዋ ትታረቅ፥" ብለው ያዝዛሉ።

በማስከተልም መለያየት ሊከሰት ስለሚችልበት አጋጣሚ በ1ቆሮ7፥15 ከትዳር አጋሮች አንዱ በእምነት የማይኖርና መለየትን የሚመርጥ ከሆነ ይለይ ተብሏል።

በጥቃት ስንዘራ የሚመላለስ አማኝ የትዳር አጋር እንደማያምን ሆኖ ሊቆጠር ይችላል ብለው የሚሉም አሉ። ይህም በ1ጢሞ5፥8 ከተነገሩት ነገሮች አንጻር ማለት ነው።

“ነገር ግን ለእርሱ ስለ ሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን፥ ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው።”

ከማያምን ባለመሻሉና በቤቱም ውስጥ ፍራቻን በማስፈኑ መለየትም ባይፈልግ እንኳን ያው የመለያየትን ሁኔታ እንደሆነ ፈጥሯል። በዚህ መረዳት መሠረት ጳውሎስ በ1ቆሮ7፥15 ያለው ለዚህ ሁኔታ ይሠራል፦

የማያምን ግን ቢለይ ይለይ፤ ወንድም ቢሆን ወይም እኅት እንዲህ በሚመስል ነገር አይገዙም፤ እግዚአብሔር ግን በሰላም ጠርቶናል።

ማጠቃለያ ቅዱሳን መጻሕፍት መለያየት ሊኖር መቻሉን በትክክል ይናገራሉ። ይህ ግን አካላዊ መለያየት ይሁን ወይም ሕጋዊ ፍቺ ማብራሪያ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። በማንኛውም የመለያያ ሁኔታና መንገድም ቢሆን፥ የትዳር አጋሮቹ ወደ ጋብቻ ቃል ኪዳን የደረሱት በመንፈሳዊ ረገድ በመሆኑ፣ በነገሮች ያልተያዙ በመካከላቸውም ለእርቅና ለንስሓ ቦታ የተው መሆን አለባቸው።

ቅዱሳን መጻሕፍት መለያየት ሊኖር የመቻሉን ነገር መናገራቸው በትዳር አጋሮች መካከል ላለው የጥቃት ስንዘራ መፍትሔነት የበለጠ ጠቃሚነት አለው። እየሱስ መለያየትን እና/ ወይም ፍቺን ፍጹም የመከልከሉ ጉዳይ፥ ጉዳት አድራሹን በጉልበተኝነቱ ሲያጸናው፣ ተጎጂውን ደግሞ በሕይወቱ ዐደጋ ላይ የመውደቅ ሁኔታ እና የአምላክን ትእዛዛት በመተላለፍ ሁኔታ መካከል የመሆን ከባድ ግር መሰኘት ውስጥ ይጥለዋል።

ጌታ በልዩና አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥም መውጫ ከሰጠን፣ ለሚያስፈልጋቸው ይህ መውጫ በመንፈግ እንቅፋትን ማኖር የለብንም።

# ጥቃት እና/ወይም እንግልት በልጆች ላይ

በልጆች ላይ የሚሰነዘር ጥቃት እና/ወይም እንግልት ለልጆች፣ ለወላጆች ብሎም ለመላው ቤተሰብ ክፉ፣ ጤና ነሺና አፍራሽ ነው። ልጅ በሸክላ ሠሪ እጅ እንዳለ ሸክላ በመጀመሪያቹ የሕይወቱ ዘመናት፥ እጅግ ጠቃሚው በሆኑት አካላት የሚደረግ ታላቅ ተፅዕኖ የሚያርፍበት ነው። ስለሆነም በወላጅ ልጅን የመቅረጽ ዐቅም ውስጥ ታላቅ ኀላፊነት አለ።

የማይሳሳቱና አንዳንዴም የልጆቻቸውን ስሜት የማይጎዱ ወላጆች የሉም፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ጉዳቶች ሲደጋገሙ ደግሞ እግልትን ይባላሉ። ይህ የወላጆች ልጆችን ማንገላታት ሁኔታ በአራት መልኩ ሊፈረጅ ይችላል፦ አካላዊ፣ ጾታዊ አእምሯዊና አመጋገባዊ። ከእነዚህም ማንኛዎቹም ቢሆኑ በልጁ የወደፊት ዕድገትና ሕይወት ላይ ዐደጋ ያደርሳሉ።

በወላጆች እንግልት የደረሰባቸው ልጆች በአብዛኛው የሰለባነትን እና/ወይም የተተናኳይነትን ዝንባሌ ያሳያሉ።

የሰለባነት ጠባይ ቁጣን፣ ትንኮላንና ፍራቻን በውስጡ አርቆ፥ ራስን በማጥፋት፣ በቁዘማ፣ በብኩንነት ሐሳቦች፣ በዐይን አፋርነትና ከሌሎች ጋር ባለመግባባት ዝንባሌው ይገለጣል።

የተተናኳይነት ጠባይም ሥቃይን ወደ ውጪ በማውጣት፥ በተጋነነ አኳኋን፣ ባለመታዘዝ፣ ዕቃዎችን በማውደምና ግንኙነትን በማደፍረስ ዝንባሌው ይገለጣል።

እዚህ ላይ ሁኔታዎቹም ሆኑ ልጆቹ የተለያዩ መሆናቸውን ማሰቡ አስፈላጊ ነው። የሰለባነትን ጠባይ የሚያሳዩ ልጆች አሉ፤ የተተናኳይነት ጠባይ የሚያዳብሩም አሉ፤ አለያም ሁለቱንም ጠባዮች በአንድነት የሚያሳዩ አሉ፤ ወይም ደግሞ ጠባዮቹን በተለያዩ የሕይወታቸው ደረጃዎች የሚያዳብሩም አሉ።

እንግልት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ በመሆኑ፣ እንግልት የደረሰባቸው ልጆች ራሳቸው አንገላቾች የመሆን ከፍተኛ ዐደጋ ውስጥ መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል። ከወላጆቻቸው እንክብካቤና ድጋፍ ያላገኙ ልጆች በቀጣይ የባሰውን ኀይለኞች ሊሆኑና ይህን ጠባያቸውን ለልጆቻቸው ሊያወርሷቸው ይችላሉ።

ስለዚህም የልጆችን በእንግልት መሠቃየት ቀደም ብሎ ማወቁ በጣም ጠቃሚ ነው። ለእንግልት ምስክርነት ያላቸው ምልክቶች ከልጅዬው፣ ከወላጁ ወይም ደግሞ በመካከላቸው ካለው መስተጋብር ሊታይ ይችላል። እነዚህም ምልክቶች ቀጥታ በንግግር፣ በአካላዊ ቋንቋ፣ በአኳኋን፣ በሥዕልና በጨዋታ ሊገለጡ ይችላሉ።

ማስታወስ ያለብን ነገር አብዛኛውን ጊዜ ልጅን የሚያንገላታ ወላጅ ጥቃት ስንዘራ ተቀባይነት የሌለው ነገር መሆኑን ስለሚያውቅ ሁኔታውን ይደብቃል። ስለሆነም ተጨባጩ ሁኔታ ሌላ ሆኖ እያለ በማኅበራዊ ድግሶች ላይ ከንቱ አስመሳይነትን የተላበሰ የፍቅር ስሜት ማሳየቱ ሊዋጣለት ይችላል። ስለዚህ በቤተሰብ ውስጥ ያለውን የአኳኋንና የመስተጋብር ልዩነቶችን ልብ ማለቱ ይመከራል።

ልጅ ወላጁ የሚያደርስበትን እንግልት አውጥቶ ለመናገር ብዙ ድፍረት ያስፈልገዋል፤ በልጅ አፍ የተጋለጠን፥ ያውም ደግሞ ጾታዊ እንግልትን ሲሆን፥ ለማድመጥ ቀላልም ባይሆን፤ በተገቢው ሁኔታ ምላሽ መስጠትና ልጁን ነገሩ ተአማኒነት እንዳለው እንዲሰማው ማድረግ አስፈላጊ ነው። ለማመን ብንቸገርም እንኳን በምንም ዐይነት መንገድ የልጁን አቤቱታ መንቀፍም ሆነ መግፋት የለብንም። እንግልት መፈጸሙን የማመኑ ሁኔታ፣ ልጁንና ቤተሰቡን ከመርዳት ተነጥሎ የማይታይ ጉዳይ ነውና።

ድርጊቶች አጋልጠው አዎንታዊ ምላሽ ካገኙት ልጆች አንጻር፤ የተደረጉበትን ድርጊቶች ለሆነ ሰው ያጋለጠና ከሰውዬው አሉታዊ ምላሽ ያገኘው ልጅ ሰቀቀን ይሆንበታል፤ ወደፊትም ደግሞ የበለጠ ይሳቀቃል።

### የቤተክርስቲያን አግልጋይ የሆነ አባት ያላት ሴት ልጅ ምስክርነት

ሰዎች ሁሉ የሚወለዱት የተወሰነ <u>ኀይለኝነት</u> ኖሯቸው ነው። ልጆች ትንሽ ሳሉ ወላጆቻቸው ስለ እነርሱ ግድ ስለሚላቸው በፍቅር በመያዝ የግንኙነትን መንገድ፣መረዳትንና ተሳትፎን ያስተምሯቸዋል። እነዚህ ሁሉ በቤት ውስጥ ካለው ግንኙነት ወላጅ ሁሉ ከልጁ ጋር በሚኖረው ግንኙነት እንጂ ከመጻሕፍት አይማሯቸውምና።

ወላጅ ልጁን በሚመታው ጊዜ፣ በዚህ ድርጊቱ ለልጁ አኳኋን አሉታዊ የሆነ ምሳሌን ያሳየዋል። ልጁም የተገባው አኳኋን የትኛው እንደሆነ፣ "ተቀባይነትም ያለው ሁነት" የቱ እንደሆነ የሚያውቀው ነገር የለም፤ ይልቁንም እንዲህ ያለ ሁኔታ በሰፈነበት ቤት ውስጥ በማደጉ፥ በቤተሰብ ውስጥ ጥቃት ስንዘራ ክልክል መሆኑንም አያውቅም። ትልልቅ ሰዎች ይህንን እንደ ቀጣይ ቅኝት ሊመለከቱት ይችሉ ይሆናል፤ ለልጅ ግን ወቅት ወይም የተወሰነ የጊዜ ገደብ ብሎ ነገር የለም፤ ይህ ሕይወቱም፣ በሕይወቱም ዘመን ሁሉ የሚሆን ነውና።

የልጅ ማንነት ገና በደንብ ስላልጎለበተ በአካባቢው የሚሆነውን ሁሉ በራሱ ያላክካል። በቤቱ ወስጥ በሚሆነውም ሁሉ ራሱን ጥፋተኛ ያደርጋል፤ በሁኔታው መመሳሰልን ባይፈልግም እንኳን ወላጁ ያለውን ይቀበላል።

በውስጡ ያለው ቁጣና ብስጭትም በተወሰነ ደረጃ ላይ ወደ ውጪ ይወጣል። ይህም “መጥፎ ልጅ” በመሆኑ ሳይሆን፣ አኳኋኑ ሌላ ሊሆን ባለመቻሉ ነው።

በዚህም ሳቢያ ልጁ በሁለት ዓለም መኖርን ይለምዳል፦ በውጫዊው ዓለም ግልፍተኛ ወይም ዝግ ሆኖ፣ በውስጣዊው ዓለም ደግሞ የሕመም የብስጭት የኀፍረትና የፍራቻ ስሜት ሁሌም አብሮት የሚሆንና የማይጠፋ የፍራቻ ስሜት ይሰማዋል።

================================================================

ከተጨማሪ የልቅሶ፣ የጩኸትና የድብደባ ቀን በኋላ፣ እንደገናም ከትልቅና ረዥም አባት ፊት ለፊት ከቆምሁበት ሌላ ተጨማሪ ቀን በኋላ፣ ደግሞ ባለ 7 ሳንቲ ሜትር ውፍረት ቀበቶ ከተገረፍሁ በኋላ፣ እንዲሁም ስለ ራሴ ካሰብሰለሰልሁበት ተጨማሪ ቀን በኋላ “አባ እባክህን ተወኝ ….. እባክህን አትምታኝ” እያልሁ እንቀጠቀጥ፣ ዐነባ፣ በኀፍረት እከናነብና እፈራም ነበረ ሆኖም ማምለጫ አልነበረም። ለመተኛት ስለሚቸግረኝ፣ በጣም እቸገር የነበረው ደግሞ ሌሊት ሌሊት ነው፤ ምክንያቱም አብረን የምንሆነው እኔ ሐሳቦቼና ፍራቻ ብቻ በመሆናችን ነው።

ከፍራቻ ይሁን ከቤት ወይም ከገዛ ራሴ ይልቁንም ደግሞ ከደነዘዘ ተጠቂ ጠበኛ ሰውነቴ ማምለጫ አልነበረኝም። ይህ ቅድስተ ቅዱሳን ነውና በዙሪያዬ ከተቀጠረው ቅጥር ውስጥ ማንንም ላስገባ አልችልም። ወደ እዚህ ማንንም አያስገቡም።

እኔ በእውነትም ጣዕም የሌለው ልጅነት እንደሌለኝ፣ ይህንንም በፍጥነት መቋቋም እንዳለብኝና የምነግረውም እንደሌለኝ በተሰማኝ ጊዜ አካባቢዬን ስቃኝ፣ ልጆች ከአእምሮ በላይ በሆነ ታላቅ ደስታ እንዴት ይኖሩ እንደነበር፣ ከወላጆቻቸውም ጋር እንዴት ይጫወቱና ይስቁ እንደነበር አስታውሳለሁ። በቤትም ሆነ በውጪ ስለዚህ ጉዳይ አንድም ሰው ትንፍሽ አይልም። እንዲያው ብቻ ክልክል ነበር፤ እንዳይሆን ስለተባለ ሳይሆን፥ በቃ እንዲህ መሆን ስላለበት ነው። ቁስልን አይነካኩም። ጊዜ ይነጉዳል ነገሮች ግን አይለወጡም፤ ያኔ ትንሽ የነበረው ልጅ ከማደጉና በዙሪያው ተጨማሪ ቅጥሮች ከመገጥገጣቸው በቀር፥ ሕመሙም አይለወጥም።

የ10 ዓመት ልጅ በሆንሁም ጊዜ አንዴ በድፍረት ‘እናቴን ለቀቀን የማንሄደው ለምንድን ነው?’ ብዬ ጠየቅኋት እርሷም “እንዲህ ማድረጉ ጥሩ ስላልሆነ” አንለቅም አለችኝ።

“ይህ ጥሩ አይደለም፤ በፍጹም ጥሩ አይደለም” አለችኝ እናቴ። ታዲያ መሠቃየቱ ነው ጥሩ? አባ እንደሆን ቤቱን የሚያስተዳድረው እርሱ ስለሆነ የፈለገውን ማድረጉን ይቀጥላል ታዲያ ይህ ጥሩ ነው? እኔ ግን እንዲህ መቀጠል አልፈልግም ….. በፍጹም አልፈልግም….. ከዚህስ መሞት ይሻለኛል፤ እህስ ትንሽ ልጅ ሞቷን ስትመርጥ ይህ ጥሩ ነው?

አይደለም፤ ጥሩ አይደለም! ስለዚህ እኔም ጥሩ አንዳይደለ ለመግለጽና አሁን ድምፃቸውን ማሰማት የማችሉትን ልጆች ሁሉ ለማሰማት እጽፋለሁ።

በክርስቶስ አካል ውስጥ ይህ ችግር መኖሩንና ይህንንም እንዴት መቋቋም እንዳለባቸው ባለማወቃቸው ብዙዎቹ ላለማየት ዐይኖቻቸውን የጨፈኑበት ጉዳይ መሆኑን ለመመስከር እጽፋለሁ።

ምንም የማናደርግ ከሆነም ችግሩ እንደማይጠፋና እያደገ እንደሚሄድ ብሎም ርዳታ የሚያስፈልጋቸው ርዳታውን ሳያገኙ ቀርተው ከችግሩ ጋር አብረው እንዳያድጉ በሚል ለማስጠንቀቅ እጽፋለሁ።

=================================================================

=================================================================

## በልጆች ላይ የሚደረግ አካላዊ እንግልት

**ብያኔ፦**

- ለዐይን የሚታይ ጉዳት ወይም ቁስል (ጭረት፣ በስለት የመቆረጥ ምልክቶች፣ የእሳት ቃጠሎ ምልክቶች፣ ስብራቶች፣ ንክሻዎች ወዘተ)
- ልጅ በጽኑ ዐደጋ ለመጎዳት ያለው ዕድል (ሁኔታው ለዐይን ግልጽ የሆኑ ቁስሎች ባይኖሩትም)

**ተፅዕኖዎች፦**

- የአካል ጉዳት፦ እንግልት የሚደርስባቸው ልጆች ከሚከተሉት አንዱን አለያም የተወሰኑት ይደርሱባቸዋል።
  * በስለት የመቆረጥ ምልክቶች፣ ጠባሳዎች፣ የእሳት ቃጠሎ ምልክቶች፣ ስብራቶች።
  * ድብደባ፣ መናጥ፣ መታነቅ፣ ስንበር፣ ጥለዛ፣ ቁንጥጫ፣ ምረዛ፣ በውሃ ደፈቃ።

- እነዚህኞቹ ወዲያውኑ የሕመም፣ የሥቃይ ስሜትና የአጭር ወይም የረዥም ጊዜ የጤና ቀውስ ይፈጥራሉ።
  ለምሳሌ
  * መስማት የመሣን ሁኔታ።
  * በእይታ ላይ የሚደርስ ጉዳት።
  * ነርቭ ነክ ችግሮች።
  * የአእምሮ ወይም የዕድገት ዘገምተኝነት።
  * ውስጣዊ መቁሰሎች።
  * እንዲያም ሲል ለሞት ያደርሳሉ።

- ስሜታዊ ጉዳት፡- አካላዊ እንግልት የሚደርስባቸው ልጆች፣ እንግልቱ ከማይደርስባቸው ልጆች አንጻር አብዛኛውን ጊዜ በሚከተሉት ነገሮች ይሠቃያሉ።

  * ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ያነሰ ይሆናል።
  * የትምህርት ችግሮች።
  * ራስን የመግዛት ችግሮች።
  * የግንኙነት ችግሮች።
  * የአኳኋን ችግሮች፡-ቅዥ ቃዣነት፣ ተተናኳይነት፣ ግልፍተኝነት።
  * የአእምሮ መታወክ፡-ድኅረ ሰቀቀን፣ ድብርት ወይም ፍርሃት።
  * በአደንዛዥ ዕፅና በአልኮል ሱስ የመጠመድ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው።
  * በውስጣቸው ፀረ ኅብረተሰባዊ ስብእናን (ወንጀለኝነትንና ወፈፌነትን) ለማዳበር ቅርብ ናቸው።
  * ራሳቸው አንገላች ወላጆች ይሆናሉ።

- ማኅበረሰባዊ ጉዳት፡- በአካላዊ እንግልት የሚሠቃዩ ልጆች ላይ ወዲያውኑ የሚደርሱ ማኅበረሰባዊ መዘዞች እንደሚከተለው ሊገለጡ ይችላሉ።

  * የማኅበረሰባዊ ጥበብ መጎዳት።
  * በቡድን ውስጥ የመሰናሰል ችግር።
  * ከእኩዮች ጋር ኅብረት የመፍጠር ችሎታ የማጣት ችግር።
  * የአእምሮና የቋንቋ ችሎታ ዝቅተኛነት።
  * በሌሎች ላይ እምነት ማጣት።
  * በሰዎች መካከል ያሉትን ችግሮች በጥቃት ስንዘራ የመፍታት ዝንባሌ።

**በወላጆች አኳኋን ላይ ያሉ ምልክቶች (አባት ወይም እናት)**

- ከልጅ ዐቅም በላይ የሆነን ነገር ከእርሱ መጠበቅ፡- ከእርሱ የሚጠበቁት ነገሮች ከፍተኛ መሆናቸውና ልጁ ባልተሳካለትም ጊዜ የሚኖረው ከፍተኛ ቅሬታ። (የተጎዳን ልጅ እንዳያለቅስ ማዘዝ፣ ትንሽን ልጅ ለረዥም ጊዜ ዝም እንዲል ማዘዝ።)
- ቅጥ ባጣ ሁኔታ ልጅን ወዲያውኑ እንዲታዘዝ እና/ወይም የተባለውን በትክክል እንዲያደርግ ማዘዝ።
- በወላጅ ችግር ልጅን ተጠያቂ ማድረግ።
- በወላጅ ጎጂ ጠባዮች ልጅን ጥፋተኛ ማድረግ።
- ተፈጥሯዊና የተለመዱ በሆኑ አኳኋኖች ላይ አግባብ የሌለው የወላጅ ምላሽ (በሕፃን ለቅሶ መቆጣት)።

- ልጅ በየዋህነት የሚሠራውን ሥራ ሆን ብሎ እንዳደረገው ማሰብ (ሕፃኑ የሚያለቅሰው እኮ እኔን ለመረበሽ ነው ብሎ ማሰብ)።
- ለልጁ የማራቅ ሁኔታን ማሳየት።
- በልጁ ክህሎት ማፌዝ።
- በልጁ ላይ መዛት ወይም ሌላውን (ሰው ወይም እንስሳ) ለመጉዳት መዛት።
- በንብረት ላይ የሚደረግ ጥቃት ስንዘራ፡- ዕቃዎችን ማሽቀንጠር፣ ግድግዳን ወይም የቤት ዕቃዎችን መምታት።
- ልጅ ስለደረሰበት ጉዳት ድብስብስ ያለ ምክንያት መስጠት።
- ያለ ምንም ሌላ  አማራጭ ለልጁ የሚያስፈልገውን ሕክምና ማዘግየት ወይም ደግሞ ሕክምና እንዳያገኝ መቃወም።
- "ብትወደኝ ኖሮማ ይህን ባላደረግህ ነበር" እያሉ የልጅ ስሜት መጠቀሚያ ማድረግ።
- ልጅ ማሳደግን በተመለከተ የሁለተኛውን ወላጅ ምክር አለማድመጥ።

## በልጅ አኳኋን ላይ ያሉ ምልክቶች

- ከጤናማው የዕድገትና የመዳበር ግራፍ መስመር ውጪ መሆን።
- አሁንም አሁንም በሚሆኑ ዐደጋዎች ሮሮ ማሰማት።
- የንክሻ፣ የምት የቃጠሎ የጠባሳ ሙሉ በሙሉ ሆነ በከፊል የዐይን ደም የመልበስ ምልክቶች። (እነዚህ ምልክቶች የሚገኙባቸው ቦታዎች፣ ይዘቶችና ደረጃዎች ጠቃሚነት አላቸው፤ በውኑ ቁስሉ ልጁ ከተናገረው ነገር ሳቢያ የሆነ ነው? የልጁ ዕድሜና የዕድገት ደረጃ ከእንዲህ ዐይነት ቁስል ጋር ግንኙነት አላቸው?)።
- ትልልቅ ሰዎችን መፍራትና ከእነርሱ ወደ ኋላ ማለት።
- የሕፃንን ወይም የሌላን ልጅ ለቅሶ ለመስማት መፍራት።
- ያልሆነን ነገር የማድረግ ፍራቻ፣ የመሳሳት ፍራቻ።
- በተጠንቀቅ መሆን እና/ወይም ሁሌ ክፉ ነገር ይሆናል የሚል ሥጋት።
- ከሌላው ሰው ድንገተኛ እንቅስቃሴ የተነሣ ተሸማቅቆ ጎንበስ ማለት ወይም በመበርገግ መዝለል።
- ከትምህርት ተቋሞች ወይም ከጓደኞች ዘንድ ወደ ቤት ለመመለስ መፍራት።
- ስለ ወላጅ በተጋነነ መልኩ መጨነቅ እና/ወይም የወላጅነት አስተሳሰብ ማሳየት።

- የትልልቅ ሰዎች አኳኋንን ማዳበር (ስለ ሌሎች ልጆች መጨነቅ ስለ እነርሱ ኀላፊነት መውሰድ) ያ ካልሆነ ደግሞ ከዕድሜው በታች የሆኑ ልጆች ባሕሪያትን መውረስ (የሕፃንን አነጋገር፣ ጣትን መጥባት ወዘተ)።
- ድንገትና ቅጥ ያጣ የጠባይ ለውጥ (ከዳተኝነት ወደ ጠበኝነት፣ ከቁጥብነት ወደ ሽቁጥቁጥ ታዛዥነት) ወይም ችሎታ ከመተግበር ረገድ በማርክ ላይ ከፍተኛ የሆነ ንረትና ዝቅጠት ማሳየት)።
- በወላጁ የተቆጣውን ቁጣ ወደ ራሱ ወይም በአካባቢው ወዳሉት ማዞር።
- ራስን ለዐደጋ የመዳረግ ጠባያት፦ ፀጉርን መንጨት፣ ጭንቅላትን መምታት፣ ዐደገኛ ዝላዮች ወዘተ።
- በሌሎች፣ በእንስሳት፣ በንብረት ላይ ጥቃት ስንዘራን ማሳየት (ቁጣን ከወላጅ መቅዳት እና/ወይም ከወላጅ ጋር መመሳሰል)።
- ስሜታዊ ዝግነት።
- የመቀራረብ ሥጋት፣ እምነት ማጣት፣ ከሰዎች ጋር ግንኙነት የመፍጠር ችግር።
- ራስን ዝቅ አድርጎ መገመት እና/ወይም ራስን መጥላት።
- ተስፋ ማጣት፣ የወደፊቱ ሁኔታዎች መጨለም።
- የጥፋት ዝንባሌዎች፦ ሐሳቦች ዛቻዎች ወደ ዐደኛ ሁኔታዎች መድረስ።
- አልኮልና አደንዛዥ ዕፆችን መውሰድ።
- ፀረ ኅብረተሰባዊ ጠባያትና የወንጀለኝነት ዝንባሌ።
- ማኅበረሰብን ፣ የቡድን እንቅስቃሴዎችን የመለመድና በማዕቀፎች ውስጥ የመስተዳደር ችግር።
- ከትልልቅ ሰዎች ጋር የሚሆንን አካላዊ ንክኪ በእጅጉ መሥጋት።
- በወላጆቹ ወይም በሌሎች አዋቂዎች ልጁ ፊት ፍርሃት ያደረበት የመምሰል ሁኔታ።
- የልጁ ወደ ቤት የመሄድ ፍራቻ።
- ለበላዮች ባልተለመደ መልኩ የመታዘዝ ሁኔታ።
- ዐይነ ዐፋር፣ ዝግና ግንኙነት መፍጠር የሚያስቸግረው።
- የቀዥቃዣነት ምልክቶችን ሊያሳይና በመተናኮልም ሊረብሽም ይችላል።
- ልጁ ሲጎዳ ምንም ዐይነት የመጎዳት ስሜት አያሳይም።

=================================================================

## በልጆች ላይ የሚደረግ ጾታዊ እንግልት

**ብያኔ፦**

በቤተሰብ ውስጥ በልጆች ላይ የሚደረግ ጾታዊ እንግልት እዚያው ቤተሰብ ውስጥ ባሉ አዋቂ (ወላጅ፣ አያት፣ አጎት ወዘተ) እና ልጅ መካከል የሚደረግ አካላዊ ወይም አካላዊ ያልሆነን ንክኪን ያካትታል፤ ይህም ልጁ መጠቀሚያ ሲሆንና ወይም ለጾታዊ ውርደት ሲዳረግ ወይም ደግሞ ለአዋቂው ወሲብ የመነሣሻ ምንጭ ሲሆን ነው።

ከእኩያሞች ይልቅ በጎረምሳና በትንሽ ልጅ መካከል የሚደረግ የእንግልት ሁኔታም አለ (ወንድማማቾች፣ የአጎት ልጆች ወዘተ)።

ይህኛው እንግልት ግን ጉልበትን መጠቀም ወይም አካላዊ ሕመምን ማስከተል የሌለበት ነው። አብዛኛውን ጊዜም የሚከናወነው "ከመዋደድ" ግንኙነት ነው፤ አለያም ለልጁ የተሳሳተ "ደስ መሰኘትን" ተላብሶ የጨዋታው ክፍል ሆኖ የሚመጣ ነው።

**የመገለጫ መንገዶቹ፦**

- ልጁ ወሲባዊ ድርጊት ያደርግ ዘንድ መለመን ወይም ይህን መሰሉን ድርጊት እንዲያደርግ በልጁ ላይ ተፅዕኖ ማድረግ።
- በልጁ ፊት ኀፍረተ ሥጋን መግለጥ።
- እያባበሉ ከልጁ ጋር ወሲባዊ ንክኪ ማድረግ።
- የአካል ብልቶችን/ ዕቃዎችን በልጁ ብልቶች ውስጥ ማስገባት።
- ለወሲባዊ እርካታ የሚሆኑና ወደ ውስጥ ሳይገቡ የሚደረጉ ድርጊቶች (ወደ እርካታ ለመድረስ ሲሉ ልጅን ማሻሸት)።
- ልጅን ለወሲባዊ ድርጊት ትይንቶች ማጋለጥ።
- በልጁ አማካይነት የልጆች ወሲባዊ ድርጊቶችን ቀረጻ ማካሄድ።
- ልጁን ለዝሙት መጠቀም።

**ተፅዕኖዎች፦**

**አካላዊ ጉዳት፦** በልጆች ላይ የሚደረግ ጾታዊ እንግልት የሚከተሉትን ሊያመጣ ይችላል።

* በካይ የአባለዘር በሽታዎችን
* የኀፍረተ ሥጋ መቁሰልና መድማት

* በነፍረተ ሥጋ ላይ ጉዳት ማድረስ።
* በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ጊዜም ውስጣዊ ብልቶች ሊጎዱና ነርቭ ነክ ጉዳቶች ሊከተሉ ይችላሉ።

***ሥነ ልቦናዊ ጉዳት፦*** በቤተሰብ ውስጥና ከቤተሰብ ውጪ የሚሆን ወሲባዊ እንግልት የሚከተሉትን ሊያስከትል ይችላል።

*ትካዜ

*የድኅረ ሰቀቀን መረበሽ

*ፍርሃት

*የአመጋገብ ሁኔታ መዛባት

*ለስብእና የሚሰጡት ዋጋ ማነስ

*በፍርሃት የመረበሽና የመለየት ሁኔታ

*አጠቃላይ ሥነ ልቦናዊ ችግር

*አካላዊና ነርቭ ነክ ሁከት

*የአእምሮ ቀውስ

*የጾታዊ ሁነት ችግሮች

*በትምህርት ቤት ውስጥ የመማር ችግር

*የጠባይ ችግሮች (የአደንዛዥ ዕፅና የአልኮል ሱሰኝነት፣ አውዳሚነት፣ የኋላ ኋላም የወንጀለኝነትና ራስን የማጥፋት ዝንባሌ ማሳየት)

*ተዳጋጋሚ ሰለባነት

**በእንግልት አድራሹ ጠባይ ላይ የሚታዩ ምልክቶች:**

- አጠቃላይ የልጆች ፍቅር
- ቅጥ ያጣ የልጅ ተከላካይነት
- ለልጅ መቅናት
- በጥቃት ሰንዛሪውና በልጅ መካከል ያለ ዕድሜን የማይመጥን ቅርርብ (አባት የአስራ ሶስት ዓመት ሴት ልጁን በጉልበቱ ላይ ማስቀመጥን የመሰለ)
- ልጆችን ባካተተ ወሲባዊ ፍላጎት ቀስቃሽ ድርጊቶች መጠመድ
- ከመጠን ያለፈ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ፍላጎት ወይም ከትዳር ጓደኛ ጋር ለሚሆነው የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ደንታ ማጣት

- በሴቶች ወይም በወንዶች ልጆች ላይ ዐይንን መጣል
- በልጅ አካላዊ እይታ ላይ የሚሰጥ አስተያየት (በአብዛኛው አባት ለሴት ልጁ የሚሰጠው ጨዋነት የሌለበት አካላዊና የአለባበስ አስተያየት)

እናቶች በልጆቻቸው ላይ ወሲባዊ እንግልት ቢያደርሱም በዚህ ጉዳይ ያለው ጥናትና ዘገባ ቁጥር አናሳ በመሆኑ አጠቃላይ ከሆኑ ለገዛ ራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ግምትና የሌላውን ስሜት የመካፈል ውስንነት  በቀር የተወሰኑ መለያ ምልክቶች የሉትም።

**በልጁ ጠባይ ላይ የሚታዩ ምልክቶች:**

- አካላዊ እንቅስቃሴን ከማድረግ እና/ወይም ሌሎች ልጆች አጠገብ ልብስን ከመቀየር ወደ ኋላ ማለት
- በቀን ውስጥ የውስጥ ሱሪን ደጋግሞ የመቀያየር ፍላጎት
- ለመሄድም ሆነ ለመቀመጥ መቸገር
- በኀፍረተ ሥጋ አካባቢ የሕመም ስሜት
- የንክሻ ወይም የመሳም ምልክቶች
- ዕድሜን የማይመጥን ወሲባዊ ጠባይ
- ዕድሜን የማይመጥን የወሲባዊ ድርጊቶች ወይም ጉዳዮች ዕውቀት ማሳየት
- ከዕድሜ እኩዮች ጋር የሚኖር ግንኙነት ማነስ ወይም ከእነርሱ መገለል
- አብዝቶ አዋቂዎችን የመቅረብ ፍላጎት
- የጾታዊ ልዩነት መምታታት
- የዕንቅልፍ እጦት/ ድካም
- ቅዠት
- ድንገተኛ የለቅሶ ትንቅንቅ
- የአመጋገብ እክል እና/ወይም የተጋነነ የሰውነት ክብደት ለውጥ
- አጸፋዊ የሆነ ጎጂ ጠባይ - ሌሎች ልጆች ላይ ወሲባዊ ጥቃት ማድረስ
- አጸፋዊ የሰለባነት ጠባይ - ለወሲባዊ ድርጊት መጠቀሚያነት መቀየር
- አጸፋዊ የአማላይነት ጠባይ - ቅርበትን/ተቀባይነትን ለማግኘት ወሲባዊነትን መጠቀም

## በልጆች ላይ የሚደርስ ስሜታዊ እንግልት

**ብያኔ፡-**

ማንኛውም ወላጅ አንዳንዴ የልጆቹን ስሜት ይጎዳል። ነገር ግን እነዚህ ጉዳቶች ሲደጋገሙና ሁኔታውን እያባሱት ሲሄዱ ጉዳቱ የስሜታዊ እንግልትን መልክ ሊይዝ ይችላል።

ስሜታዊ እንግልት የልጅን ሁነኛ ዕድገት አጣማሚ፣ ገቺና አበላሽ ሆኖ የተዘየደ የወላጅ ጠባይ ነው። ይህ ሁኔታ ልጅን ማንነቱን እንዲያጣ አድርጎ አሁንም ይሁን ወደ ፊት ከሰዎች ጋር ለሚኖረው ግንኙነት የመፍጠር ዕድል ስሜታዊም ሆነ ዕውቀታዊ ክንዋኔውን ሊያስተጓጉልበት ይችላል፤ ብሎም ይህ ሁኔታ ስለ ራሱ፣ ስለ ሌላው፣ ስለ አካባቢውና ወደ ፊትም ስለሚሆነው ነገር ያለውን ግንዛቤና ግምትም ሳይቀር የማጣመም ኀይል አለው።

መቼም ቢሆን በአካላዊም ሆነ ወሲባዊ እንግልት ውስጥ ስሜታዊ እንግልት መኖሩ አይቀሬ ነው (ማለትም ልጅ አካላዊም ሆነ ወሲባዊ እንግልት እየደረሰበት ስሜታዊ እንግልት ላይደርስበት ፈጽሞ አይችልምና።)

**የመገለጫ መንገዶችና ተፅዕኖዎች፡-**

- መገፋት፡- ከጎደኞቹ በኩል የሚታዩ የማግለል፣ የመግፋትና የማራቅ ሁኔታዎች በልጁ ዘንድ ተፈላጊነትንና ተቀባይነትን የማጣት ስሜት ያሳድሩበታል። ለምሳሌ ልጅ የቤተሰቡን አብሮ መሆን ሲፈልግ ለእርሱ ግድ ማጣትንና በተደጋጋሚ ጊዜ ያለማግኘት፣ ትኩረት ሊሰጠውና ቅርበት ሊያገኝ ያልተገባው መሆኑን የሚጠቁሙ፣ ሁልጊዜም ከእርሱ ይልቅ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚያስፈልጉ አስስቸኳይና ቀዳሚ ጉዳዮች እንዳሉ የሚያንፀባርቁ አኳኋኖችን የማሳየት ሁኔታዎች።
- ማጣጣልና ማቃለል፡- በዚህን ጊዜ ልጅ ለትችት የተጋለጠ፣ ቅር የሚያሰኙ አሉባልታና መጥፎ ስምም የወጡለት፣ ክብሩም የተገፈፈና በአካባቢውም የሚያውም የአቀራረብ ሁኔታ እርሱ ከሌሎች አንጻር የበታች እንደሆ አድርጎ የሚያስረግጥለት ነው። ማለትም ልጁ መዘባበቻ በመሆን የተለያዩ የውግዘት መጠሪያዎች ወጥተውለታል፣ ሁልጊዜ በስህተቱና እንደ አግባቡ ባልሠራቸው ነገሮች ይመጡበታል ማለት ነው።
- ማስፈራራት፡- ይህ ደግሞ ልጁ በቃላት የሚዛትበትና የሚፈራበት ሁኔታ ነው። እንዲህ ያለው ልጅ የሚኖረው በቤት ውስጥ ባለ የፍራቻ ድባብ ስለሆነ ቤት ለእርሱ ሰላማዊ ቦታ ባለመሆኑ፣ እንዳይተነኮል ያለ አንዳች መዘናጋት የሚጠነቀቅበትና ቀጥሎ የሚመጣውን ትንኮሳ ፈጥኖ ለማወቅ የሚጥርበት ቦታ ነው። የሚኖረውም የወላጆቹ ቁጣ እንዳይቀሰቀስበት እየተሳቀቀ ነው።

- ብቸኝነት፦ ልጁ ከቤተሰብ ውጪ ማኅበረሰባዊ ግንኙነት እንዳይኖረው የሚደረግበት ሁኔታ ነው፤ ከእኩያዎቹ ጋር እንዲገናኝ አይፈቀደልትም፤ ያለ ምንም ኀበረሰባዊ መስተጋብር እንዲህ ባለ ውስን ቦታ ረዘም ላለ ጊዜ ይያዛል። እንዲህ ያለው ጉዳት ልጅ ማኅበረሰባዊ ኑሮ ባጣበት ሁኔታም ሊገለጽ ይችላል፤ በቤት ውስጥ ያለው ድባብ አስፈሪና አስደንጋጭ ነው። (ማለትም ጓደኞቹ እንዳያውቁበት ወይም ደግሞ እንዳይጎዱበት የሚፈልገው እንደ ጩኸትና የጠባይ ችግር የመሳሰሉት ማለት ነው)

- ብልሹነት፦ ይህ ደግሞ ልጁ አጉል በመባል የሚታወቀውን ጓደኝነት ለመመሥረት የሚያልፈው ሂደት ነው፤ በዚህ ጓደኝነት ውስጥ ፀረ ማኅበረሰብ የሆነን አኳኋን ይማራል፣ በሚኖርበት ማኅበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት የሌላቸውን ጉዳዮችና ሁኔታዎችንም ተቀብሎ በእርሱ ዘንድ እንዲያዳብራቸው ያበረታቱታል። ለምሳሌ ያህል ልጅን ለወሲባዊ እና/ ወይም ለጥቃት እና/ ወይም ግብረገባዊነት ለሌላቸው ነገሮች ማጋለጥ)
- መጠቀሚያነት፦ ልጅ ለወላጅ ፍላጎት አካላዊ ወይም የነፍስ እርካታ መጠቀሚያነት የሚውልበት ሁኔታ ነው። ማለትም ወላጅ፣ ልጁ እርሱን ያገለግለው ዘንድ የገዛ ራሱ ፍላጎት ቸል እንዲል ከልጁ ይጠብቀብታል (የወላጁ ችግር እንዲካፈልና እንዲያስተዛዝነው ወዘተ) የሚና ተገላቢጦሽ ሆኖ የወላጅ ኀላፊነት በልጅ ጫንቃ ላይ እስኪወድቅ ድረስ ማለት ነው። ልጅ የወላጅን ፍላጎት እርካታ እንዲያሚላ ከእርሱ መጠበቅ ማለት ነው።
- መባዘን/መማሰን፦ ልጅ ለስሜቱ ትኩረት የማያገኝበት ሁኔታ፣ በስሜታዊ ዕድገቱ መጫጫትና ለስሜቱ ቦታ ያለመስጠት ሁኔታ ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነው ልጅ ተቸግሮ ለሚያሳየው ስሜታዊ ሁኔታም ሆነ ልጅ የገዛ ስሜቱን ቸል ማለት እስኪደርስ ድረስና የገዛ ስሜቱን ቸል ማለት እስኪደርስ ድረስ ለልጅ ስሜት ቦታ ያለመስጠት ነገር ነው። ለእርሱ የሚደረገው ትኩረት ያን ያህል የሆነና አካላዊ ፍላጎቱ ባስመለከተ ብቻ ነው።
- ታአማኒነትንና ተዘውታሪነትን ማጣት፦ ከልጅ መንተያ የሆነንና ወጥነት የሌለው ግዳጅ የሚፈለግበት ሁኔታ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ታአማኒነትንና ዘላቂነትን የሌለው የወላጅ ድጋፍና እንክብካቤ፣ ልጅን ቤተሰባዊ መረጋጋት ማሳጣትና ወላጅ በየቀኑ የሚለዋወጡ ደንቦችን እያወጣ ልጁ ወላጁ ከእርሱ ምን እንደሚፈልግ ለማወቅ ግራ እስኪጋባ ድረስ ያደናግረዋል፤ ብሎም ወላጅ በገባውም ቃል ጸንቶ ካለመገኘቱ ባሻገር፤ ልጁን እየዋሸ የተምታታ መልእክት ያስተላልፍለታል።

**በልጁ ጠባይ ላይ የሚታዩ ምልክቶች፦**

- ሕፃናት፦ የግንኙነት ሂደቶች ይጎዳሉ፣ ተፈጥሯዊ የሆነው የማወቅ ፍላጎታቸው ይጎዳል፣ እንግዳ ሰዎችን መፍራታቸው ይቀርና ሳይለዩ በሌሎች ላይ ጥገኛ መሆን ያመጣሉ። በባሰ ጊዜም አእምሮአዊ ጉዳት ወይም ዕድገታዊ ዘገምተኝነት ይታይባቸዋል።
- ዕድሜው ለትምህርት ቤት ያልበቃ ልጅ፦ የአመጋገብ ችግር፣ የዕንቅልፍ መዛባት፣ ሳይለዩ በማያውቋቸው ሰዎች ላይ ጥገኛ መሆን፣ በጨዋታ ብቃታቸው ላይ ዘገምተኝነት ማሳየት፣ በስሜታዊና ንቃታዊ ዕድገት ልዩነት ማሳየት፣ በስሜት ያለመረጋጋት፣ ድብርት፣ ተተናኳይነትና ራስን መምታት ይታይባቸዋል።
- አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ወጣቶች፦ የበታችነት ስሜት፣ ጭንቀት፣ ተቃራኒነት፣ ቸልተኝነት፣ ቁጡነት፣ መረጃን የማገናዘብና ትኩረት የማድረግ ችግር፣ ሽንፈት፣ በሽንት ማምለጥ የሚገለጽ ስሜታዊ ፀፀት፣ ጣትን የመጥባት ሁኔታና የመሳሰሉት ናቸው። እንዲህ ዐይነቶቹ ልጆች ማኅበረሰባዊ ጥበብ የሌላቸው ሊሆኑና አዎንታዊ አስተያየትን ተቀብለው ለማኅበረሰባዊው ተሞክሮዎችና ውጥረቶች ምላሽ ለመስጠት ይቸገራሉ።
- ወጣቶች፦ ለወላጆቻቸው እንግልት ሰለባነታቸው ካወቁ በኋላ ሁለት ዐይነት ምላሽ ያሳያሉ። 1.ዝግነት፦ የድብርት ምልክቶችን፣ የሥቃይና ራስን የማጥፋት ዝንባሌዎችን ማሳየት፣ አካላዊ እክሎች ማሳየት (ለምሳሌ የምግብ ፍላጎት መስተጓጎል) ከዓለምና ከቤተሰብ ተነጥሎ የመገለል ዝንባሌ። 2.ዐመጸኝነት፦ በትምህርት ገበታ ላይ አለመገኘት፣ ከቤት መሸሽ፣ ሕግን የመጣስ ድርጊቶች ማድረግ፣ ሱሰኝነትን በሚያመጡ ነገሮች መጠቀም የመሳሰሉት ናቸው።

**የወላጆች መለያ ጠባዮች፦**

ስሜታዊ እንግልት የሚያደርሱቱ ወላጆች ለልጅ አስፈላጊ የሆነውን ማንኛውም አካላዊና ትምህርት ነክ ነገሮች ማሟላት የሚችሉ አስተማማኝ ገቢ ያላቸውና የተማሩ ሊሆኑ ይችላሉ ሆኖም ለልጅ ያላቸው ስሜታዊ ትኩረት ደግሞ በጣም ብልሹ ይሆናል።

በስሜታዊ እንግልት እና በወላጆችም ይሁን በቤተሰብ መካከል እንደሚከተሉት ዐይነት የሆኑ ግንኙነቶች አሉ፦

- የአንዱ ወይም የሁለቱም ወላጆች የአእምሮ መታወክ (ድብርትን ጨምሮ)
- የአንዱ ወይም የሁለቱም ወላጆች የስብእና መታወክ
- የትዳር ችግሮች
- የግንኙነት ችግሮች
- የውጥረት ሁኔታዎችን የመቋቋም ችሎታ ዝቅተኛነት
- በሰዎች መካከል ላሉ ችግሮች መፍትሔ የማግኘት ችሎታ አናሳነት
- ዘወተር ተቆጣጣሪነትን መፈለግ
- ያለ ምንም ማንገራረግ መታዘዝን የሚጠይቁ፥ አክራሪነትና ግትርትርነት ያላቸው የአስተዳደግ ዐቋም የያዙ ወላጆች

## ቸል ማለት

**ብያኔ፡-**

ቸል ማለት፡- ባለማሰለስ ልጅ የሚስፈልገውን ነገር መንፈግ ወይም ከመስጠት ማቋረጥ ማለት ነው፤ ለምሳሌ የሕክምና ርዳታ፣ በሽታን የመከላከል ሁኔታ፣ ትምህርትና በአካባቢ የሚያጓጉ ነገሮችን ለልጅ ከመስጠት ማቋረጥ ማለት ነው።

**የመገለጫ መንገዶች፡-**

- አካላዊ ፍላጎቶችን ቸል ማለት፡- መሠረታዊ ለሆኑ የልጅ ፍላጎቶች ግድ ማጣት (ምግብ፣ ተስማሚ ልብሶች) ወይም ደግሞ በቤት ውስጥ ከተገጠሙና ልጅን ሊጎዱ ከሚችሉ ነገሮች አለመጠንቀቅ።
- ለብቻ መተውና ያለጥበቃ ማስቀረት፡- ልጅን መተውና ያለ ተገቢ ጥበቃ ትቶ መሄድ (ሕፃን ልጅን ለአራት ዓመት ልጅ በዐደራ ትቶ መሄድ) የጠፋን ወይም የሸሸን ልጅ አለመፈለግ።
- ከሕክምና ረገድ ቸልተኝነት፡- ልጅ የሚያስፈልገውን አእምሯዊ እንክብካቤ ወይም አካላዊ ሕክምናን መንፈግ ለምሳሌ አለማስከተብ፣ መረጃ መሣሪያዎችን (መነጽር፣ የመስሚያ መሣሪያዎችን ወዘተ) መንፈግ፣ በታመመ ጊዜ ወደ ሕክምና አለመውሰድና የመሳሰሉት ናቸው። በአደንዛዥ ዕፅ የመጠቀምን ሁኔታ ማጽደቅና እንዲጠቀሙ ማባበልም ደግሞ ሕክምናዊ ቸልተኝነት ተደርጎ ነው የሚወሰደው።
- ትምህርት ነክ ቸልተኝነት፡- ልጅ የትምህርት ዕድል እንዲያገኝ፣ ሐሳቡን ወደሚያነቃቁ ሁኔታዎች የመውጣት ዕድል እንዲገናኝ ለማድረግ ግድ ማጣት፣ ከትምህርት ማዕቀፍ መጉደሉንም ከምንም አለመቁጠርና ወዘተ።
- ስሜታዊ ቸልተኝነት፡- ፍቅር መንሣት፣ አለመዳሰስ፣ ስሜታዊ ምላሽና አዎንታዊ ቀረቤታ አለመስጠት።

**ሊታወስ የሚገባው፡-**

እነዚህን የመሳሰሉ አጠራጣሪ ምልክቶች እያሉም እንኳን አንዳንዴ የሚያሳስቱና የሚያመለክቱትም ቸልተኝነትን ሳይሆን ይልቁንም የተወሰነን ችግር ይሆናል።

- ድህነትን፡- ከድሃ ቤተሰብ የሆኑ ልጆች በቸልተኝነት የሚሠቃዩ መስለው ሊታዩ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ በደንብ ሲስተዋሉ ግን ልብሳቸው ያረጀ ይሁን እንጂ ንጹሆች፣ ደስተኞችና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ጤናማ ግንኙነት ያላቸው ናቸው።

- አለማወቅ፡- ዐደጋዎችና የጤና ችግሮች በወላጅ ቸል ሳይልም አንዳንዴ እንደውም ገለጻ ብቻ ከሚያስፈልገው ስለ ሕክምና ዕውቀት ማጣት የተነሣ ሊመጡ ይችላሉ።
- ጊዜያዊ ቀውስ፡- (ከሥራ በመሰናበት፣ ከፍቺ፣ ከስደት የተነሣ) ወላጆቻቸው በጊዜያዊ ችግር ውስጥ የሚገኙ ልጆች ለተወሰነ ጊዜ ቸል ሊባሉ ይችላሉ፤ ይህን ግን ወላጆችን ስላሉበት ሁኔታ ግንዛቤ በማጨበጥ መፍታት ይቻላል።

**ተፅዕኖዎች፡-**

- አካልን ባስመለከተ፡- በቸልተኝነት የሚሠቃዩ ልጆች መጫጫት (የሚገኙበትን ዕድሜ ወደሚመጥን ቁመትና ክብደት አለመድረስ እየተባለ የሚታወቀው ሕክምናዊ ሁኔታ) ሊታይባቸው ይችላል። ሁኔታው ሲብስ ደግሞ ከፍተኛ የሆነን የዕድገት ጉዳት ሊያስከትል ይችላል።
- አእምሮን ባስመለከተ፡- በቸልተኝነት የሚሠቃዩ ሕፃናት ከዐዋቂዎች ጋር ግንኙነት የመፍጠር ችግር አዝማሚያ ይታይባቸዋል፤ በቀጣይም እነዚህ ልጆች የፈጠራና የምርምር ችሎታ ሊሳናቸው ይችላል። በኋላም ዕድሜያቸው ሲጨምር ቸልተኝነቱ የጥፋተኝነትን ስሜት ይፈጥርና የበታቸኝነት ስሜት፣ ዳተኝነት፣ ማኅበራዊ ግንኙነት የመፍጠር ችግር፣ የትምህርት ፍላጎት እጦት ያስከትላል።

**የወላጆች ጠባዮች፡-**

ቸል በማለትና በቤተሰባዊ መዋቅር ማለትም በቤተሰቡ ውስጥ በሚካሄዱት ጉዳዮች መካከል ተያያዥነት አለ። አስቸጋሪ ድህነትን፣ በሽታዎችን፣ የትዳር ችግሮችንና የመሳሰሉትን የሚታገሉ ቤተሰቦች ለልጃቸው ተገቢውን እንክብካቤ የማድረጊያ ግብዐቶችን ለማግኘት ይቸገራሉ። በሌላ አንጻር ደግሞ በግል ስኬታቸው የተዋጡና /ወይም በየጉባኤዎቻቸው በሚሰጡት አገልግሎት የተጠመዱ ወላጆች ለልጆቻቸው በክንዋኔዎቻቸው ቁሳዊውን ፍላጎት ሊያረኩላቸውና ትምህርትን ወይም ስሜትን በተመለከተ ግን ቸል ሊሏቸው ይችላሉ።

**በልጅ ላይ የሚታዩ ምልክቶች፡-**

- በዕድገትና በብስለት መስተጓጎል
- ባስፈላጊው ወቅት የእንክብካቤ /የሕክምና/ የመድሃኒት እጦት
- በመኖሪያ አካባቢ ከዐደጋ ጥንቃቄ ጉድለት
- የገላ ንጽህና ጉድለት፡- የሚረብሽ የገላ ጠረን፣ ያልታጠበ ፀጉር፣ ያልተፋቀ ጥርስ
- ለወቅቱና/ወይም ለዕድሜ የማይስማማ አለባበስ

- ምግብ፦ ወደ ትምህርት ቤት ምግብ አለማምጣት፣ የአመጋገብ እጥረት፣ የረሃብ አቤቱታ መኖር
- በቋሚነት ትምህርት ቤት አለመምጣትና አብዝቶ መቅረት
- ዘዋሪነትና ጥበቃ ማጣት
- አብዛኛውን ጊዜ ነገርን በሆድ መያዝና ዝግ መሆን
- አብዛኛውን ጊዜ ከኅብረተሰብ የተገለሉ ናቸው፤ በሃሜት ይሠቃያሉ።

---

---

## ልጆችን ሥርዐት ለማስያዝ የሚደረግ አካላዊ ቅጣት

ቀደም ብለን እንዳየነው ማንኛው ሰው ላይ ጥቃት መሰንዘር ክልክል እንደሆነ ሁሉ እንዲሁ ልጆችም ላይ ጥቃት ማድረስ ክልክል ነው። ታዲያ አካላዊ ቅጣትን ባስመለከተስ ምን ይሁን?

በመጀመሪያ ነገር በሥርዐት ማስያዣ ዘዴዎችና በሥርዐት መመሪያዎች መካከል ልዩነት ያለ ሲሆን፤ ቅዱሳት መጻሕፍት ጠቃሚ በሆኑት የሥርዐት መመሪያዎች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ እንጂ ወደ ተወሰኑት የሥርዐት ማስያዣ ዘዴዎች አይወግኑም። የሥርዐት መመሪያዎች ለሥርዐት ማስያዣ ዘዴዎች ሁሉ ጠቃሚ መሠረቶች ናቸው። የሥርዐት ማስያዣ ዘዴ፥ የሥርዐት መመሪያዎችን የምንተገብርበት ሁኔታ ነው። ልጆች ስለሚቀጡት አካላዊ ቅጣት የተጠቀሱ ጥቅሶች የሚገኙት በመጽሐፈ ምሳሌ ነው። እነዚህ ጥቅሶች የሥርዐት ማስያዣ ዘዴዎችን ወይም የሥርዐት መመሪያዎችን የሚያስተምሩ መሆናቸውን ለመረዳት ደግሞ መጽሐፈ ምሳሌ ማወቅ ያስፈልጋል። የዚህ መጽሐፍ ዐላማ አንባቢውን የሁነኛ ግብረገብ ጥበብን ማሳወቅና ማስተማር ነው። ይህም የሚሆነው ምሳሌ እየተባለ በሚጠራ ጹሑፍ፥ ጠቅለል ባለ ሁኔታም ሆነ በቅኔያዊ መልኩ በሚነገሩ ወጋዊ አባባሎችና ተረቶች አማካይነት ነው። ምሳሌ ሰውን፣ ሕይወት ያለውን ነገርና ዕፅዋትን አስመልክቶ ዘይቤያዊ በሆነ አነጋገሮች ትምህርታዊ መልእክትን በተጋነነ መልኩ ማስተላለፊያነት የሚጠቅም ነው።

ለምሳሌ ያህል በምሳ23 ከ 1-3 ያሉት ቁጥሮች ከመኳንን ጣፋጭ መብልና ከሐሰት እንጀራ ይልቅ ሰው በጉሮሮው ላይ ካራ ማድረግ እንዳለበት ያስተምረናል።

“ከመኰንን ጋር ለመብላት በተቀመጥህ ጊዜ፥ በፊትህ ያለውን በደኅና አስተውል፤ ሰውነትህም ቢሳሳ፥ በጕሮሮህ ላይ ካራ አድርግ። ጣፋጩ መብል አይመርህ የሐሰት እንጀራ ነውና።”

በእርግጥም ቃል በቃል እንደተነገረው በጕሮሮዋችን ላይ ካራ ማድረግ የለብንም በቃለ አጋኖው ለማለት የተፈለገው ግን ወደ አፋችን ስለሚገባው ነገር መጠንቀቅ እንደሚኖርብንና ለምርኮነት እንዳይዳርገን መጠንቀቅ እንደሚገባን ነው።

እንዲሁም በምሳ 26 ቁጥር 3 ላይ "አለንጋ ለፈረስ፥ ልጓም ለአህያ፥ በትርም ለሰነፍ ጀርባ ነው" ይላል። መቼም ጥቅሱ ሰነፎችን በበትር ምቱ እያለን አይደለም የሚያስተምረን ይልቁን በፈሊጣዊ አነጋገርና በቃለ አጋኖ አለንጋ ፈረስን ፈጥኖ እንዲሮጥ እንደሚያደርገውና ልጓም አህያን ወደ ትክክለኛ አቅጣጫ ለመምሪያ እንደሚጠቅም እንዲሁ ሰነፎችን እያነሣሣን ወደ ትክክለኛው መንገድ መምራት እንዳለብን ነው። በትር ለመምቻነት ሳይሆን ሥልጣንን ለማመልከቻነት እንደሚያስፈልግ ማለት ነው።

በተለያዩ የመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፎች ውስጥ ልጅ አስተዳደግን ባስመለከተ የተጠቀሱ አራት ጥቅሶች አሉ።

- በበትር ከመምታት የሚራራ ሰው ልጁን ይጠላል፤ ልጁን የሚወድድ ግን ተግቶ ይገሥጸዋል።
- ስንፍና በሕፃን ልብ ታስሮአል፤ የተግሣጽ በትር ግን ከእርሱ ያርቃታል።
- ሕፃንን ከመቅጣት ቸል አትበል፥ በበትር ብትመታው አይሞትምና። በበትር ትመታዋለህ፥ ነፍሱንም ትታደጋለህ።
- በትርና ተግሣጽ ጥበብን ይሰጣሉ፤ ያልተቀጣ ብላቴና ግን እናቱን ያሳፍራል።

ለነገሩ እነዚህ ጥቅሶች ልጅን ሥርዐት ለማስያዝ ሲባል መምታትን ይደግፋሉ ብሎ መደምደም ይቻላል። አብዛኞቹ የክርስቲያን፣ የመሲሐዊና የአይሁዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ተንታኞች እነዚህን ጥቅሶች እንዳሉ ስለሚተረጉሟቸው፤ ልጅን ሥርዐት ለማስያዝ አካላዊ ቅጣት ተገቢ ነው ወደሚለው ይወግናሉ።
ከዚህ ጋር አብሮ ሊታይ የሚገባው ነገር ግን በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ያለው ቃለ አጋኖ፣ ልክ ቀደም ሲል ሰነፍን ባስመለከተ እንዳየነው ጥቅስ በትር ወይም የተግሣጽ በትር የሚያመለክቱት የግድ በኀይል ያልሆነ ሥልጣንን መጠቀምና ሕግን ማስከበር ነው። ለምሳሌ አባት ልጁን እንደማይጠላ ግልጽ ሆኖ ሳለ በቃለ አጋኖ ግን አባት ልጁን ያለመቅጣቱን ሁኔታ ልጁን መጥላቱ እንደሆነ ተደርጎ ሆኖ ተጠቅሷል። እንዲሁም ደግሞ ስንፍና በመንፈሳዊ/ በስሜታዊ ሁኔታ እንጂ በውን እንደሚሆነው የመታሰር ዐይነት ከልብ ጋር የታሰረ አይደለም። ሌላው ደግሞ "በትር" ነፍስን በእውነት ከሲኦል አያስጥላትም ምክንያቱም በትር በራሱ ጥበብ ሰጪ አይደለምና።
በዚህ መሠረት ጥቅሶቹ የግድ ልጅን ሥርዐት ለማስያዝ በሚል አካላዊ ቅጣትን አያበረታቱም ይልቁንም ተሰሚነት ያለውን የልጅ አስተዳደግና ገደብ የማድረግን ዋናነት ያበረታታሉ እንጂ። ጥቅሶቹ በበትር ስለመምታት ሲናገሩ፥ የሚናገሩት ብላቴናን ስለመምታት ነው። በብሉይ ኪዳን ደግሞ ብላቴና ማለት ሕፃን ትንሽ ልጅ፣ ወጣትና ለዐቅመ አዳም ያልደረሰ፣ አገልጋይና ባሪያ፣ ወታደርም ማለት ነው። በመጽሐፈ ምሳሌ ብላቴና የሚለው ቃል በተጠቀሰበት ቦታ ሁሉ ለማለት የተፈለገው ወጣትና ለዐቅመ አዳም ያልደረሰን ሰው ነው።

ይሁን እንጂ አስተዋይ የሆነ ሰው ማለት ነው። ሰው አስተዋይ ከሆነ ደግሞ እርሱን ሥርዐት ለማስተማር በትር መጠቀሙ ተገቢ አይደለም። “መቶ ግርፋት በሰነፍ ጠልቆ ከሚገባ ይልቅ ተግሣጽ በአስተዋይ ሰው ጠልቆ ወደ ልቡ ይገባል” ምሳ17፥10

ይኸኛውም ጥቅስ በአጋኖ የተነገረ ነው አስተዋይ ሰውን ያለ አካላዊ ቅጣት አስፈላጊነት ሥርዐት ማስተማር መቻሉን መማር ይቻላል። ሰው ሰነፍ ቢሆንም እንኳን መቶ ግርፋት ምንም አይፈይድም። ነገሩን ልጁ አስተዋይ ነው ወይስ ሰነፍ በሚለው በልጁ ሁኔታ ላይ የሚወሰን ይመስላል። ይሁን እንጂ በአብዛኛው ሁኔታ ልጅ አስተዋይ እንዲሆን አለያም ሰንፎ እንዲቀር የማድረግ ነገር የወላጅ ኀላፊነት ነው።

ይኸን የወላጅ ኀላፊነት ደግሞ ከመጽሐፈ ምሳሌ መማር ይቻላል፦“በብልሃተኛ ከንፈር ጥበብ ትገኛለች፤ በትር ግን አእምሮ ለጐደለው ሰው ጀርባ ነው።” ምሳ10፥13 በብልሃተኛ ሰው ከንፈር ጥበብ ትገኛለች፤ አእምሮ ለጐደለው ሰው ግን በትር ይገኛል ይህም ማለት አእምሮ የጐደለው ሰው ማስረዳትና ማስተማር ስለማያውቅ በበትር ይጠቀማል ማለት ነው።

ልጅን ሥርዐት ለማስተማር ሲባል የሚደረግን አካላዊ ቅጣት ቅዱሳት መጻሕፍት በእርግጥ አይከለክሉ እንጂ የግድ መሆን ያለበት ነገርና ልጆችን በሥርዐቱ ለማሳደግ ደግሞ ብቸኛ መንገድ ወይም በጎ አማራጭ አይደለም። ቃለ አጋኖን በመጠቀም በመጽሐፈ ምሳሌ የተጠቀሱ ጥቅሶች ልጆችና ወጣቶች ግብረገብ፣ ተግሣጽ ብሎም ቆም እንዲሉ ገደብ የሚያደርግላቸው ወይም የሚገራ ነገር ግን የሚጠቅም የበላይ መሪ እንደሚያስፈልጋቸው የሚያስተምሩ ናቸው።

እነዚህ ጥቅሶች የተጻፉት እግዚአብሔር ለወላጆች የሰጠው ተፈጥሯዊ ዝንባሌ ርኅራኄ በመሆኑ ይመስላል፤ ይሁን እንጂ ገደብና ተግሣጽ ደግሞ ለልጆች መርዳታቸውንና የዕውነተኛ ፍቅር መገለጫነታቸውንም ይገልጻሉ።

ለልጅ አስተዳደግ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ከሚከተሉት ጥቅሶች መማር ይቻላል።

- ክብር፦ ልጆችን አባትና እናትን ያከብሩ ዘንድ ማስተማር። “አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም።” ዘፀ20፥12
- ትምህርት፦የእግዚአብሔርን ትእዛዛትና ድንቅ ሥራዎችን ለልጆች ማስተማር። እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው፥ በቤትህም ስትቀመጥ፥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሣም ተጫወተው። ዘዳ4፣9፤ዘፀ 12፥26-27፣ዘዳ6፥6-7፣20-21
- “እኔ ዛሬ እንደማደርግ ሕያዋን እነርሱ ያመሰግኑሃል፤ አባት ለልጆች እውነትህን ያስታውቃል።”
- ምሪትና ገደብ፦ ልጆች በክፉ መንገድ እንዳይሄዱ መከልከልና ከክፉ ልማድ እንዲርቁ ማድረግ። “በዚያም ቀን በቤቱ ላይ የተናገርሁትን ሁሉ በዔሊ አወርዳለሁ፤ እኔም ጀምሬ እፈጽምበታለሁ። ልጆቹ የእርግማን ነገር እንዳደረጉ አውቆ አልከለከላቸውምና ስለ ኃጢአቱ በቤቱ ለዘላለም እንድፈርድ አስታውቄዋለሁ።” ሳሙ3፥12-13

- አቅጣጫ፦ ልጆች በቀና መንገድ ይሄዱ ዘንድ መምራት። "በኃያል እጅ እንዳለ ፍላጻች፥ የጐልማስነት ልጆች እንዲሁ ናቸው።" መዝ127፥4
- መንገድ ማሳየት፦ልጅን በመንገዱ መምራት። "ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።" ምሳ22፥6
- ፈቃድንና ነጻ ምርጫን ማወቅ፦ "ሕፃናትን ተዉአቸው፥ ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው፤ መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉ ናትና አለ።" ማቴ19፥14
- አዘኔታ የተመላን መሆንና ግትር አለመሆን፦ ለልጆች በመራራትና ውስንነታቸውንም በመረዳት ቅስማቸውን አለመስበር። "ልጆች ሆይ፥ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፥ ይህ የሚገባ ነውና። መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር፤ እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት። እናንተም አባቶች ሆይ፥ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጡአቸው።" ኤፌ6፥1-4

---

---

## መሲሐዊው ኅብረት ለልጆች አስተዳደግ ያለው አመለካከት

በመሲሐውያን ዘንድ አንዳንዴ የልጆች አስተዳደግ መመሪያዎች ከሌሎቹ መመሪያዎች ይልቅ ጠንከር ያለ ትኩረት ያገኛሉ፤ ለምሳሌ ያህል "መታዘዝን" በተመለከተ ልጅ ወላጆቹ ያዘዙትን ያለ ምንም ተቃውሞ ወዲያውኑ መፈጸም አለበት። ይህ ሲሆን ግን ይህ የአስተዳደግ መመሪያ ከተጨማሪ የአስተዳደግ መመሪያ ጋር ሚዛኑን ባልጠበቀ መልክ ነው።

የልጆች አስተዳደግ ማሚያ ለሆኑት መመሪያዎች ትኩረት ሳይሰጥ ቅጣትን (በአብዛኛው መቀመጫን መምታት) ያካተተ የአስተዳደግ ዘዴ ላይ ማተኮሩ አብዛኛውን ጊዜ ጥቃትና /ወይም እንግልት የተላበሰ የአስተዳደግ ዘዴን ሊያበረታታ ይችላል።

ስለዚህ ሥነ ሥርዐትን ለማስከበር ለወላጆች የተለያዩ ዘዴዎችን ማስተማሩ በጣም ይጠቅማል፤ ብሎም "ከመታዘዝ" መመሪያዎች አስተዳደግ ባላነሰ ጠቃሚነት ባላቸው በአስተዳደጉ ማሚያ መመሪያዎችም ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል።

### በእስራኤል ያለው የሕግ ሁኔታ፦ ልጆች በሥርዐት ለማሳደግ አካላዊ ቅጣትን የመጠቀም ክልከላ።

- በ 50 ዓመት መጀመሪያ ላይ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ወላጆች ልጆቻቸውን ሥርዐት ለማስያዝና ለማስተማር ሲሉ አካላዊ ቅጣትን የመጠቀም መብት እንዳላቸው ደንግጓል።

- በ 2000 ዓ.ም የካቲት ወር ላይ ከፍተኛው ፍርድ ቤት፤ ወላጅ በቅንነት ልጁን ሥርዐት የማስያዝ መብትና ግዴታ እንዳለው ቢያስብም እንኳን፣ በልጆች ላይ የሚያደርገው አካላዊ ቅጣት በምንም መልኩ ውድቅ ነው ሲል ደነገገ። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ የምንኖረው ጥቃት ሰንዛሪ በሆነ ኅብረተሰብ ውስጥ በመሆኑ ነው። “ቀላል” ጥቃትን የመፍቀዱ ሁኔታ ወደ ከፋ ጥቃት ስንዘራ ያሸቆለቁላልና፤ እንደ ማኅበረሰብ ለአካላዊ ቅጣት የይለፍ መብራት ማብራትም ሆነ ይህን ሁኔታ ወላጅ ሁሉ እንደፈቀደው እንዲረዳው ማድረግ ክልክል ነው።

- ማንኛውም አካላዊ ቅጣት ወይም ቅጣት ድብደባ ያለበት ሥርዐት የማስያዝ ዘዴ ሁሉ (መቀመጫን መምታትምን ጨምሮ/Spanking) በሕግ የተከለከለ ነው።

- ሥርዐት ለማስያዝና ለማስተማር ሲሉ አንድ ጊዜ ብቻ በልጆቻቸው ላይ በጉልበት የሚጠቀሙ ወላጆችን በተመለከተ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ያሉ ማጣሪያዎች አሉ። እርሱም ለፍርድ ማቆምን ባስመለከተ የሕግ አስከባሪ አካላት ወይም ከጉዳዩ ሕዝብ ተኮር ካለመሆኑ የተነሣ ፋይልን ለማስዘጋት የሚወስዱት ግምት ነው፤ እንደየድርጊቱም ተጨባጭ ሁኔታ፣ መንስኤ፣ ውጤቶቹና ሕዝባዊ ፋይዳ አንጻር ምንም አንኳን ድርጊቱ በመሠረቱ ወንጀል ቢሆንም ከአጠቃላይ ውንጀላ ነጻ ሊያደርጉትም ይችላሉ።

**የቅጣቱ ምሳሌዎች፡-**

- በቀበቶ መቀመጫን የተወሰኑ ግርፎችን መግረፍ። ቅጣቱ፡- የ 9 ወር እስራት + 5000 ሽቁል ክፍያ + 150 ሰዓቶች ያህል ሕዝብ ነክ አገልግሎቶችን መስጠት ነው።
- የልጁ ልጅ የሄደበትን ሳያሳውቀው በመጥፋቱ፣ ከመጨነቁ የተነሣ አንድ ጊዜ ብቻ የሆነ የአያት የልጅ ልጁን መምታት ሁኔታ ቅጣቱ፡-100 ሰዓቶች ያህል ሕዝብ ነክ አገልግሎቶችን መስጠት ነው።

የፈለገውን ዐይነት የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ቢሆንም በድብደባ አማካይነት ሥርዐት ማስተማር በአገሪቱ ሕግጋት መሠረት ክልክል ነው። ሥልጣናትን እናከብር ዘንድ የተጠራነው ለዚህም ጭምር ነው። ስለሆነም የሚሻለውም ማኅበረ ምእመናን ወላጆችን አካላዊ ቅጣት የሌለበት አስተዳደግና ሥነ ሥርዐት ማስያዣን መንገድ እንዲያዳብሩ ቢያበረታቱ ነው።

## መንፈሳዊ እንግልት በቤተሰብ ውስጥ

መሲሐዊው ሕይወት መንፈሳዊ ገጽታን ያካተተ እስከሆነ ድረስ በመንፈሳዊው ዘርፍ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚሆነውን ጥቃትና እንግልት በአንክሮ መመልከቱ ጠቃሚ ነው።

መንፈሳዊ እንግልትን ለመለየት አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም ትክክለኛ የሆነ የመሲሐዊ ቤተሰብ ኑሮ ገጽታ ስለሚኖረውና ከውጪ ሲታይ ደግሞ እጅግ መልካም በመሆኑ ነው። ሚስት ባሏን ታሞግሳለች ባልም በተገባቢጦሹ እንዲሁ ያደርጋል፤ ልጆችም ደግሞ ጨዋዎችና ታዛዦች ይሆናሉና። የቤተሳባዊውን መሲሐዊ መልክ ለመጠበቅ ሲባል ተቀባይነት ባላቸው ከፍተኛ የአስተሳሰብ ልኮችና የአኳኋን ግዴታዎችን ለመወጣት እንጂ ሙገሳዎቹና መታዘዞቹስ ከመረዳት ወይም ከፍቅር የመነጩ አይደሉም። በማቴ 23፥5፣28

"ለሰውም እንዲታዩ ሥራቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፤...እንዲሁ እናንተ ደግሞ በውጭ ለሰው እንደ ጻድቃን ትታያላችሁ፥ በውስጣችሁ ግን ግብዝነትና ዓመፀኝነት ሞልቶባችኋል።"

መንፈሳዊ እንግልት የሚያደርስ ሰውም ከውጪ ሲታይ እንዲሁ ነው፤ ምክንያቱም የሚያደርገውን በመረዳት ስለማያደርገው ኀጢአተኛና ምህረት የሚያስፈልገው ነው። መነገር የተገባውን መሲሐዊ ነገር ይናገራል፤ መደረግ የሚገባውንም መሲሐዊ ነገር ያደርጋል። በልቡ ግን ቅዱሳት መጻሕፍትን በቤተሰቡ ላይ ለመሰልጠኛነት ይጠቀምበታል።

ሁሌም ቢሆን ወዲያውኑ የሚሆን ታዛዥነትን ይሻል እርሱን ባልታዘዙትበት ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ካለ መታዘዝጋር ያያይዘዋል። ባልሆነለት ጊዜ ከባድ የሆነን የጥፋተኝነትን ስሜት ይቀሰቅሳል፤ በተሳካለትም ጊዜ  ቅጥ ባጣ ኩራት ይበረታታል።

እርሱን ቅር ላለማሰኘት የሚል ፍራቻን፣ የመሳሳት ፍራቻ፣ የዓለም ፍራቻ፣ የገሃነም ፍራቻ በቤተሰቡ ላይ ያሳድራል። በቤተሰቡ ስለሚያደርገው ስለ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ የመወሰንን መብት ለገዛ ራሱ ይወስዳል። ስለ ማንኛውም ድርጊት ውሳኔ ፍላጎት ዕቅድ ልብስ መረጃ ወዘተ እርሱ ተቆጣጣሪ ይሆናል። በመብቱ ላይ ይግባኝ እንዲጠየቅበት አይፈቅድም።

ለጥያቄም ይሁን ለውይይት ቦታ አይሰጥም። ጥቂት ለየት ያለ የአስተሳሰብ መንገድንና እምነትንም አይፈቅድም። ጥቂት ለየት ያለ አስተሳሰብ ያለው ከቀናው መንገድ የሳተ፣ የወጣ፣ መንፈሳዊ ያልሆነ፣ ቅዱስ ያይደለ፣ ንጹሕና የመሳሰሉትን ያልሆነ ነው።

መንፈሳዊ እንግልት የሚያደርስ ሰው አብዛኛውን ጊዜ በተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያዎች ላይ አለያም በተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ትኩረቱን በማድረግ ሌሎቹ መመሪያዎችንና ዘዴዎችን ሚዛናዊነት ባጣ መልኩ ቸል ይላቸዋል። እነዚህን አጽንኦቶች በመጠቀም፥ እነዚህን ከማይጠቀሙት ራሱንና ቤተሰቡን ለመለየት ይጠቀምበታል። እንዲህም እኛና እነርሱ የሚል ስሜትን በመፍጠር በዚህ መለኪያ የማይኖሩትን ይተችበታል።

የዚህ እንግልት መዘዞችም ከባዶች ናቸው ምክንያቱም በቀጥታ የእግዚአብሔርን ቃል ያጣምሙና ተጎጂው ስለ እግዚአብሔር ያለውን ግንዛቤ ያበላሹበታል፤ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታም ላይ ጥርጣሬ በመዝራት የክርስቶስን ወንጌል ያስታሉ። ይህ ነገር ደግሞ በራሱ ክፉ ነው። በገላትያ 1፥7-9 እንዲ ተብሎ እንደ ተጻፈው፦

> "እርሱ ግን ሌላ ወንጌል አይደለም፤ የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ እንጂ። ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፥ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።"

እንዲህ ላለው እንግልት ሰለባ የሆነው ሰው የሚያንገላታውን ሰው ከሞላ ጎደል የእግዚአብሔር እኩያ ነው ብሎ ያስባል። ይህ ማለት ደግሞ ይኸው ሰው ቅር ቢያሰኘው ወይም አንዳችን ክፉ ነገር ቢለው እግዚአብሔርንም እንዲሁ እንደሆነ አድርጎ ይወስደዋል። ይህ ሐቅ ተጎጂው እንግልት እየደረሰበት መሆኑን ለመረዳትና አቤቱታ በማሰማት ይህን የሐሳብ ኬላ ለመጣስ በጣም ያስቸግረዋል። ስለሆነም እንዲህ ያሉትን ሁኔታዎች ፈልጎ በማግኘት እንክብካቤ ለማድረግ የተለየ ስሜት ስስነት ያስፈልጋል።

# ተጨማሪ የጥቃት ዐይነቶች በቤተሰብ ውስጥ

## በወንድማማቾች መካከል ያለ ጥቃት ስንዘራ

ቅዱሳት መጻሕፍት በወንድማማቾች መካከል ያለን ጥቃት ስንዘራ ይገልጻሉ። (በአቤልና በቃየል፣ በዮሴፍና በወንድሞቹ፣ በአምኖንና ትዕማር፣ በአቤሴሎምና በአምኖን ወዘተ መካከል)

ለምሳሌ በዮሴፍና በወንድሞቹ መካከል በነበረው ግጭት ሳቢያ ከፍተኛ የሆነ ቀውስ መኖሩን ተገልጿል (ዘፍ37፥4-11)። ያዕቆብ ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ ዮሴፍን አስበልጦ ወደደው፣ ስለዚህም በሰላም ማነጋገር እስኪሳናቸው ድረስ ወንድሞቹ ዮሴፍን ጠሉት። እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈው "በሰላም ይናገሩትም ዘንድ አልቻሉም።"

የግንኙነቱ መስተጓጎል የሚገለጸው ወንድሞቹ ዮሴፍን ማነጋገር ባለመቻላቸው ብቻ ሳይሆን ስለ ሕልሙ ሁሉ ሲነግራቸው ዮሴፍ በነበረው የመኩራራት ሁኔታም ጭምር ነው። ይህም ለስሜታቸው ባለመጠንቀቅ ወይም እነርሱን በመናቅ ከአባታቸው ዘንድ እኩል ቅርበት እንዲኖራቸው የነበራቸውን ወስጣዊ ፍላጎታቸውን አላከበረላቸውም።

በዚህ መልኩ በየፊናቸው ጥላቻቸውን አከረሩ። በመካከላቸው የነበረው የግንኙነት መስተጓጎልም ወንድሞቹ ጥላቻቸውን በልባቸው "እንዲይዙ" አደረጋቸው፤ ጥላቻቸውም ባለ ጉልበቱ በገነፈለ ጊዜ ውጤቱ የከፋ ነበረ።

ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያስተምሩን በወንድማማቾች መካከል ያለ ጥቃት ስንዘራና እንግልት በወላጆችና በልጆች መካከል ከሚሆነው ባላነሰ ሁኔታ አጥፊ ሊሆን መቻሉን ነው።

ብዙ ልጆች ከወንድሞቻቸው በሚደርስባቸው ትንኮላ ይሠቃያሉ፤ ስለዚህ ወላጆች ይህን ልብ እንዲሉና በቤተሰብ ውስጥ በአጠቃላይ ስለ ጥቃት ስንዘራና እንግልት ሲነጋገሩ ይህን ጉዳይ በተለይ አንሥተው እንዲወያዩበት ማሳወቁ ጠቃሚ ነው።

**ትኩረት ሊደርግባቸው የሚያስፈልጉ፡-**

- በወንድማማቾች መካከል ያለ ጥቃት ስንዘራ አካላዊና /ወሲባዊ ጉዳትን ሊያካትት ይችላል።
- የጥቃት ስንዘራው መጠን እንደየዕድሜ ልዩነቱ ያይላል።
- በጥናት መሠረት በቤተሰብ ውስጥ ከሚደረገው ወሲባዊ ጥቃት ስንዘራ ውስጥ አምስት እጅ በታላቅ ወንድምና በታናሽ ወንድም ወይም እኅት መካከል የሚሆነው ነው።(በወጣትነት ዕድሜና እኩያሞች በሆኑ ዘመዳሞች መካከልም ወሲባዊ ጉዳት በብዛት አለ)
- በወንድማማቾች መካከል ወሲባዊ እንግልት መኖሩ ሲደረስበት ጉዳት አድራሹን ልጅ ከቤት ውጭ ወዳለ ማዕቀፍ በማውጣ ለጎጂውና ለተጎጂው እንክብካቤ ማድረግ ጠቃሚ ነው።
- ዕድሜው ከ 12 ዓመት በላይ የሆነው ልጅ ስለ ሥራው ወንጀል ኀላፊነት ይወስዳል።

**ጎረምሶች በወላጆቻቸው ላይ የሚያደርሱ ጥቃት፡-**

- አባትና እናትን ማክበር ባስመለከተ ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ ይናገራሉ። "አባትህንና እናትህን አክብር፤"(ዘፀ20፥12) በእርጅና ዘመናቸውም ቢሆን "እናትህም ባረጀች ጊዜ አትናቃት።"(ምሳ23፥22)
- ቅዱሳት መጻሕፍት አዛውንቶች ስለማክበርም ይናገራሉ። "በእርጅናዬ ዘመን አትጣለኝ፥" (መዝ71፥9) "በሽበታሙ ፊት ተነሣ፥ ሽማግሌውንም አክብር፥" (ዘሌ19፥32)
- ዘፀ21፥15-17 የልጆች በወላጆች ላይ እንግልት የማድረስ ክልከላ በግልጽ ተጠቅሷል "አባቱን ወይም እናቱን የሚመታ ፈጽሞ ይገደል።...አባቱን ወይም እናቱን የሚሰድብ ፈጽሞ ይገደል።" ይህ ክልከላ በወላጆቻቸው ላይ እንግልት የሚያደርሱትን ትልልቅ ሰዎችን ወይም ጎልማሶችን የሚመለከት ይመስላል።
- ይህ ጥቃት በንግግር መጉዳትን፣ በአካል መጉዳትን፣ አጋዥ የሌላቸውን ወላጆች ችላ ማለት፣ ኢኮኖሚያዊ ብዝበዛ፣ ገንዘብ ዘረፋ፣ ወሲባዊ እንግልት፣ ግድያ፣ ወላጆችን የመግደል ሙከራን ሊያካትት ይችላል።
- ይህ ሁኔታ በጣም አይነግም፤ ስለዚህ በአጠቃላይ በቤተሰብ ውስጥ ስላለ እንግልትና ጥቃት ስንዘራ ሲነገር ለውይይት ማቅረብ ያስፈልጋል።

## ተጎጂዎቹ

ብዙውን ጊዜ ተጎጂዎች ፍራቻና በራስ አለመተማመንን ይቀሰቅሱብናል፤ መልካምና ጋሻ በሆነው በእግዚአብሔር እንደሚያምኑ ሰዎች ከቀውስና ሥቃይ ጋር በተጋፈጥን ጊዜ እግዚአብሔር ሉዐላዊ ነው፤ ጸሎትንም ሰምቶ ይመልሳል፤ በሚለው ግንዛቤያችን ላይ ተግዳሮትና ጥያቄ ሊፈጥር ይችላል።

ይህ ተጋፍጦም የሕይወትን ተሰባሪነትና ይህን ተሰባሪነት ደግሞ ለመካድ ያደረግነው ሙከራ ውድቅነት ሊያሳስበን ይችላል። ይህ ለምን እንደሚሆን በተደጋጋሚ ለተጎጂዎችና ለራሳችን ምክንያታዊና አመክንዮአዊ በሆነ መልኩ ለማስረዳት እንሞካክር ይሆናል የሚሻለው ግን አለመሞከሩ ነው። “ይህ ለምን ይሆናል?” ለሚለው ጥያቄ ሁሌ መልስ የለንምና (የኢዮብ ባልንጀሮች እንዳደረጉት) መልስ ለማግኘት ወይም ለእግዚአብሔር ወግኖ ለመከላከል መሞከሩ የእኛ ድርሻ አይደለም።

ከዚህ ጋር አብሮ መታየት ያለበት ነገር ደግሞ መልስ ባለመኖሩ ለጥያቄ ቦታ አለመስጠት የለብንም የሚለው ነው። በተጎዱ ሰዎች የስሜት ረብሻ ውስጥ ብዙ ስሜቶች አሉ። እነዚህ ስሜቶች ብርቱዎች፣ ያልተገሩና “የከህደት” ናቸው የሚገልጹትም ቁጣን ሕመምን በቀልን ተስፋ መቁረጥንና ወዘተ ነው። እነዚህን ጥያቄዎችና ስሜቶች በመቀበል ተጎጂው ማዘንና ስሜቱን ለመግለጽ ሰሚ ጆሮዎችንም እንዲያገኝ ማስቻል አለብን።

---

## ተጎጂዎቹ ከጉዳቱ ወይም ከተጋልጠ በኋላ የሚቋቋሙት ችግሮች

- አካላዊ ችግሮች፡- ራስንና መላ አካልን ማመም፣ የዕንቅልፍ እጦት፣ ያላሰለሰ መደካከም፣ የክብደት መጨመር/መቀነስ ሁኔታ።
- አእምሯዊ ችግሮች፡- ድብርት፣ ጭንቀት፣ ያለፉት ጉዳት ተደጋግሞ በኀሊታ የመታየት ሁኔታ፣ ቅዥት፣ ዕረፍት ማጣት፣ የማስታወስ ችሎታን ማጣት፣ ድኅረ ሰቀቀን።
- መንፈሳዊ ችግሮች፡- የእምነት በጥያቄ መሞላት፣ እምነትን ማጣት፣ ተጠራጣሪነት፣ በራስ ላይ የጥፋተኝነት ስሜት፣በእግዚአብሔርና በፍቅሩ ላይ የተጣመመ አመለካከት።
- ስሜታዊ ችግሮች፡- ራስን ማስተዛዘን፣ ሥቃይ፣ ትርጒመ ቢስ መሆን፣ በቀል፣ በሆነው ሁኔታ ዕረፍት መነሳት፣ ለጥያቄ መልስን ለማግኘት በቅበዝበዝ፣ የብቸኝነት ስሜት፣ በእግዚአብሔርና በፍቅሩ ላይ የተጣመመ አመለካከት።
- የግንኙነት ችግሮች፡- መራቅ ከማኅበረሰቡ/ከቤተሰቡ ጋር ያለውን ግንኙነት ማጣት ቅጥ የሌለው የልጆች ተከላካይነት።
- ኢኮኖሚያዊ ችግሮች፡- በመድሃኒት፣ በጤና ነክ ምክርና በፍርድ ቤት ጉዳይ የወጪ መጨመር።
- ሥራ ነክ ችግሮች፡- በሥራ ላይ ሚዛናዊነትን ማጣት ወይም ደግሞ የሥራ ሱሰኛ መሆን።

**ተጎጂዎቹ የሚያስፈልጋቸው ነገሮች፦**

ተጎጂዎቹ በተለያየ መልኩ አንዱ ከአንዱ ይለያዩ እንጂ ከታች የተጠቀሱት ነገሮች ያስፈልጓቸዋል።

- መሠረታዊ ከለላ፦ ጉዳቱ ዳግም እንደማይደርስባቸው የመተማመን ስሜት እንዲኖራቸው።
- አድማጭ ጆሮ፦ የደረሰባቸውን ሲያወሩ መደመጣቸው እንዲሰማቸው።
- ክብደት መስጠት፦ የመጎዳት፣ የቁጣና የሰቀቀን ወዘተ ስሜታቸውን መረዳት።
- የጉዳያቸው ተሳታፊነት፦ በደረሰባቸው ጉዳት ሳቢያ ለሚያልፉት ሂደት ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ መሆን።
- ፈውስ፦ለሕይወት ትርጉም ማግኘትና ግንኙነትን ማደስ።
- ድጋፍ፦ ከጓደኞችና ከባለ ሞያዎች ዘንድ የሚሰጥ ምክርና ዕገዛ።
- ካሣ፦ ተጎጂዎች በተወሰኑ ሁኔታዎች ለጉዳታቸው የገንዘብ ካሣ ያስፈልጋቸዋል። ካሣውም ተቀጥረው መሥራት ባለመቻላቸውና በባለ ሞያዎች የሚሰጠውን የማገገሚያ አገልግሎቶች ወጪ መሸፈን ይገባዋል።

---

## ጎጂዎች/ ጉዳት አድራሾች/

መቼም ከእኛ እያንዳንዱ በሕይወቱ ዘመን ቢያንስ አንዴ ሌላውን ለመማታትም ሆነ ዕቃን ለማውደም ግልፍ ሳይልበት አልቀረም። ጥቃት ማድረስ መንሥኤው ብዙውን ጊዜ ችግር ነው፤ ሁላችንም ደግም በኑሯችን ጽኑ በሆኑ የችግር ሁኔታዎች ውስጥ እናልፋለን።

ጥቃት ሰንዛሪ ሰው በአብዛኛው ዕለት ዕለት የሚገጥሙትን ውስጣዊና ውጫዊ ጭንቀትንና ችግርን መቋቋም የማይችል ሰው ነው። ብዙውን ጊዜ ጥቃት ሰንዛራ የሚቃጣውም ይኸው ሰው የሚያስፈልገውን/ፍላጎቱንና ስሜቱን ማስረዳትና ራሱን መግለጽ ስለማይችል ነው። ቅር ሲሰኝና ሲጎዳ ወይም ደግሞ የመጣጣል ስሜት ሲሰማው ራሱን ገትቶ በንግግር በመመካከር አለያም ዕገዛ በመጠየቅ ስሜቱን እንደመቋቋም እየተበሳጨ እየተሠቃየና ያልሻረ ቂጣን በማከማቸት አንድ ቀን ቱግ ይልና ምላሹ ጥቃት ሰንዛራ ይሆናል።

በሌሎች ላይ ወሲባዊ እንግልት የሚያደርስም በወሲባዊ ፍትወት እና/ወይም ከስሜት ብስለት ማነስ እና/ወይም በሰዎች መካከል ባለ ማኅበረሰባዊ ግለላ ሲቢያ የሚሠቃይ ነው።

አብዛኛውን ጊዜ ጥቃት ሰንዛራ የሚመነጨው ደግሞ ቀድሞ በተለይም የግፍ ስሜታቸውን መግለጽና ማመዛዘን በማይችሉበት በልጅነታቸው ወቅት በራሳቸው ላይ ጉዳት ከደረሰባቸው ሰዎች ነው። በልጅነቱ የተጎዳና ጉዳቱን ማመዛዘን ያልተቻለው ደግሞ እርሱ ሌሎቹን እየጎዳ የጉዳቱን ዑደት ሊቀጥል ይችላል፤ የማይፈልገውን ያን የቀድሞውን የጉዳት ሰለባነት የሚያሳስበውንም ያጣጥለዋል።

ከእኛ እያንዳንዱ በአደገበት ቤተሰብ ውስጥና በሕይወት ገጠመኞቹ ካለፋቸው ሁኔታዎች የተነሣ ነገሮችን ለመቋቋሚያ የቀሰማቸው የራሱ እምነቶች፣ ዐቋሞች፣ ግንዛቤዎችና የአኳኋን መንገዶች እንዳሉት እንዲሁ ጎጂውም ከልጅነቱ ባወቀው ውስን ግንዛቤ ውስጥ ተይዞ ይቀራል።

---

## የጎጂዎች ስሜታዊ ድባብ

ርዕዮተ ዐለም፦ ጉዳት የሚያደርስ ሰው ዐለምን ማየት የለመደው ዐደገኛና አስፈሪ ቦታ እንደሆነ አድርጎ በመሆኑም ሁሌም የሚገኘው ባላሰለሰ ዝግጁነት ውስጥ ነው። ይህ ዝግጅቱ ደግሞ በማንኛውም የዐደጋና/ወይም የዛቻ ጊዜ ምላሽ እንዲሰጥና ነገሮችን እንዲቆጣጠር ያስችለዋል። በጉዳት አድራሹ ዘንድ ሥጋት ሆኖ የሚቆጠረው ምንድነው? እርሱ እንዴት መቋቋም እንዳለበት የማያውቀውን ማንኛውም ስሜት የሚገልጥበት ወይም የሚያወጣበትና የተለማመደውን ውስጣዊ ሚዛናዊነቱን ጥያቄ የሚፈጥርበት ነገር ሁሉ ነው። ሁኔታውን ለመቆጣጠር ቀላሉ መንገድ ቁጣ ነው። ቁጣ የስሜትን ምርነት በመግለጽ ወደ ተለመደው ውስጣዊ ስሜቱ እንዲመለስ ይረዳዋል።

መመሳሰያ መንገድ፦ አብዛኛውን ጊዜ ጉዳት አድራሹ የሚያድገው የጎጂነት ምሳሌ ባለበት ቤተሰብ ውስጥ ሲሆን (አርአያውም በአብዛኛው አባት ነው)። ጎጂው ሆነ ብሎ ምሳሌውን ባይከተለውም፤ ከጎጂው ምሳሌ ጋር መመሳሰልን ይመርጣል።

የብርታትና የድክመት ግንዛቤ፦ ጎጂው ለራሱ እንደመሰለው "ለደካሞች" እና "ለብርቱዎች" ስሜትና አኳኋንን ይለያል። ለእርሱ ደካማነት ማለት ችግር፣ ሽንፈት፣ ሃፍረት፣ ሕመም፣ ጥገኝነት፣ ስሜትንና/ወይም የሚያስፈልጉትን ነገሮች በቃላት መግለጽን የማያስፈልግ ሁኔታ ናቸው። በአብዛኛው ብርቱነት ማለት ደግሞ የበላይነትን ማሳየት፣ መራቅ፣ ለዘብተኝነትና ጉልበተኝነት ናቸው።

ስለ ራሳቸውን ያላቸው ግንዛቤ፦ ጎጂው ራሱን ደካማ አድርጎ ለመቁጠርና በእርሱ አስተያየት ደካማነት መስሎ የሚታዩትን ስሜቶችን ለመቀበል ይቸገራል። ጥፋተኝነትንና ኀላፊነትን ያምታታቸዋል፤ በመሆኑም ኀላፊነት መውሰድ ትርጉሙ ራስን ጥፋተኛ ማድረግ ነው ብሎ ስለሚያስብ ይህን ለመቋቋም ይቸገራል።

ስለ ሌላው ያላቸው ግንዛቤ፦ ጎጂው ችግሩና ሃፍረቱን የገዛ ስሜቱን ፍርሃቱን ጉዳቱን ለመካድና በሌሎች ላይ እነዚህን ስሜቶች ለመፍጠር በመሞከር ይቋቋመዋል። ሌሎችን ጥፋተኛ በማድረግ ራሱን ከጥፋተኝነት ነጻ ያደርጋል። እነርሱም ሊቀበሉት የማይፈልጉትን ስሜቶች በእነርሱ ላይ ያላክካል። የራሱን ግንዛቤ ይዞ በመቅረት ራሱን ብርቱ እነደ ሆነ አድርጎ ያስብ ዘንድ እንደ ደካማ ሰው አድርጎ የሚይዘው ይፈልጋል።

ስሜቶችን የመለየት ችግር፦ ተተናኳይ ሰው ስሜቶቹንና ችግሮቹን ለመለየትና ለመቀበል ይቸገራል። የድካም ገላጭ ከሆኑት ስሜቶች ይቆጠባል እንዲህም አብዛኛዎቹ ስሜቶቹ በቁጣና በመሳሰሉት ይወጣሉ።

የጉዳት አድራሹን ድርጊቶች ማውገዝ አለብን ሆኖም በሆነ ጊዜ፣ በሆነ አጋጣሚ በተለያዩ ምክንያቶች እኛ ከእርሱ ባላነሰ መልኩ የከፋ ድርጊት ልናደርግ እንችል እንደ ነበር በማሰብ ጎጂውን ራሱን እንዳንኮንነው ልንጠነቀቅ ይገባል።

ከዚህ ጋር አብሮ መታየት ያለበት ነገር ግን ጎጂውን የመረዳታችንና ያለበትን ሕይወት ግምት ውስጥ የማስገባታችን ሁኔታ በምንም ዐይነት መንገድ የተጎጂውን ጉዳት ማስተባበል የለበትም። ዛሬ ሰዎች በሌሎች ሰዎች ላይ የሚያደርሱትን ጥፋት ከነጭራሹ ማስቆም ይገባል። ያኔ ብቻ ነው ጎጂውንም ተጎጂውንም ወደ ማገገሚያ መምራት የሚቻለው።

---

## የከለላ ማዘዣ

### በከለላ ማዘዣ ማዕቀፍ ውስጥ ሰው ላይ ሊጣሉ የሚችሉት ማዕቀቦች የትኞቹ ናቸው?

- ወደ ቤተሰብ የመኖሪያ ቦታ የመግቢያ ፈቃድ ክልከላ።
- ከቤተሰብ መኖሪያ ቦታ ማራቅ።
- በማንኛውም መንገድ ቢሆን ቤተሰቡን እንዳያስቸግር መከልከል።
- ለሁነኛ ፀባይ ማረጋገጫ ተያዥ የማስያዝ ግዴታ።
- መሣሪያ እንዳይዝ/እንዳይታጠቅ መከልከል።
- ፍርድ ቤት በሚወስነው አካል በኩል የእንክብካቤ ክትትል ለመድረግ መገደድ።

### የከለላ ማዘዣ ጥያቄ ማመልከቻ  አቀራረብ።

- የማዘዣውን ጥያቄ ማመልከቻ የቤተሰብ ጉዳዮችን ወደሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በመኖሪያ ቤት አካባቢው በሚገኘው የወረዳ ፍርድ ቤት በኩል ማቅረብ ይቻላል። በድንገተኛ ጊዜም በመኖሪያ ቤት አካባቢው ባይሆን በተገኘው የወረዳ ፍርድ ቤት በኩል ማቅረብ ይቻላል።
- ቤተሰቡ የጥያቄ ማመልከቻ ቅጹን ይሞላና በጸሐፊዋ በኩል ያቀርበዋል።
- የጥያቄው ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ፣ በአንድ ሳምንት ውስጥ ጉዳዩ ለውይይት የሚቀርብበት ቀነ ቀጠሮ ይያዛል።

### የከለላ ማዘዣውን ለማውጣት የሚደረግ የውይይት ሂደት።

- ማዘዣውን ለማውጣት ይወስን ዘንድ ፍርድ ቤቱ ሁለቱን ወገን ያካተተ ውይይት ያካሂዳል።(ጎጂና ተጎጂን)
- አስቸኳይ በሆነም ጊዜ ፍርድ ቤቱ ከአንደኛው ወገን ጋር ውይይት ያካሂድና በቀጣይ ከሁለቱ ወገኖች ጋር የሚደረገውን የውይይት ጊዜ ይቀጥራል።

- ከሁለቱ ወገኖች ጋር ውይይት ካካሄደም በኋላ ማዘዣውን ለማውጣት ወይም ላለማውጣት ይወስናል።
- የከለላ ማዘዣው ያስፈለገው ዕድሜው ለዐቅመ አዳም ላልደረሰ የቤተሰብ አባል ከሆነ የማኅበረሰብ ጉዳይ ቢሮ ሠራተኛ ያጠናቀረውን ምርምር ካቀረበ በኋላ፣ ከቤት ውጪ ያለው የመሰናዶ አማራጭ ለልጁ ተስማሚ መሆኑ ከተመረመረ በኋላ ስለ ማዘዣው ይወሰናል።

**የፍርድ ቤቱ ውሳኔ።**

- ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን ለመቀበልና የከለላውን ማዘዣ ለማውጣት ከወሰነ፣ ማዘዣው እስከ ሶስት ወር ሊቀጥልና በተለያዩም ሁኔታዎች እስከ ዓመት የመራዘም ዕድል ሊኖረው ይችላል።
- የከለላ ማዘዣ ዕድሜው ለዐቅመ አዳም ላልደረሰ ሰው ከተሰጠ ከማኅበረሰብ ጉዳይ ቢሮ ሠራተኛ ዘንድ ለዐቅመ አዳም ባልደረሰ ሰውና የከለላ ማዘዣው በወጣበት በቤተሰብ መካከል ስለሚኖረው ቀጣይ ግንኙነት የምርምር ጥንቅር ይቀርባል።
- የከለላ ማዘዣው ከወጣ በኋላ ማዘዣው አልተከበረም የሚል አቤቱታ ለፖሊስ ከቀረበ ያላከበረውን አካል ማሠር ይቻላል።
- ፍርድ ቤቱ የከለላውን ማዘዣ ጥያቄ በግል አነሣሽነት የቀረበ ነው ሲል ላይቀበለው ወይም ደግሞ አልባሌ ነው በሚል ማዘዣውን በጠየቀው ሰው ላይ የፍርድ ማስፈጸሚያ ወጪዎች ለመንግሥት እና/ወይም ማዘዣውን ላስወጣበት ሰው እንዲከፍል ሊወስንበት ይችላል።

---

---

## ፀረ ዛቻ ማዘዣ

**የከለላ ማዘዣን መጠየቅ የሚቻልባቸው ሁኔታዎች የትኞቹ ናቸው?**

- የሆነ ሰው በቤተሰቡ ሕይወት፣ አካል፣ ንብረት፣ መልካም ስም፣ ግል ጉዳይ ወይም ነጻነት ላይ ዐደጋ ለማድረስ (በግልጽ/መስሎ በሚሰማ አነጋገር፣ በቀጥታ/በተዘዋዋሪ፣ በቃል/በጹሑፍ አለያም በሌላ መንገድ) ከዛተ።
- ቤተሰቡን የመሰለል ነገር ካደረገ፣ እንቅስቃሴውን ወይም ድርጊቱን እየተከታተለ (በግልጽ/መስሎ በሚሰማ አነጋገር፣ በቀጥታ/በተዘዋዋሪ፣ በቃል/በጹሑፍ አለያም በሌላ መንገድ) ደባ ካደረገ።

**በከለላ ማዘዣ ማዕቀፍ ውስጥ ሰው ላይ ሊጣሉ የሚችሉት ማዕቀቦች የትኞቹ ናቸው?**

- ማዘዣ በጠየቀው ሰው ላይ የሚደረግ የዛቻ ክልከላ።
- ማዘዣ የጠየቀውን ሰው ስለማስቸገር የሚደረግ ክልከላ።
- ማዘዣ ከጠየቀው ሰው ጋር እንዳይገናኝ መከልከል።(በቃል/በጹሑፍ አለያም በሌላ መንገድ)
- የጠያቂውን ሰው ግል ጉዳይ እንዳይነዳ መከልከል።
- ጠያቂውን ሰው የመሰለል ወይም በነገር ዳር ዳር የማለት ክልከላ።
- ከተወሰነ ቦታ ማራቅ፦ በጠያቂው ላይ ከምር ስለሚደርስ ጉዳት ሥጋት ሲኖር ብቻ።
- መሣሪያ የመያዝ/የመታጠቅ ክልከላ። በጠያቂው ላይ ከምር ስለሚደርስ ጉዳት ሥጋት ሲኖር ብቻ።
- ለሁነኛ ፀባይ ማረጋገጫ ተያዥ ማስያዝ።

**የከለላ ማዘዣ ጥያቄ ማመልከቻ  አቀራረብ።**

- የማዘዣውን ጥያቄ ማመልከቻ የቤተሰብ ጉዳዮችን ወደሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በመኖሪያ ቤት አካባቢው በሚገኘው የወረዳ ፍርድ ቤት በኩል ማቅረብ ይቻላል። በድንገተኛ ጊዜም በመኖሪያ ቤት አካባቢው ባይሆን በተገኘው የወረዳ ፍርድ ቤት በኩል ማቅረብ ይቻላል።
- ቤተሰቡ የጥያቄ ማመልከቻ ቅጹን ይሞላና በጸሐፊዋ በኩል ያቀርበዋል።
- የጥያቄው ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ፣ በአንድ ሳምንት ውስጥ ጉዳዩ ለውይይት የሚቀርብበት ቀነ ቀጠሮ ይያዛል።

**የከለላ ማዘዣውን ለማውጣት የሚደረግ የውይይት ሂደት።**

- ማዘዣውን ለማውጣት ይወስን ዘንድ ፍርድ ቤቱ ሁለቱን ወገን ያካተተ ውይይት ያካሂዳል።(ጎጂና ተጎጂን)
- አስቸኳይ በሆነም ጊዜ ፍርድ ቤቱ ከአንደኛው ወገን ጋር ውይይት ያካሂድና በቀጣይ ከሁለቱ ወገኖች ጋር የሚደረገውን የውይይት ጊዜ ይቀጥራል።
- ከሁለቱ ወገኖች ጋር ውይይት ካካሄደም በኋላ ማዘዣውን ለማውጣት ወይም ላለማውጣት ይወስናል።

**የፍርድ ቤቱ ውሳኔ።**

- ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን ለመቀበልና የከለላውን ማዘዣ ለማውጣት ከወሰነ፣ ማዘዣው እስከ ሶስት ወር ሊቀጥልና በተለያዩም ሁኔታዎች እስከ ዓመት የመራዘም ዕድል ሊኖረው ይችላል።

* የከለላ ማዘዣው ከወጣ በኋላ ማዘዣው አልተከበረም የሚል አቤቱታ ለፖሊስ ከቀረበ ያላከበረውን አካል ማሠር ይቻላል።
* ፍርድ ቤቱ የከለላውን ማዘዣ ጥያቄ በግል አነሣሽነት የቀረበ ነው ሲል ላይቀበለው ወይም ደግሞ አልባሌ ነው በሚል ማዘዣውን በጠየቀው ሰው ላይ የፍርድ ማስፈጸሚያ ወጪዎች ለመንግሥት እና/ወይም ማዘዣውን ላስወጣበት ሰው እንዲከፍል ሊወስንበት ይችላል።

## የተደብዳቢ ሚስቶች መጠጊያ

**ተደብዳቢ ሚስቶችን ወደ መጠጊያ ቦታ የመላኪያ ደብዳቤ፦**

* ሚስት በትዳር ጓደኛዋ አቅራቢያ መቆየት ካልቻለች አንዳንዴ ቀጣዩን ጥቃት ማስወገድ የሚቻልበት ብቸኛ መንገድ እርሷን ወደ ተደብዳቢ ሴቶች መጠጊያ መላክ ነው።

* ይህ የመላኪያ ደብዳቤ የሚሰጠው ደግሞ በፖሊስና/ ወይም በማኅበራዊ ጉዳይ ባለሥልጣናት ሲሆን የሚከናወነውም ከመጠጊያው አስተዳደር መመሪያዎችን በመቀበል ነው።
* የመጠጊያዎቹ አድራሻዎች ድብቆች የሆኑ ሲሆኑ የማይፈለጉ ሰዎችም የማይገቡባቸው ናቸው።
* ልጆችንም ወደ መጠጊያው ማምጣት ይቻላል።
* በመጠጊያው ሆና ተጎጂዋ ሕግና ገንዘብ ነክ ምክርን ልትቀበል ትችላለች እንዲሁም ወደ ፊት ልታደርገው ያላትን እርምጃ መለየት ትችላለች።

**በመጠጊያው ቦታ ስለሚያደርጉት ቆይታ ለተደብዳቢ ሚስቶች የሚተላለፍ ማስታወቂያ፦**

* በተደብዳቢ ሚስቶች መጠጊያ ቦታ የምትቆይ ሠራተኛ ሴት መብቷን ለማስጠበቅ ስትል በመጠጊያ ቦታ በመቆየቷ በሥራ ገበታዋ ላይ እንደማትገኝ ለአሠሪዋ ማሳወቅ አለባት።
* ሴቲቱ በሥራ ገበታዋ ላይ የማትገኝበት ወቅት ሊጀምር አካባቢ እንዳገባቡ ለአሠሪዋ ማሳወቅ አለባት።
* ሠራተኛዋ በሥራ ገበታዋ ላይ ከታጣችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 14 የሥራ ቀናት ድረስ ለአሠሪዋ በመጠጊያ ቦታ ስለመቆየቷ ከማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ማስረጃ መላክ አለባት።
* ከሥራ ገበታዋ ላይ መታጣቷ በሚያበቃበትም ጊዜ ሠራተኛዋ የመጠጊያው ቦታ ቆይታዋ መጠናቀቁን የሚያስረዳ ማስረጃ ከማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ታመጣለች።

**በተደብዳቢ ሚስቶች መጠጊያ ቦታ ለቆዩ ሴቶች የሚሰጥ የማላመጃ ስጦታ፦**

- በማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ፈቃድ አማካይነት በተደብዳቢ ሚስቶች መጠጊያ ቦታ ሁለት ወር ወይም ከዚያ በላይ የቆየችና ወደ ቋሚ መኖሪያ ስፍራዋ ያልተመለሰች ሴት፣ ከመጠጊያው ቦታ በወጣች ጊዜ ለመቋቋሚያና ለእንክብካቤ ፕሮግራም ተብሎ የተወሰነላት የማላመጃ ስጦታ ይደርሳታል።
- የማላመጃው ስጦታ 8000 ሼቁል ገደማ ያህል ነው፤ ልጆቿ ከእርሷ ጋር ከሆኑ ደግሞ ከ 1000 እስከ 2000 ሼቁል ያህል ተጨማሪ ይደርሳታል።
- የማላመጃው ስጦታ ጥያቄ የሚቀርበው ለማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ነው።
- የማላመጃው ስጦታ የሚከፈለው ሴቲቱ ከተደብዳቢ ሚስቶች መጠጊያ ቦታ ከወጣችበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ሁለት ወር ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ይሆናል።

**በዐደጋ ውስጥ ያሉ ሕፃናት ለሕፃናት ዕለታዊ እንክብካቤ መስጫ ቦታ (ለማየን) ያላቸው መብት፦**

- በቤተሰቡ ውስጥ ካለው ጥቃት፣ የአእምሮ መረበሽ፣ የአእምሮ ቀውስ፣ የአልኮል ሱሰኝነት፣ የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኝነት፣ ሴሰኝነት የተነሣ ወይም ከቤተሰቡ አባላት አንዱ ወንጀለኛ የሆነበትና በዕድሜው መሆን የሚገባውን ሁኔታ የማያሳይ የ 3 ዓመት ሕፃን በመኖሪያ ቤቱ አቅራቢያ ባለው የሕፃናት ዕለታዊ እንክብካቤ መስጫ ቦታ የመቆየት መብት አለው።
- ልጁን በሕፃናት ዕለታዊ እንክብካቤ መስጫ ቦታ ለማቆየት የሚከፈለውን የአጠቃላዩን ክፍያ 5% ማየኑ ሲችል፤ የአካባቢው ባለሥልጣን ደግሞ ከቀረው 25%ቱን ይችላል። ከዚህ የተረፈው ክፍያ ግን በተጠሪው ወይም በማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮው የሚከፈል ይሆናል።

## የትንንሽ ልጆች ከለላ መስጫ ማዕከል

የተለያዩ ወሲባዊ ወንጀሎች የተፈጸመባቸው ልጆች አቤቱታ ለማቅረብ፣ ለምርመራና ለማኅበራዊ ጉዳይ ጣልቃ ገብነት ሲባል ወደ ተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ለመዘዋወር ይገደዳሉ። በአብዛኛው ደግሞ እነዚህ የአገልግሎት ዘርፎች ለወንጀል ምርመራ የሚያስፈልገውንና የልጁንም ሆነ የቤተሰቡን ፍላጎት ያገናዘበ እርስ በርስ መናበብ ያለበት አሠራር አይሠሩም።

በመሆኑም በወሲብ ወንጀል ወይም በጥቃት ስንዘራ የተጎዳ ትንሽ ልጅ ወደ ተለዩ የከለላ ማግኛ ማዕከሎች የመቅረብ መብት አለው። የልጆችንና የወጣቶችን ከለላ መስጫ ማዕከሎች የታቀዱት በወንጀል ለተጎዱ ልጆችና ለቤተሰቦቻቸው የሚደረገውን የመጀመሪያ እንክብካቤ ለማሻሻል ነው።

በማዕከሉ ሥራ ተሰማርተው የሚገኙት ከአጠቃላይ ባለሥልጣናት (ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከፍትህ ሚኒስቴርና ከእስራኤል ፖሊስ ቢሮ) የተውጣጡ ሲሆኑ፣ የሚሠሩትም በልጁ ላይ በደረሰው ቀውስ ጣልቃ ገብነት ባለበት አሠራር ከማኅበራዊ ጉዳይ ጋር በመናበብ ልጁን ለፍርዱና ለሚመለከታቸው አገልግሎቶች ከማቅረብ ረገድ በሚያስደስት ድባብና የልጁን የሁኔታ ምርመራ በሚያከብር ብሎም የልጁንም ሆነ የቤተሰቡን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ሁሉም በአንድ ጥላ ሥር ነው። ይህም ለልጁ በተቻለ ፍጥነት መፍትሔ ለማግኘት ሲባል ነው። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ልጁ ከከለላ መስጫ ጊዜያዊና/ወይም ቋሚ ወደ ሆነ ውጫዊ ማዕቀፍ ያልፋል።

ልጁ በሚተማመንበት፣ ቤተሰቡን ከሚያውቅ ሰውና ከቤተሰቡ የድጋፍ ምንጮች ጋር በመሆን አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ ልጁን ሊረዱ የሚችሉ ዘመዶች ስሞችና አድራሻዎች አሰባስቦ ወደ እነዚህ ማዕከሎች መድረሱ አስፈላጊ ነው። እንዲህ ማድረጉ ልጁን ከቤት ውጪ ወደሆነ የእንክብካቤ መስጫ ማዕቀፍ እንዳይወጣ ይረዳዋል።

### በከለላ መስጫ ማዕከል ውስጥ ለትንንሽ ልጆች የሚሰጥ ርዳታ።

- ሕክምናዊ ምርመራና እንክብካቤ።
- አእምሯዊ ምርመራና እንክብካቤ።
- አካል በፍጥነት ሊያገኘው የሚያስፈልገውን ምግብና አልባሳት ማሟላት።
- እንደየጉዳዩ አስፈላጊውን ሕክምናና እንክብካቤ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ልጆችን ከሚመረምር ከመርማሪ ፖሊስ ጋር፣ የማኅበራዊ ጉዳይ ሠራተኛ የወጣቶች መርማሪ ወይም ሌላ ሕጋዊ አካል ጋር ማገናኘት።
- ሕግ ነክ ምክርና/ወይም ድንገተኛ ክፍልና/ወይም የረዥም ጊዜ ሕክምና ሊያገኝ ወደሚችልበት መንግሥታዊ አለያም መንግሥታዊ ያልሆኑ የርዳታ ሰጪ አገልግሎቶች መምራት።

## በጉዳት አድራሹ ላይ የሚደረግ የውንጀላ ክንዋኔ

በእስራኤል አገር መርማሪዎች መጽሐፍ ውስጥ በአጠቃላይ ጥቃት ስንዘራንና /ወይም እንግልትን ሆነ በቤተሰብ ውስጥ የሚኖርን ጥቃት ስንዘራንና /ወይም እንግልትን የሚከለክሉ ብዙ የቅጣት አንቀጾች አሉ።

በእነዚህ የወንጀል አንቀጾች አማካይነት ደግሞ ወላጆችንና /ወይም በቤተሰብ ውስጥ በዕድሜ ከፍ ያሉትን/ (ዕድሚያቸው ከ 12 በላይ የሆኑትን) ትንንሽ ልጆች ጭምር ለፍርድ ማቆም ይቻላል።

ወንጀሉ በቀለለ ልክ ወይም ደግሞ ማገገም የሚቻልበት ሁኔታ ሲኖር ፍርድ ቤቱ ተወንጃዩን ወደ ሂደቱ ማስፈጸሚያ ሊመራው ይችላል።

---

## የቅጣት አንቀጾች

- ቸል ማለት፦ ልጅን ለዐደጋ ሊያጋልጥ በሚችል መልኩ መተው ወይም ለልጅ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች አለማድረግ፦ እስከ 3 ዓመት እስራት።
- ትንሽ ልጅን ወይም የትዳር አጋርን መተናኮል፦ እስከ 4 ዓመት እስራት።
- ትንሽ ልጅን ወይም የትዳር አጋርን መጉዳት/ማቁሰል፦ እስከ 6 ዓመት እስራት።
- ትንሽ ልጅን (አእምሯዊ/አካላዊ) ጉዳት መጉዳት፦ እስከ 7 ዓመት እስራት።
- ትንሽ ልጅን (አእምሯዊ/አካላዊ) በጽኑ መጉዳት፦ እስከ 9 ዓመት እስራት።
- ትንሽ ልጅን አካላዊ/አእምሯዊ/ ወሲባዊ እንግልት፦ እስከ 9 ዓመት እስራት።
- የቤተሰቡን አባል በጽኑ መጉዳት፦ እስከ10 ዓመት እስራት።
- በሴቷ የትዳር አጋር ላይ አስጸያፊን ነገር ማድረግ፦ እስከ 3 ዓመት እስራት።
- በቤተሰብ ውስጥ በትንሽ ልጅ ላይ አስገድዶ አስጸያፊን ነገር ማድረግ፦ እስከ10 ዓመት እስራት።
- የትዳር አጋርን መድፈር፦እስከ 15 ዓመት እስራት።
- የትዳር አጋርን አስገድዶ መድፈርና ማንገላታት፦ እስከ15 ዓመት እስራት።
- በቤተሰብ ውስጥ በትንሽ ልጅ ላይ ግብረ ሰዶማዊ ድርጊት ማድረግ/መድፈር፦ 20 ዓመት እስራት።

- አዛውንትን መተናኮል፦ እስከ 5 ዓመት እስራት
- አዛውንትን በጽኑ መጉዳት፦ እስከ 7 ዓመት እስራት።
- የግል ጉዳዩን በመጣስ መጉዳት - ማስቸገር/ መሰለል/መብሸቅ/የግል ጉዳዩን ይፋ ማውጣት፦ እስከ 5 ዓመት እስራት።
- በወሲብ ነክ ጉዳዮች ማስቸገር፦ በመቸገር ላይ ያለው ሰው በአኳኋኑ/በቃላቱ አለመፈለጉን ከገለጸ፣ ወይም ደግሞ ትንሽ ልጅ በመሆኑ ይህ ዐይነቱን ምላሽ ባይሰጥም ተደጋጋሚ ወሲባዊ ጥያቄዎች ወይም ወሲብ ተኮር የሆነ አቀራረብ ወይም የሰውን ፆታ የሚያቃልል/የሚያጣጥል አቀራረብ፦ እስከ 2 ዓመት እስራት።
- በቤዜክ መገኛዎች አማካይነት (በቋሚ/በተንቀሳቃሽ መገኛ መሣሪያዎች ሁሉ) ማስቸገር - ለማስፈራራት፣ ለመጉዳት፣ ለማስቸገር ወይም ለማናደድ ሲባል በቋሚ/በተንቀሳቃሽ ስልኮች መጠቀም፦ እስከ 3 ዓመት እስራት።

## በቤተሰብ ውስጥ ጥቃት የማድረስ ሁኔታ ሲኖር የማሳወቅና የማስገንዘብ ግዴታዎች

**ወደ ፖሊስ አቤቱታ ማቅረብ፦**

- ማንኛውም አካል (አገልግሎት ሰጪዎች፣ ዘመድ አዝማድ፣ ጎረቤቶች፣ ጓደኞች ወዘተ) በቤሰብ ውስጥ ስለሚሆነው ጥቃት ስንዘራ ወደ ፖሊስ ለመደወል ይፈቀድለታል።
- ጥቃት ስንዘራን ወንጀል በተመለከተ የሚደወል ስልክ በፖሊስ ጣቢያ እንደ ድንገተኛ የስልክ ጥሪ (100) ተደረጎ ነው የሚወሰደው።
- ጥቃት ስንዘራን ወንጀል በተመለከተ ስልክ ሲደወል ይህ የስልክ ጥሪ ቅድሚያ ይሰጠውና የፖሊስ መኪና ተልኮ ጉዳዩ ምላሽ ያገኛል።
- አቤቱታውን መቀበልና ምርመራው ማድረግ የሚካሄዱት በሞያው በሰለጠነ  የጥቃት ስንዘራ መርማሪ እጅ ነው። አቤቱታውን ከተቀበለም በኋላ ይኸው ባለሞያ የተቀበለውን አቤቱታ ይመረምረዋ።
- በትዳር አጋሮች መካከል በሆነ የጥቃት ስንዘራን ወንጀል ተጠርጣሪ በሚመረመርበት ጊዜ ሁሉ፣ የመታሰር አስፈላጊነቱ ከግምት ውስጥ ይገባል። ባይታሰርም በዋስ ይለቀቃል፤ ይህ ሲሆን ግን የመለቀቁ ሁኔታ የተጎጂውን ደኅንነት ከለላ ጋር በማይፋለስ መልኩ ነው የሚሆነው።

- በቤተሰብ ውስጥ ስለሆነው ጥቃት ስንዘራን ወንጀል ተጎጂው አቤቱታውን ቢያነሣና የምርመራውን ሂደት/ የክሱ መመዝገብ እንዲቆም ቢጠይቅ ጥያቄው አብዛኛውን ጊዜ ተቀባይነት አይኖረውም። ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ በቤተሰብ ውስጥ ያለው የጥቃት ስንዘራ ሁኔታ ውስብስብ በመሆኑ ነው።
- በምርመራው ሂደት ለተጎጂውና ለጎጂው ከማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮና /ወይም ከተለያዩ ድርጅቶች ዘንድ የእንክብካቤና የእርዳታ ሐሳቦች ይቀርባሉ።

### በወንዱ/በሴቷ የትዳር አጋር ላይ የሚፈጸምን ወንጀሎች የማሳወቅ ግዴታ፡-

በትዳር አጋሮች መካከል ባለው የጥቃት ስንዘራ ጥርጣሬ ሁኔታ፣ የሕክምና እርዳታ እንዲደረግለት ወደ ሐኪም ቤት የሚመጣው ሰው ጥቃት እንደደረሰበት ጥርጣሬ ሲኖር ሁኔታውን የማሳወቅ ኀላፊነት የሐኪም ቤቶች ብቻ ነው።

### በወንዱ/በሴቷ የትዳር አጋር ላይ የሚፈጸምን ወንጀሎች የማሳወቅ ግዴታ፡-

ሃይማኖኛ ሰው በእንክብካቤ መስጠት ምክንያት ወይም በሙያው ወይም በስራው ማዕቀፍ ውስጥ ለሰው ምክር በሚሰጥ ጊዜ በዚያ ሰው ላይ ከትዳር አጋር በኩል በወቅቱም ይሁን ከዚህ በፊት የተፈጸመ ወንጀል (ወሲባዊ/አካላዊ ጥቃት ስንዘራ) እንዳለ ቢረዳ የሚከተሉት የማድረግ ግዴታ አለበት፡-

- ጥቃት የተሰነዘረበትን ሰው ወደ ፖሊስ ጣቢያ፣ ወደ ማኅበረሰብ አገልግሎት ክፍል እና/ ወይም ከማኅበረሰብ አገልግሎት ክፍል ጋር በመተባበር እንክብካቤ ማድረጊያና በቤተሰብ ውስጥ ያለን ጥቃት ስንዘራ መከላከያ ማዕከል መሄድ እንደሚችል ማሳወቅ።
- በፍትሕ ሚኒስቴር ድረ ገጽ ተዘግበው ከሚገኙት ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ውስጥ ለተጠቂው መኖሪያ ቦታ ቅርብ የሆኑትን አካላት አድራሻዎችና ስልክ ቁጥሮችን መስጠት።
- የሚደረጉትን ነገሮች በጹሑፍ ይዞ ጹሑፉን በሁነኛ ቦታ በማኖር ስለሚረዳው አካል መረጃው እንዲኖረው በደንብ መጠበቅ።

### በትንንሽ ልጆች ላይ የሚፈጸሙን ወንጀሎች የማሳወቅ ግዴታ፡-

ማንኛውም ሰው ሃይማኖተኛውን ጨምሮ በቅድሚያ የልጆችን ሕግ ባስመለከተ ለሚሠራ የማኅበረሰብ ጉዳይ ሠራተኛ ወ ይም ደግሞ የሚከተሉት ሁኔታዎች የተሟሉ ከሆነ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

- ጥቃት ስንዘራ፣ ወሲባዊ ጉዳት፣ እንግልት ወይም ትንሽ ልጅን በቸልተኝ የመተው ወንጀል እንደተሠራ ከታሰበ።

- ሕፃን በነላፊው (ወላጆች ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላት) አማካይነት ወንጀል ሲፈጸምበት ወይም የቤተሰብ አባል አማካይነት ወሲባዊ ወንጀል ሲፈጸምና ፈጻሚው ራሱ ትንሽ ልጅ ሲሆን።
- በቅርቡ (በቀናት ወይም በሳምንታት ወስጥ) የተፈጸመ ወንጀል ሲኖር።
- (ከሃማኖተኛው ይልቅ) ባለሞያ ሰው ላይ ወይም የትንሹ ልጅ ተጠሪ (ወላጅ) በሆነው ሰው ላይ በቅርቡ የተፈጸመ ወንጀል ባይሆንም እንኳን የበለጠ የማሳወቅ ግዴታ አለበት። ይህን ሳያሳውቁ ቢቀሩ ግን የ 6 ወር እስራት ቅጣት ያስከትላል።

---

---

## በውንጀላ ክንዋኔዎች ማዕቀፍ የተጎዱ የወንጀል ጉዳተኞች መብቶች

የወንጀል ተጎጂው የውንጀላው ክንዋኔ ወገን አይደለም። ምክንያቱም በእርሱ ቦታ ወንጀሉን አድርጓል በተባለው ተጠርጣሪ ላይ መንግሥት ክንዋኔውን ያካሂዳልና፤ ተጎጂው በፋይሉ ውስጥ ያለውን ጣልቃ ገብነት ሚዛናዊ ለማድረግ ሲባልም በወንጀል የጉዳተኞች መብቶች ሕግ አማካይነት ለተጎጂው የተለያዩ መብቶች ተሰጥተውታል።

የወንጀል ጉዳተኛው ወደ ፖሊስ አቤቱታ በሚያቀርብበት ጊዜ ለስልክ ግንኙነት የሚያገለግልና/ወይም ኮምፒዩተራይዝድ የሆነ ኮድ ይቀበላል። በዚሁ ኮድ አማካይነትም ስለ ፋይሉ ዝርዝር ሁኔታና ተጠርጣሪው የሚገኝበትን ሁኔታ በሚከተለው መልኩ እንዲያውቅ ይደረጋል፦

**ከሁሉም ዐይነት የሆኑ የወንጀል ጉዳተኛው መብቶች፦**

- ስለ ወንጀል ጉዳተኛ መብቶችና የውንጀላው ክንዋኔ የሚካሄድበትን መንገድ መረጃ ማግኘት፤
- የተጎዳበትን ወንጀል ባስመለከተ የውንጀላው ክንዋኔ ስለ ደረሰበት ደረጃ መረጃ ማግኘት፤ (ማለትም የፋይል መተላለፍ፣ የመዝጋት/የማራዘም፣ እስር/መለቀቅ/ሁኔታዎች/ የቀጠሮ ቀናት ወዘተ)
- የክሱን ደብዳቤ መመልከትና/ወይም የፋይሉን መዘጋት መመልከት፤
- ለወንጀል ጉዳተኛ መንግሥታዊና/ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ስለሚሰጡት እርዳታዎች መረጃ ማግኘት፤
- ውይይቱ በዝግ ችሎት ቢሆንም እንኳን ከሰው ጋር አብሮ በመሆን በፍርድ ችሎት ውይይት ላይ መገኘት፤

- ከተከሳሹ ውንጀላ ጋር ተያይዞ በፍርድ ቤቱ ውይይት ላይ ሊጠቀስ ያለውን፥ ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ የደረሰውን ማንኛውም (የአካል፣ የነፍስ፣ የንብረት) ጉዳትና ዐደጋ ለመርማሪው/ለጠያቂው አካል ቃልን በጹሑፍ መስጠት፤
- ከፖሊስ ኮምፒዩተራይዝድ መልስ መስጫ መረጃ ለማግኘትና የግል መለያ ኮድ ለመቀበል ማመልከቻ ማቅረብ፤
- ተጎጂው የተጎዳበት ጉዳይ ውይይቱ በችሎት እስኪጀመር ድረስ በማንኛውም ፍርድ ቤት ውስጥ ተጠርጣሪው/ተከሳሹ/ የእርሱ ልኡካንም ሆኑ ዘመዶቹ ሊገቡ የተከለከሉበት የተለየ የመጠበቂያ ክፍል እንዲያገኝ ይደረጋል።

**የጥቃት ስንዘራ/የወሲብ ወንጀል ጉዳተኛ ተጨማሪ መብቶች፦**

- ጉዳተኛው፣ ተፈላጊው አካል በመለቀቁ ሳቢያ የሚኖረውን ዐደጋ ባስመለከት በነፃ ለቃቂዎች ኮሚቴ ፊት ዐቋሙን በጹሑፍ የሚገልጽበት ዕድል መስጠት፤
- ጉዳተኛው፣ ይግባኝ ስለለማለቱ በአገሪቱ ፕሬዘዳንት ፊት ዐቋሙን በጹሑፍ የሚገልጽበት ዕድል መስጠት፤
- የተፈላጊውን አካል የእስር/የሆስፒታል መተኛ ጊዜ ባስመለከተ መረጃ ማግኘት፤ (የእርቅ ጅማሬ፣ የዕረፍት ጊዜ/ቀደም ብሎ የመለቀቅ ሁኔታ/ይግባኝ ማለት)
- በፍርድ መቾገርን ለማስወገድ ሲባል ወንጀሉን ባስመለከተ የሚደረጉትን የክንዋኔዎች ሂደት በጊዜው ማድረግ፤
- የመርማሪው አካል በሚያደርገው የምርመራ ሂደት ውስጥ ከተጠርጣሪው ጋር ካለው ጾታዊ ግንኙነት አንጻር እንዲደረግ ከሚፈለግ ምርመራ ወይም ይህ ምርመራ እውነቱን ለማውጣት የሚጠቅምና የግለሰቡን ክብርና ግላዊ ጉዳዮች በጠበቀ መልኩ ካልሆነ በቀር ተጎጂውን ስለቀድሞው ጾታ ነክ ጉዳይ የመመርመር ክልከላ፣
- የመርማሪው አካል በሚያደርገው የምርመራ ጊዜ ሌላ ተጨማሪ ሰው መገኘት፤
- ወንጀሉ ወሲብ ነክ በሆነ ጊዜ የምስክርነትን ቃል የመስጠቱ ሁኔታ እንዲቀልል መጠየቅ ይቻላል (ለምሳሌ፦ ተከሳሹ በሌለበት እንዲሆን ማድረግ)
- ዕድሜው ከ 14 ዓመት በታች የሆነ ልጅ ወሲባዊ ወንጀል፣ ጥቃት ስንዘራ፣ እንግልት፣ በቸልተኝነት መተውና አፈና በአካሉ የተፈጸመበት ወይም እርሱ በተገኘበት የተፈጸመ ከሆነ ወይም ደግሞ እርሱ ራሱ በድርጊቱ ተጠርጣሪ ሆኖ ሲገኝ ስለ ሁኔታው በቪዲዮ እየተቀረጸ በልጆች መርማሪ ይመረመራል ሆኖም በልጆች መርማሪ በኩል ቀለል ባለ ሁኔታ እንጂ በፍርድ ቤት ምስክርነት አይሰጥም (ማለትም፦ በፍርድ ቤት አይቆምም፤ ተከሳሹ ባለበት ምስክርነት አይሰጥም)

**ጽኑ የሆነ የጥቃት ስንዘራ/የወሲብ ወንጀል ጉዳተኛ ተጨማሪ መብቶች፡-**

- ለውንጀላው ክንዋኔዎች ላልሆኑ የግለሰቡን ግላዊ ዝርዝሮች የመስጠት ክልከላ (የተከሳሹ ከለላ፣ በባለሥልጣናት መካከል ያለ መረጃ ወዘተ)
- በሂደቱ የሚኖሩ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃዎችን መቀበል (የመርማሪው ስም፣ የእስራት/የመፈታት ሁኔታዎችን፣ ሌሎች ክንዋኔዎች ና ወዘተ)
- የሕግ አማካሪው በተከሳሹ ላይ የሚደረገውን የውንጀላ ክንዋኔ ለማዘግየት ከመወሰኑ በፊት ጉዳተኛው ዐቋሙን በጹሑፍ የሚገልጽበት ዕድል መስጠት፤
- የተባለውን ጉዳይ አስመልክቶ ክስን ከመወሰኑ ወይም ፋይል ከመዝጋቱ በፊት ዐቋሙን በከሳሹ ፊት በጹሑፍ የሚገልጽበት ዕድል መስጠት

## የጉባኤ/የክሂላ/ ለተቃውሞ ምክንያትነት

የተጎዱትን ከመከላከሉ ሂደት ጋር ወይም በጎጂዎች ላይ ከሚደረግ የውንጀላ ክንዋኔ ጋር በተጓደነ መልኩ መሲሓዊ ክሂላ በቤተሰብ ውስጥ ለሚኖረው ቀውስ የተቃዋሚነት ሚና ሊኖራት ይችላል። ከሰብአዊው ሁኔታ ጋር የተቆ ራኘ ወቅታዊነት ያላቸው በመሆኑ ክሂላ ግጭቶችና ቀውሶች ለመፍታት መሥጋት የለባትም። እንደ ክሂላ በአንድነት የመማሪያና ሌላውን የመርጃ ልዩ አጋጣሚ ነው፤ ሥቃይን መቋቋም ትዕግሥትን፣ ይቅርታንና እርቅን የመማሪያ አጋጣሚ ነው።

የግላሰቦችና የቤተሰብ ወንጀሎች ብሎም ቀውሶች መላው ክሂላን በመጉዳት ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው። አንዳንዴም ደግሞ በራሷ በክሂላዋ ውስጥ ያሉትና መፍትሔ መሻሻልና መስተካከል የሚያሻቸው ችግሮች፣ እክሎችና መንስኤዎችን ጠቋሚዎች ሊሆኑም ይችላሉ። በመሠረቱ ክሂላ በቀውስ ወቅት ተፅዕኖ የሚያሳድሩባትን ሐሳቦችና ስሜቶቿን ልትገልጽ ደግሞም ራሷን ልትመረምርና በቀውስ ወቅት ያላትንም የኀላፊነት መጠን ልትፈትሽ ብሎም ሁኔታውን ለማሻሻል ለመርዳት መሞከር ይገባታል።

ከዚህም ሌላ በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት እንደ ክሂላ አንዳችን የሌላው ብልቶችና እርስበርሳችን በሕይወት የተሳሰርን ነንና እንድንቃረን ሳይሆን እንደ ወንድማማቾች ልንተባበር ይጠበቅብናል። የክሂላ ብልቶች የተቀራረቡና እርስበርስ የተሳሰሩ በመሆናቸው ስለ ክሂላው አባላት ሰላም፣ በግል ጉዳዮችም በተለይም የችግር ምልክቶች ወይም ደግሞ በሕይወት ውስጥ አሉታዊ ለውጦች ሲታዩ እርሱን ያገባው ዘንድ መብትም ግዴታም አለው። በሰዎች የግል ጉዳዮች ውስጥ የመግባቱ ሁኔታ ለሐሜት ሳይሆን ለሌላውና ለክሂላ ከማሰብ የተነሣ ነው።

በእርግጥም በክሂላው አባላት የግል ሕይወት ውስጥ የመሳተፉ መብት በግዴለሽነት የሚገኝ አይደለም። በእነርሱና በክሂላዋ መካከል ረዘም ላለ ጊዜ በአክብሮትና በፍቅር የደረጀ መተማመን ከሌለ በቀር የተደብዳቢው ልጅም ይሁን ተደብዳቢዋ ሴት ወደ ክሂላ አባላቱ ደጅ ዝር አይሉም። በመሆኑም የተጎጂዎችን ልብ በማግኘት ወደ እኛ ይቀርቡና ምክርና እገዛ ያገኙ ዘንድ ምቹ ሁኔታን መፍጠር አለብን። በሕይወታቸውም ሆነ በቤተሰባቸው ሕይወት ውስጥ ጣልቃ ለመግባት እንዲፈቅዱልን በተተናኳዮቹም በኩል ደግሞ እንዲተማመኑብን የማድረግ ነገር ማዳበር አለብን።

በሚከተሉት ገጾች ውስጥ ክሂላ በቤተሰብ ውስጥ የሚሆንን የቀውስ ሁኔታ እንድትከላከልና እንዳስፈላጊነቱም ጣልቃ እንድትገባ የሚያስችል ናሙና ይቀርባል። ናሙናው የተለያዩ ክሂላዎች ቤተሰባዊ ጥቃት ስንዘራ ከመከሰቱ በፊት፣ ጥቃቱ በተፈጸመበት ጊዜና ነገሩ ካባራ በኋላ ሁኔታውን የመቋቋሚያ መሣሪያ ለመለገሥ ነው።

በቀውሱ ወቅት ወይም ከዚያ በኋላ ጣልቃ የመግባቱ እርምጃ ከመከላከሉ ሂደት ወይም/ እና ከውንጀላው ሂደት ጋር አብረው ጎን ለጎን አለያም ሂደቶቹ ካበቁ በኋላ ወይም በምትካቸው እንደየመንሥኤዎቻቸውና እንደየክሂላዎቹ ዐቅም ሊከናወኑ ይችላሉ።

የክሂላዋ ሂደት ለሚደረገው ቤተሰባዊ እንክብካቤና መልሶ የማቋቋም ሁኔታ ማዕከላዊው ሊይዝ የሚችልባቸው ሁኔታዎችም አሉ። የክሂላዋ ሂደት ለፍርድ ሂደቶቹ ተጨማሪ ድጋፍና ማጠናከሪያ የሚሆንበትም ሁኔታዎች አሉ። የፍርድ ሂደቶቹ ሳይጠናቀቁ በፊት የክሂላዋን ሂደት መጀመርም ሆነ መፈጸም የማይቻልባቸው ሁኔታዎችም አሉ።

በማንኛውም ሁኔታ ለክሂላዋም ሆነ ለቤተሰቡ በጎነት ሲባል በተፈላጊው ጊዜ አቅጣጫ ማስያዣ ይሆን ዘንድ በየክሂላው ቤተሰባዊውን ቀውስ ባስመለከተ የሆነ የተዋቀረ ምላሽ ቢኖር ጥሩ ነው። ይህ ዐይነቱ ምላሽ በቀውስ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ለክሂላም ሆነ ለቤተሰብ ከፍተኛ እገዛ ሊያደርግ ይችላል።

---

## ተጎጂውና ክሂላዋ - የመጮኽ ግዴታና የማድመጥ ግዴታ

በዘዳግም 22፥23-27 የታጨችን ልጃገረድ ስለመድፈር የተሰጠ ብያኔዎች ተጠቅሰውበት ይገኛል። ምንም እንኳን ትዕዛዛቱ ለዘመኑ ሰሚዎች ከባድ ቢሆኑም እግዚአብሔር ክሂላንና ተጎጂውን በሚያይበት ሁኔታ አንጻር ከትዕዛዛቱ መመሪያዎችን ማግኘት ይቻላል። በብያኔዎቹ መሠረት በከተማው የተደፈረችው ልጃገረድ አስጥሉኝ ብላ ካልጮኸች ፍርዱ ልጃገረዷቱን ከደፈራት ወንድ ጋር አብሮ መወገር ነው፤ "በሜዳ" የተደፈረችው ልጃገረድ ግን አስጥሉኝ ብላ ብትጮኽም ባትጮኽም አትወገረም።

ይህ ማለት ደግሞ ተጎጂው ጉዳቱን አስመልክቶ የመጮህና ቃልን በማሰማት ጉዳቱን የመከላከል ወይም የማስቆም ግዴታም ሆነ ኀላፊነት አለበት። የተጎጂው መጮህና ድምፁን የማሰማት ግዴታውና ኀላፊነቱ ክሂላዋ እርሱን እንድትሰማው ያደርጋታል።

"ከተማ" ጩኺው ሊሰማ እንደሚችል አስቦ የሚጮኽበት ሁኔታ ምሳሌ ነው "ሜዳ" ደግሞ ጩኺው ቢጮኽ የሚሰማው እንደሌለ በማወቅ የማይጮኽበት ሁኔታ ምሳሌ ነው።

እነዚህ ብያኔዎች ሰዎች የተጎጂውን ድምፅ የመስማትና ለተጎዳው እርዳታ የማድረግ ኀላፊነታቸው ብዩን መሆኑን ያሳያሉ። ስለሆነም ክሂላዎቻችን ተጎጂዎች ድምፅቸውን ሊያሰሙ የሚችሉባቸው "ከተማዎች"ሊሆኑ ይችላሉ ምክንያቱም ድምፃቸውን ሰምቶ ሊረዳቸው የሚፈጥን እንዳለ ያውቃሉና። በሌላ አንጻር ደግሞ ማሰማት እስኪሣናቸው ድረስ የተጎጂዎችን ድምፅ የማንሰማባቸው ቦታ "ሜዳ" ሊሆኑ ይችላሉ።

---

---

## በክሂላ ሊተገበር የሚመከር ናሙና

ናሙናው ውስብስብም ቢሆን በእርግጥ ተጨባጩን ሁኔታ የሚያመለክት ነው። ሁሉም ክሂላዎች እንዲህ ዐይነቱን ናሙና ለመተግበር ግብዐቱም ሆነ ክህሎቱ እንደሌላቸው የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ ክሂላዎች ሁሉ ከናሙናው ሐሳቦችን መመሪያዎችንና አጽንኦቶችን ለየራሳቸው በሚስማማ መልኩ እንዲቀዱና ጥቅም ላይ እንዲያውሉት ይመከራል።

## አንደኛ ደረጃ - መከላከል

**ዐላማ፡-** ግንዛቤን ማሳደግ፣ ገና ቀውስ ያልተቀሰቀሰባቸውን ቤተሰባዊ መድብሎች ማነጽና ማጠናከር።

**የአፈጻጸም መንገዶች፡-**

- (በየዓመቱ) የሚከተሉትን ዐብይ ርዕሶች ያካተተ፥ የአንድ ዐመት ተከታታይ ትምህርት
  * የወንድ ማንነትና ኀላፊነት፤ የሴት ማንነትና ኀላፊነት።
  * ከጋብቻ በፊትና በጋብቻ ማዕቀፍ ውስጥ ያለ ግንኙነት።
  * ልጆችን ማስተማርና የልጆች አስተዳደግ ባስመለከተ የተለያዩ አስተዳደግ ተኮር ዘዴዎችን ለወላጆች ማሳወቅ።
  * የቤተሰባዊው መድብል ሙሉነትና ሰላም መሆን ፋይዳው።
  * የቤተሰባዊው መድብል መፍረስ መግለጫዎች።
  * በቤተሰብ የሚደርስ ቀውስ፣ በቤተሰብ ውስጥ ያለ ጥቃት ስንዘራና እንግልት፣ መልሶ የመቋቋምን ሁኔታ ተኮር የሆነ።
  * ክሂላ ያላትን ቦታና በቤተሰብ ላይ በሚደርሰው ቀውስ ላይ የክሂላ አሠራርና ጣልቃ ገብነት የሚያስረዳ ገለጻ።

**ጥንዶች እንክብካቤና ምክር ወደ ማግኛ መምራትና ማበረታታት፡-**

- ጥንዶች ከጋብቻ በፊት ና/ወይም በጋብቻ ወቅት፤
- ያገቡ ወይም ያላገቡ ብቸኞችን ( በድሮ ጊዜ፣ በልጅነታቸው ዘመንና/ ወይም በቤተሰባቸው ውስጥ) ባለፉት ሰቀቀን ወይም ቀውስ ሳቢያ፤

## ሁለተኛ ደረጃ - ፈልጎ ማግኘት

**ዐላማ፡-** በቤተሰብ ውስጥ ባለ ጥቃት ስንዘራና /ወይም እንግልት የሚሠቃዩ ጥንዶችን፣ ወላጆችንና/ ወይም ልጆችን መለየት።

**የአፈጻጸም መንገዶች፡-**

- በቀውስ ውስጥ የሚገኙ ልጆችን/ ጎረምሶችን/ ዐዋቂዎችን ለመለየት መሪዎችን፣ አለማማጆችን፣ አማካሪዎችን ማሰልጠን።
- የቤት ለቤት ጉብኝቶች፡- በክሂላ ውስጥ ባሉ አገልጋዮች - መሪዎች፣ አለማማጆችና ወይም አማካሪዎች አማካይነት በክሂላዋ አባላት መኖሪያዎች ጉብኝቶች ማድረግ።

## ሶስተኛ ደረጃ - ማሳወቅ

**ዐላማ፡-** ተጎጂዎችን በቤተሰብ ውስጥ የሚሰነዘርባቸውን ጥቃትና /ወይም እንግልት እንዲያሳውቁ ማበረታታት።

**የአፈጻጸም መንገዶች፡-**

- በትምህርት መስጫ ክፍሎችና በወጣቶች የቡድን ማዕቀፍ ውስጥ ልጆችን/ ወጣቶችን በቤተሰብ ውስጥ ስላለ ጥቃት ስንዘራና እንግልት ማስተማር። አስፈላጊ ሆኖም ሲገኝ እምነት ለሚጥሉበት ለኀላፊያቸው ስለ ሁኔታው እንዲያሳውቁ ማበረታታት።
- በክሂላም ውስጥ ይሁን ከክሂላ ውጪ ለጎጂዎችና ለተጎጂዎች የእርዳታ ሰጪ ስም ዝርዝሮች ያሉበትን የመረጃ ገጾች ማደል።
- የክሂላዋ አባላት በክሂላዋ ውስጥ ስላለ ቤተሰብ የሚያውቁት የጥቃት ስንዘራና የእንግልት ሁኔታ እንዲያሳውቁ ማበረታታት፤ ተጎጂ አባላቱንም ስለ ሁኔታው እንዲያሳውቁ ማበረታታት፤ በዐደጋው ውስጥ ያሉ ልጆች ካሉም እራሳቸው እንዲያሳውቁ ማበረታታት።
- ወደ እርሱ በመቅረብ የሚያሳውቁትን ኀላፊ መምረጥ፡- ሰው መረጣ (በሰል ያሉ ጥንዶች ቢሆኑ ይመረጣል) የስራ ድርሻቸውም በቤተሰብ ውስጥ ስላለ ጥቃት ስንዘራና እንግልት ሁኔታን አቤቱታን መቀበል እንዲሆን ያስፈልጋል። እነዚህን ሰዎች እንዲህ ያለውን አቤቱታ ሰምተው የመጀመሪያ ክር መስጠት እንዲችሉ ማሰልጠን ያስፈልጋል። ይህ የስራ ድርሻም ለተመረጡቱ ሰዎች በክሂላዋ ውስጥ ዋና ሥራቸው ቢሆን ይመረጣል።

## አራተኛ ደረጃ - እንክብካቤና ጣልቃ ገብነት

**ዐላማ፦** በአጭርና በረዥም ጊዜ ውስጥ ለቤተሰብ ተስማሚ የሆነ እገዛና ምሪት መስጠት።

**የአፈጻጸም መንገዶች፦**

- በቤተሰብ ውስጥ ስላለ ጥቃት ስንዘራና እንግልት ሁኔታን አቤቱታን ለመቀበል ኀላፊ የሆነው ሰው፥ ስለ ሁኔታው የተቻለውን ያህል መረጃዎች እያሰባሰበ በሂላ ውስጥና ከክሂላ ውጪ ለሚኖረው ጣልቃ ገብነት የረዥምና የአጭር ጊዜ ፕሮግራሞች ያዘጋጃል። እነዚህ ፕሮግራሞች እንደየአቤት ባዩ ፍላጎት፣ ሕጉ እንደሚጠይቀውና እንደየሁኔታው ጽኑነት ይዘት ይለዋወጣሉ።
- ኀላፊ የሆነው ሰው ቤተሰቡን ሂደቱን ሁሉ አብሮት ያካሂዳል ወይም ሌላ ሰው/ጥንድ/ ይመርጥና አብሮ እንዲያካሂድ ያደርጋል።
- የተለያዩ አልባሌ አቤቱታዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ኀላፊ የሆነው ሰው ለሚሠራው ሥራ ንቁ መሆን አለበት። ከዚህ ጋር አብሮ መታየት ያለበት ነገር አልባሌ አቤቱታዎች በቤተሰብ ውስጥ ላለው ቀውስ ግልጥ ያሉ ምልክቶች በመሆናቸው በመንኛውም ሁኔታ እርዳታ ማድረግ ያስፈልጋል።

**የጣልቃ ገብነት ደረጃ መነሻ ነጥቦች - የጠፋውን መፈለግ፦**

ምን ይመስላችኋል? ለአንድ ሰው መቶ በጎች ቢኖሩት ከእነርሱም አንዱ ቢባዝን፥ ዘጠና ዘጠኙን በተራራ ትቶ ሄዶም የባዘነውን አይፈልግምን? ቢያገኘውም፥ እውነት እላችኋለሁ፥ ካልባዘኑቱ ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ በእርሱ ደስ ይለዋል። እንደዚሁ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ በሰማያት ያለው አባታችሁ ፈቃድ አይደለም። (ማቴ18፥12-14)

- በቤተሰብ ውስጥም ሆነ ከእርሱ ውጪ ስላለ ጥቃት ስንዘራና እንግልት ሁኔታ ሁለት ጠፎች አሉ። እነርሱም - ጎጂና ተጎጂ ናቸው።
- የክሂላዋ አባላት የተቻላቸውን ሁሉ አድርገው ወደ ክሂላዋ ዕቅፍ መልሰው ያስገቡት ዘንድ አንዱን በግ መፈለግ አለባቸው፤ አንድም የጎዳውን፥ አንድም የተጎዳውን።
- መጨነቁ አንዱ ጎጂ፥ ሌላው ደግሞ ተጎጂ በመሆን ለጠፉት ለሁለቱም በጎች ደህንነት ነው፤ ተጎጂውንና ክሂላዋን ለመከላከል መፈለጉና ጎጂውን ወደ ክሂላዋ ዕቅፍ መልሶ ለማስገባት የመፈለጉ ጉዳይም ውስብስብና ውጥረት ፈጣሪ ሁኔታ ነው።

በመልካሙ ሰማርያዊ ታሪክ ላይ በ (ሉቃ10፥30-37) እንደሚታየው የእየሱስ ልብ ለተጎጂው ሰው ንቁ ነበረ፦

> ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ፦ አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ በወንበዴዎችም እጅ ወደቀ፤ እነርሱም ደግሞ ገፈፉት ደበደቡትም በሕይወትና በሞት መካከልም ትተውት ሄዱ። ድንገትም አንድ ካህን በዚያ መንገድ ወረደ አይቶትም ገለል ብሎ አለፈ። እንዲሁም ደግሞ አንድ ሌዋዊ ወደዚያ ስፍራ መጣና አይቶት ገለል ብሎ አለፈ። አንድ ሳምራዊ ግን ሲሄድ ወደ እርሱ መጣ አይቶትም አዘነለት፥ ቀርቦም ዘይትና የወይን ጠጅ በቍስሎቹ ላይ አፍስሶ አሰራቸው፥ በራሱ አህያም ላይ አስቀምጦት ወደ እንግዶች ማደርያ ወሰደው ጠበቀውም። በማግሥቱም ሁለት ዲናር አውጥቶ ለባለቤቱ ሰጠና፦ ጠብቀው፥ ከዚህም በላይ የምትከስረውን ሁሉ እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ አለው። እንግዲህ ከነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ባልንጀራ የሆነው ማንኛው ይመስልሃል? እርሱም፦ ምሕረት ያደረገለት አለ። ኢየሱስም፦ ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ አለው። (ሉቃ10፥30-37)

ሰማርያዊው ያለ ምንም ጥያቄ፥ የመጀመሪያ የሕክምና እርዳታ አደረገለት፤ ወደ አስተማማኝ ቦታም ተሸክሞ በመውሰድና ስለ እርሱ በመክፈል የሚያስፈልገውን እንዲያገኝ አደረገ፤ ተመልሶም ያለበትን ሁኔታ ጠየቀ።

---

## የእየሱስ ልብ ለጎጂዎችም ንቁ ነበረ፦

> ጻፎችና ፈሪሳውያንም በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ አመጡ በመካከልም እርሱዋን አቁመው፦ መምህር ሆይ፥ ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች። ሙሴም እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን፤ አንተስ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ? አሉት። የሚከሱበትንም እንዲያገኙ ሊፈትኑት ይህን አሉ። ኢየሱስ ግን ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ፤ (ዮሐ8፥፥3-7)

ልባችንም ለጎጂውም ለተጎጂውም የነቃ ሊሆን ያስፈልገዋል። ስለሆነም እንዲህ በመሰሉ አሳዛኝ ሁኔታዎች ለጠፉቱ የሚኖረን መጨነቅ በሁለት መልኩ መሆን አለበት፦
(1) **በአጭር ጊዜ ውስጥ፦** ጥቃቱን ማስቆምና ተጎጂውን መከላከል ማለትም የተጎጂውን አካላዊ አእምሯዊና መንፈሳዊ ደህንነት ማረጋገጥ። አንዳንዴም ደግሞ በቤተሰብ ውስጥ ያሉ ጎጂና ተጎጂን ለጊዜ መለያየትም ያስፈልጋል።

(2) **በረዥም ጊዜ ውስጥ፡-** የጎዷው የተግግጽ ማለትም ጎዷውን ንስሐ እንዲገባ በመጋበዝ የጉዳቱን አላግባብነት ተቀበሎ ቤተሰባዊውን መድብል እንዳዲስ እንዲያንጽ መርዳት።

**በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት - ጥቃቱን ማስቆምና ተጎጂዎቹን መከላከል**

**የአፈጻጸም መንገዶች፡-**

- በጥንዶች መከከል የጥቃት ስንዘራ ሁኔታ ሲኖር የመጠጊያ ቦታ መኖር አስፈላጊነት።
- በልጆች ላይ የጥቃት ስንዘራና የእንግልት ሁኔታ ሲኖር የማሳወቅ ግዴታ መኖር።
- የሕክምና እርዳታ በሚያስፈልግበት ሁኔታ ደግሞ ወደ ጤና ጣቢያ፣ ወድ ሐኪም ቤትና ወደ ድንገተኛ የሕክምና ማዕከል መምራት።
- ሁኔታው የሚቀጥልና/ወይም ጽኑ በሚሆንበት ጊዜ በማኅበረሰቡ በኩል ወይም ከዚያ ውጪ በሆኑ አካላት በኩል (ፖሊስ የማኅበራዊ ጒዳይ ክፍል የእርዳታ ሰጪ በሆኑ አካላት በኩል) የጥቃት ስንዘራውን ወይም የእንግልቱን ሁኔታ በማዘግ ማስቆምና/ ወይም ተጎጊውን ከለላ ወዳለበት መጠጊያ ማስተላለፍ።
- ማኅበራዊ ከሆኑ ወይም ካልሆኑ አካላት ጋር በሚደረገው ተሳይፎ ውስጥ ዋናዋ ክሂላ ከቤተሰቡ ጋር አብራ መሆኗን የመቀጠሏ ጒዳይ ፋይዳ አለው።
- ለልጆችም እንዳስፈላጊነቱና ዐቅም በፈቀደ መጠን የገንዘብና የሕክምና እርዳታ ማድረግ።
- እንዳስፈላጊነቱም ወገኖቹን ፍርድ ነክ እርዳታ ወደሚያገኙበት መምራት።

**ሴትና/ ወይም ልጅ በድንገት ከቤት መውጣት ባለባቸው ጊዜ ከቤት ይዘዋቸው መሄድ የሚያስፈልጓቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?(የተቻለውንና ሁኔታው የሚጠይቀውን ያህል)**

- ተጨማሪ የቤትና/ ወይም የመኪና ቁልፎችን
- ጠቃሚ መረጃዎች (ከንብረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎችን [የኪራይ ውል]፣ የባንክ ሂሳብ ደብተር፣ የጥንዶቹ የስምምነት ውሎች፣ የመንጃ ፈቃድ፣ የዋስትና መታወቂያ፣ የዋስትና ደንቦችን)
- የሕክምና መረጃዎች (የጤና ጣቢያ ካርድ፣ የክትባቶች ማስታወሻ ደብተር፣ የመድሃኒት መግዣ ደብዳቤዎች፣ ጤና ነክ ወረቀቶችን ወዘተ)
- የትምህርት መረጃዎች (የልጆች መታወቂያ፣ የምርመራ ወረቀቶች ወዘተ)
- ወዲያው አስፈላጊ ሆኖ ለሚገኝ ሁኔታ ለመሸጥ እንዲቻል ጌጣጌጦችና ዋጋቸው ውድ የሆኑ ቁሳቁሶችንም
- የቤተሰብ ፎቶዎችን
- የልጆች አሻንጉሊቶችንና መጫወቻዎችን

**በረዥም ጊዜ ውስጥ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት - ጉዳቱን አምኖ ቤተሰባዊውን መድብል እንዳዲስ ማነጽ**

> ወንድምህም ቢበድልህ፥ ሂደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው። ቢሰማህ፥ ወንድምህን ገንዘብ አደረግኸው፤ ባይሰማህ ግን፥ በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና፥ ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ፤ እነርሱንም ባይሰማ፥ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፤ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት፥ እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ። (ማቴ18፥15-17)

**የረዥም ጊዜ ሂደቶችን መተግበሪያ መሠረታዊ መመሪያዎች፦**

**"ቢበድልህ"**

ሂደቱ ሁሉ የሚገልጸው ተጎጂው የመገሠጽ መብትና ግዴታ ያለበት መሆኑን ነው። ይህን ለማድረግ ተጎጂው ግብረገባዊ ሥልጣን አለው። ስለደረሰበት በደል መልስ ለማግኘት የማወጣጣትና የመጠየቅ ኀይል ያለው ራሱ ነው። ተጎጂው በሂደቱ ማዕከላዊ የሆነ ተሳትፎ እስካለው ድረስ ፍላጎቱና ጥያቄው ቅድሚያ ሊያገኝ ይገባዋል። እርሱ ደካማም፤ ዐቅመ ቢስም አይደለምና።

**"ገሥጸው/ውቀሰው"**

ተግሣጽ ሁለት ፍቺዎች አሉት፦

(1) የሆነ ሰው ትክክለኝነቱን ወይም እውነተኝነቱን ለማሳየት እማኝ ወይም ማረጋገጫ ማምጣት

(2) ሰው ለመሳሳቱ/ ኀጢአት ለመሥራቱ በፊቱ ተጨባጩን ነገር ማስቀመጥ ያህም ሰውየውን ወደ ቀናው መንገድ ለመመለስ ሲባል ነው።

የተግሣጽ ዐላማው መልካም ይሆንለት ዘንድ ሰውየውን ለማስተካከል ነው። የመገሠጽ ተነሣሽነቱም ከቀናው መንገድ የሳተውን ሰው ለመመለስ ከመፈለግ የመጣ ነው። በዘሌ19፥17 "ወንድምህን በልብህ አትጥላው፤ በባልንጀራህ ምክንያት ኃጢአት እንዳይሆንብህ ገሥጸው" ተብሏልና።

በጥላቻ ሰውየው ለድርጊቱ የእጁንና ዋጋውን ሲያገኝ ለማየት መመኘት መኖር የለበትም ይልቁኑም ሰውየው መንገዱን ሲያቀና ለማየት መመኘት ነው እንጂ። ካለበት ለመውጣትና ለንስሓ ዕድል ፈንታ ሳንሰጠው እንዲያው በመጥላት ኀጢአት እንዳናሸክመው እንጠንቀቅ። "የተገለጠ ዘለፋ ከተሰወረ ፍቅር ይሻላል" (ምሳ27፥5)፤ "ልጄ ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አትናቅ፥ በገሠጸህም ጊዜ አትመረር።እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥጻልና፥ አባት የሚወድደውን ልጁን እንደሚገሥጽ" (ምሳ3፥11-12)፤

"እነሆ፥ እግዚአብሔር የሚገሥጸው ሰው ምስጉን ነው"(ኢዮብ5፥17)፤ ለነገሩማ ተግሣጽም እኮ የፍቅር መግለጫ ነው።
ተግሣጹ በሚካሄድበት ጊዜ ተጎጂው በጎዳው ሰው ፊት የድርጊቱ ተጨባጭ ሁኔታና ያስከተለውን ነገሮች ሊገልጥ ይችላል፤ ይህንንም በማድረጉ የተሰማውን ስሜት ቁጣውን ብስጭቱን በመግለጽ ጎጂው ሁኔታዎቹን እንዲጋፈጣቸው አጋጣሚን ይፈጥርለታል።

**"ቢሰማህ"**
በዚህ ስፍራ (ቢሰማህ፣ ባይሰማህ) እየተባለ ያለው መቼም ቴክኒካል ለሆነው የመስማት ሁኔታ የታሰበ አለመሆኑ ዕውቅ ነው፤ ለማለት የተፈለገው ተግሣጽን ተቀብሎ በዚያ መሠረት መሄድ ነው እንጂ፤ያ ወንድም ተግሣጽን ተቀብሎ መሆን እንደሚገባው ከሆነ "ወንድምህን ገንዘብ አደረግኸው"፤ ማለትም መልሰህ አተረፍኸው ማለት ነው።

ተግሣጽን የመቀበል ምልክቶቹ ምን ምን ናቸው? መቀበል፣ ኀላፊነት መውሰድ፣ የተጎጂውን ጉዳትና ስሜት መረዳት፣ ስለ ሁኔታው መልስ በመስጠትና ጉዳትን በመቀበል እንዳስፈላጊነቱ ሁሉ ለእንክብካቤና መልሶ ለማደስ ዝግጁ መሆን ናቸው። ይህም መሉ በሙሉ የሆነ በንስሐ መመለስ ነው።
ከመጀመሪያውም ቢሆን ለመስማት ይችል ዘንድ ቀደም ብሎ ጎጂውን አግኝቶ ከእርሱ ጋር መሥራት የሚቀድምበት ሁኔታዎችም አሉ። (በአብዛኛው በጎጂው ዘንድ ከጥቃት ስንዘራ ሌላ ተጨማሪ በሽታ ሲኖር አስቀድሞ ያለውን ሱስ ወይም የአእምሮ በሽታን ማከም ያስፈልጋል)

**የጣልቃ ገብነት ደረጃዎች፦**

**የመጀመሪያ ደረጃ፦** አንድ ለአንድ "ለብቻ"
- ተጎጂው ጎጂውን ለመገሥጽ ይመክራል
- በቤተሰብ ውስጥ ባለ ጥቃት ስንዘራና እንግልት ሁኔታ ተጎጂው ለጎጂው ብዙ ጊዜ ማለትም በአንድም በሌላም መንገድ አኳኋኑ ጥሩ አለመሆኑን ነግሮት ንግግሩ ያለ አድማጭ ከንቱ እንደቀረበት መገመት ይቻላል።

**ጎጂው ግን ባይሰማ ->**

**ሁለተኛ ደረጃ፦** ተጨማሪ ሰዎች
- ተጎጂው ከእርሱ ጋር አንድ ሌላ ሰው ወይም ሁለት ተጨማሪ ሰዎች ይዞ በመሄድ የጎዳውን ይገሥጸዋል።

- ተጎጂው ከጎጂው ፊት ለመቆ የማይችል ከሆነ ቀኝ እጁን ለሌሎች መስጠት ይችላል።
- አንዳንዴም በሁለቱ ወገኖች መካከል ለተጎጂው ድፍረትን የሚሰጥና ጎጂውን ለማዳመጥ የሚያስችል ሶስተኛ ሰው ማስገባት ይመረጣል።
- ጎጂው ወደሚያከብራቸውና/ ወይም ሐሳባቸውን ወደሚቀበለው አካላት ጉዳዩን መምራት ይመከራል።

**ጎጂው ግን ባይሰማ ->**

**ሶስተኛ ደረጃ፦ ክሂላ**

- ተጎጂው ወደ ክሂላ ይቀርብና መላው ክሂላ ጎጂውን ይገሥጸዋል (ይህ እንደ ተጎጂው ፍላጎትና ችሎታ እርሱ በተገኘበት ወይም እርሱ በሌለበት የሚሆን ነው።)
- ሰው በንስሐ ካልተመለሰ በክሂላው ደህንነት ላይ ጥያቄ ይፈጥራል፤ በመሆኑም ጉዳዩ ይቀየርና ክሂላ ዐቀፍ ይሆናል።
- በአብዛኛው በጥቃት ስንዘራ/ እንግልት ማዕቀፍ ውስጥ ዝምታ ጎጂው መጉዳቱን እንዲገፋበት ጉልበት ይሰጠዋል፤ ወደ ክሂላ ቀርቦ የማሳወቁ ሁኔታ ግን በጉጋቱ ዙሪያ የተፈጠረውን ዝምታ ያስወግድና በእርሱ ፊንታ (ሁሉም ዐወቁ በሚል) ሀፍረት ያሰፍናል።
- ነገሮች ፊት ለፊት ሲወጡ በመጋፈጥ መቋቋም እንጂ መሸሽ አይቻልም። እዚህ ጋር ትኩረት ሊደረግበት የሚያስፈልገው ጉዳይ በክሂላዋ ስብሰባ መጀመሪያ ላይ የጎጂውን ድርጊት በይፋ ስለማጋለጥ እየተነገረ አለመሆኑን ነው፤ ምክንያቱም ይህ ሊሆን የሚገባው ለዚህ ተብሎ በተመደበ ስብሰባ ላይ ነውና። በዚህም ስብሰባ ላይ ጎጂውን ለመገሠጽ የክሂላዋ ዋናዎች ይገኛሉ።

**ጎጂው ግን ባይሰማ ->**

ጎጂው ከዚህ በኋላ በክሂላዋ ዕድል ፈንታ አይኖረውምና የክሂላዋ ደጅ በፊቱ የተከፈተ ይሆናል። የማይሰማ ሰው እንደ ቀራጭና እንደ አረመኔ ተደርጎ ይቆጠራል። በእየሱስ ዘንድ ቀራጮችንና አረመኔዎችን ኀጢአተኞች ሆነው በመቆጠራቸው የእርሱ ማዳንና ፈውስ አስፈልጓቸዋል። እርሱ መልሶ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት አብስሯቸዋል።

ሰው ጉዳት አድርሶ በንስሐ ለመመለስ ዝግጁ ካልሆነ ክሂላ እርሱ ላይ የምትደክመውን ድካም ማቆም አለባት ምንም አንኳን ደጇን ለእርሱ ክፍት የማድረግ ግዴታም ቢኖርባት፣ ለድርጊቱ ብድራት እንዳለውና ግን ደግሞ ተመልሶ የክሂላዋ ቤተሰብ የመሆን ተስፋና ዕድል ፈንታ እንዳለ መግለጽ አለባት።

በእርግጥም፣ ጎጂው በእውነት ጥፋተኛ ሳይሆን ቀርቶ፥ ድርጊቱን አምኖ ላይቀበል የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ሁሌም መገመት ያስፈልጋል። በመሆኑም ጥፋተኛ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ያለውን መብት መግፈፍ አይቻልም።

ጎጂው በእያንዳንዱ ደረጃ  ከሰማ ግን ->

**"ወንድምህን ገንዘብ አደረግኸዋል"** የሚባለው

ጎጂው ኀጢአቱን አምኖ በንስሐ ለመመለስ ብሎም ለመለወጥ ዝግጁ የሆነ ሲሆን ነው። ከዚህ ጋር በማያያዝ ሊታወቅ የሚያስፈልገው ነገር እንዳየነው ተግሣጽን "መስማት" ማለት ጥፋተኝነትን አምኖ መቀበል ማለት ነው፤ አብዛኛውን ጊዜ ደግሞ ቤተሰባዊው ቀውስ በተግሣጽና ተጎጂው የደረሰበትን ጥፋት፣ ክሂላዋ የደረሰባትን ጥፋት አምኖ በመቀበልና ኀላፊነትን በመውሰድ ብቻ አያበቃም። (አንዳንዴም በጎጂው በኩል፣ በተለዩ ሁኔታዎች፣ በክሂላ በኩል፣ በተጎጂውም በኩል) ጉዳትንና የደረሰውን ጥፋት አምኖ ለተጎጂው/ ለዘመዶች/ ለክሂላ መልስ በመስጠት ለመታደስና መሉ በሙሉ በንስሐ ለመመለስ ዝግጁ መሆን ያሻል። ቀውሱ የቀጣይነት ሁኔታ ሲኖረውና ጉዳቱ ሲቀጥል እየተነገረ ያለው ለረዥም ጊዜ ስለሚካሄድ ሁነት መሆኑ ነው።

በመሆኑም ጎጂው ሰምቶ መስማማት በሚጀምርበት ደረጃ ላይ በአንድነት የእርቅን የመካካስንና በጎጂና በተጎጂው በቤተሰባዊው መድብል እንዲሁም በክሂላ መካከል መስማማትን ለማምጣት ለሁለቱ ወገኖች፣ ለደጋፊዎቻቸው፣ ለክሂላ ተወካዮች የሚሆን አንድ ቀጠሮ ወይም ተከታታይ የመምከሪያ ወይም የውይይት ቀጠሮዎች መያዙ ይመከራል። ይህ ዕቅድ ደግሞ "ተግሣጽን ወደ መስማት"ና "ወንድምን ገንዘብ" ወደ ማድረግ ይመራል።

## ለምክክር የሚሆኑ ግንኙነቶችና ወሳኔ

### የተሳታፊዎች ስብስብ፦

- የጎጂና የተጎጂ ውይይት፦ ይህ ጎጂውና ተጎጂው ከተወሰኑ ተሳታፊዎች ጋር አብረው በመሆን የሚያደርጉት ነው።
- የጎጂ፣ የተጎጂና የደጋፊዎች ውይይት፦ በዚህ ውይይት ውስጥ ደግሞ ጎጂውና ተጎጂው ዋነኛ ተሳታፊዎች ይሆኑና እያንዳንዳቸው አንድ ወይም ሁለት ደጋፊዎች ይኖሯቸዋል።
- የጎጂ፣ የተጎጂና የክሂላ ውይይት፦ በዚህ ውይይት የሚሳተፉት ደግሞ ጎጂው፣ ተጎጂው፣ ደጋፊዎችና የክሂላ ተወካዮች። ይህ በአብዛኛው የሚስማማው ቀጣይነት ላለው የጉዳት ሁኔታና የወሰባዊ እንግልት ነው።

### አቀናጅ፦

የውይይቱን ሂደት የማኅብረሰብ ሳይንስ ባለሞያ የሆነ ሰው ወይም የአማካሪነት ሞያ ያለው አለያም የቡድን ውይይት መሪ የሆነ ሰው እንዲመራው ይመከራል። የቡድኑ አቀናጅ ከሁኔታው ጋር ንክኪም ሆነ የግል ጥቅም የሌውለው መሆኑ ይበጃል። በቤተሰብ ውስጥ ባለ የጥቃት ስንዘራ ወይም ወሲባዊ እንግልት ሁኔታ ውስጥ ለጕዳዩ የሚስማሙ ጥንዶች (ወንድና ሴት) እንዲሆኑ ይመከራል።

የአቀናጁ ዋና ሥራ ዐቋሙን መግለጽ ሳይሆን በሁለቱ ወገኖች መካከል የሚሆነውን የውይይት ሂደት ሚዛናዊነት እያበረታታና በግለሰቦቹ መካከል ያለውን ግንኙነት በመጠበቅ የመስማሚያን መስመርን መዘርጋት ነው። እንዲህ ባለ ሁኔታም አቀናጁ የወገኖቹን ስምምነት፣ ለሂደቱ ያላቸውን ግድ መሰኘት፣ እየመረመር በሂደቱ ሁሉ ደካማ ጎኖችን፣ ፍላጎቶችን፣ ልዩነቶችን በመለየት ደንቦችን ለማስከበር አወያይ ጥያቄዎችን እየጠየቀና ማብራሪያ እንዲሰጥ እየለመነና ለመንፈስ ቅዱስ ስፍራ እየሰጠ ተሳታፊዎቹን ያዘጋጃል። በጸሎት ሆኖ ለማዳመጥ የጸሎት ጊዜ ይሰጣል ወገኖቹ ወደ ስምምነት እንዲደርሱ ያግዛል፤ ግዴታዎቻቸውን እንዲወጡ ይከታተላል።

**ስምምነት፦**

የምክክሩ ሂደትና ውሳኔ በወገኖቹ ሙሉ ስምምነት መሆን አለበት፤ ያለ ስምምነትና ሙሉተሳትፎ ሊሆን የሚችል ነገር እንደሌለ መግለጽ ያስፈልጋል።

**ከለላ፦**

በምክክሩ ሂደትና ውሳኔ ሁሉ ለተጎጂው ጥበቃ ለማድረግ መጣር ያስፈልጋል። ተጎጂው በሂደቱ የመጠበቁን ሁኔታና በነገሮች ግልጽነት እርግጠኝነት እንዲሰማው ምሥጢር የግድ መጠበቅ አለበት።

ጎጂው አካላዊና/ ወይም ወሲባዊ ጥቃት የሰነዘረ ቢሆንና በሚደረገው ስብሰባ ላይ ተጎጂው ከጎጂው ጋር አብሮ መገኘት ቢፈልግ ከጎጂው ዘንድ ሊቃጣ ለሚችለው ዐደጋ ዝግጁ መሆን ይመከራል።

ለሙሉ ጥበቃው ምንም አስተማማኝ ነገር እስከሌለ ድረስና ተጎጂው ወይም የሂደቱ አቀናጅ ተጎጂው ጎጂውን መቋቋም እንደማይችል እስከተሰማቸው ድረስ የጎጂውን ፍላጎቶች ይዞ በቦታው በመቅረብ ድምፁን የሚያሰማለት ሰው ይኑር እንጂ ያለ እርሱ ተከታታይ ስብሰባዎችን ማቀድ ይቻላል። ጎጂው ሲኖር ተጎጂ የማይኖርበት ወይም ደግሞ ተገላቢጦሹ የሚሆንበትና እያሰለሱ የሚደረጉ ስብሰባዎችን ማዘጋጀት ይቻላል።

**ዝግጅት፦**

በሂደቱ የሚሳተፉት መስማማታቸውን ለማወቅ ከእያንዳንዱጋር የሚደረጉ የማዘጋጃ ስብሰባዎች ያሻሉ።

ለምሳሌ፦

- **ተጎጂውን የማዘጋጃ ጥያቄዎች፦**
  * ቀውሱ በአንተም ሆነ በዘመዶችህ ላይ ተፅዕኖ ያሳደረው እንዴት ነበረ? የደረሰብህስ ጉዳት ምንድን ነው? ጎጂው ይቅርታ ቢጠይቅህስ ምን ይሰማህ ይሆን? ከዚህ በኋላ ከጎጂው ጋር የፈለገውን ዐይነት ግንኙነት ቢሆን፣ እንዲኖርህ ትፈልጋለህን?

- **ጎጂውን የማዘጋጃ ጥያቄዎች፦**
  * ለአንተ በንስሐ የመመለስ ትርጉሙ ምንድን ነው? ተጎጂውን ለመካስስ ዝግጁ ነህን? ድርጊትህን ዳግም ላለመፈጸም የምጠየቀውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነህን? ቀውሱ በአንተም ሆነ በዘመዶችህ ላይ ተፅዕኖ ያሳደረው እንዴት ነበረ?

- **የማዘጋጃ ደረጃ፦** የሚከተሉትን ነገሮች ልብ ማለት ጠቃሚ ነው።

  * ተቃውሞና ምዝበራ፣ ተጎጂው ላይ ሊሆን ያለ ከፍተኛ አእምሯዊ ጉዳት (በተለይም በድኅረ ሰቀቀን በሚያልፈው ሥቃይ) ሚዛናዊነት ያጣ የማስደሰት ፍላጎት ወይም ደግሞ የተገላቢጦሽ።

- **ይሆናሉ ተብለው ተስፋ የሚደረጉ ነገሮችን ቅንጅት፦**

  * ከስምምነትና ከዝግጅት በኋላ ይሆናሉ ተብለው ተስፋ የሚደረጉ ነገሮችና የተሳያፊዎቹን ማንነት፣ ሚና፣ የአኳኋን ደንቦች፣ የግንኙነት ደንቦች በተመለከተ (በተለይም የመናገርና የማድመጥ ፈቃድን ባስመለከተ) ደግሞም እስከ ሂደቱ መጨረሻ ድረስ የመሳተፍ ግዴታን (ሁሉም ይህን ማድረጉ ምንም ጥቅም የለውም ብለው ካልወሰኑ በቀር) ምሥጢራዊነትን፣ በሂደቱም መጨረሻ በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ መሳተፍን ባስመለከተ በሁለቱም ወገኖች ስምምነት አማካይነት ማቀናጀት ይመከራል።

- **የስብሰባዎቹ ቅደም ተከተል፦**

  * ስምምነቶቹን መከለስ
  * ይሆናሉ ተብለው ተስፋ የሚደረጉ ነገሮች ቅንጅት
  * የተደረጉት ድርጊቶች ትረካ
  * ለተደረገው ድርጊት የጎጂው አምኖ መቀበል
  * የተጎጂው ታሪክ (ዳራ መንስኤ ስሜት ቁጭት)
  * ከተጎጂው ደጋፊዎች ዘንድ የሚሰነዘር አመለካከት
  * ከጎጂው ደጋፊዎች ዘንድ የሚሰነዘር አመለካከት
  * ከክሂላዋ ተወካዮች ዘንድ የሚሰነዘር አመለካከት (በክሂላዋ ላይ ስላሳረፈው ተፅዕኖ፣ ስለ ክሂላዋ ኀላፊነት የሚሰጥ ገለጻ)
  * ለተጎጂው ስለሚያስፈልገው የተሃድሶ ፕሮግራም ውይይት
  * ወደ ስምምነት የሚያደርስ የጥፋት ካሣ ውይይት

በፕሮግራሙ ቅንብር መጨረሻ ሁለቱም ወገኖች የሁለታቸውን ስምምነት የሚያጸና ትክክለኛና ወቅታዊ በሆነ ተጎጂው/ ክሂላዋ የሚካሄብት ሁኔታ፣ በጎጂው ላይ ስለሚጣልበት ዕዳ፣ ለተሃድሶ ፕሮግራም የጎጂው ግዴታዎች፣ የጎጂው/የተጎጂው ደጋፊ አካላት፣ ተቆጣጣሪና ተከታታይ አካላት ወዘተ፣ ስምምነቱ የተላለፈስ ሲኖር ምን ይደረጋል ወዘተ የሚሉትን ባካተተ መስማሚያ ላይ ይፈርማሉ።

## የምክክር ስብሰባዎች ወቅት መቀየር

ጎጂው ተግሣጽን ሰምቶ ለመቀበል ፍላጎት በሚያሳይበት ግን ደግሞ ዕጥፍ በሆነ ሕመም ሁኔታ (በሱሰኝነት፣ በአእምሮ ችግር) የሚሠቃይ ሲሆን፣ ጎጂው አእምሮው እስኪስተካከል ርደስ ይህ ሂደት ወደ ኋላ ሊገፋ ይችላል።

ከውንጀላ ሂደት ውጪ ሌላ አማራጭ በሌለበት ሁኔታም ይህ ሂደት ወደ ኋላ ሊገፋ ይችላል። እንዲህ ባለ ሁኔታም ሊሆን የሚገባው የክሂላው ሂደት ከውንጀላ ሂደት ጋር በተጓደኘ መልኩ ሊከናወንና ተፅዕኖ ሊያሳድርባቸው ይችላል።

# የክሂላ ጣልቃ ገብነት ኀይል

## የውይይት ትርጒም

“ደግሞ እላችኋለሁ፥ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።” (ማቴ18፥19-20)

የሚፈውስም ሆነ የሚቃወም እግዚአብሔር ይሁን እንጂ ክሂላ እርሱ የሚሠራበትን ሁኔታና ቦታ የምታመቻች ነች። ቀውስ በተፈጠረበት ሁኔታ ውስጥ መፍትሔ ለስጠት በመሞከር የሚደረጉ የተሳታፊዎች ስምምነትና ጥያቄዎች ክብደት ያገኛሉ።
ስለ ይቅርታ፣ ስለ እርቅ፣ በንስሐ ስለመመለስ፣ ስለ ተሃድሶና ጉዳት ስለመተው ተብለው የሚደረጉ ስምምነቶችና ጥያቄዎች ለጽድቅና ለሰላም፣ ለምህረትና ለእውነት ሕያው ምሳሌዎች ናቸው። እነዚህ ከዐለማዊ አስተሳሰብ ጋር በተቃረነ መልኩ ይቅር ያለበት የእየሱስ ባሕሪያትና በመስቀሉ ሥራ የሰበራቸው ማብቂያ የለሽ የሰዎች ጥቃት ስንዘራና በቀል ሽረት ምሳሌዎች ናቸውና የእግዚአብሔር መንፈስም እንዲህ ባሉ ጊዜዎች ይገኛል።

### በስብሰባዎቹ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ክብደት

“እውነት እላችኋለሁ፥ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።” (ማቴ18፥18)
ቀውስ ወይም ግጭት ባሉበት ሁኔታዎች ክሂላ እግዚአብሔር እንደ ሰጠው መመሪያ በሠረት የ“መከልከልና መፍቀድ” ብያኔ የመስጠት መንፈሳዊ ሥልጣን አላት።

**የጎጂ - ተጎጂ ግንኙነት ማደስ፦**

ጉዳት ጎጂና ተጎጂን የሚያገናኘው በጤናማ መልኩ አይደለም። ኀጢአትና መዘዞቹም በሁለቱ ላይ ተፅዕኖ ያደርጋሉ፣ ይህ በመሆኑም ቋጠሮውን ለመፍታትና በጉዳቱ ሳቢያ ከሚከተለው መዘዝ ነጻ ለመሆን እርስበርስ ይፈላለጋሉ።

ተጎጂው ጎጂው እንዲሰማው፣ ያደረሰውን ጉዳት መዘዝ ዕውቅና እንዲሰጥ፣ በዚህም እንዲጸጸት፣ ለድርጊቱም ኀላፊነት እንዲወስድ፣ መልስም እንዲሰጥበትና ጉዳቱን የመካሻ ነገር (መልሶ መቋቋሚያ፣ ካሣ ወዘተ) እንዲያደርግ ይፈልጋል።

ጎጂው ተጎጂው ታሪኩን እንዲተርክና አኳኋኑ እንዴትና ምን ያህል ለጉዳት እንደዳረገው እንዲረዳው ይፈልጋል። የእምነት ቃሉንም ተጎጂው እንዲሰማና ምናልባትም ደግሞ ይቅር እንዲለው ይፈልጋል። ከተጎጂው ጋር የሚደረገው ስብሰባ ጎጂውን የጥፋተኝነት ስሜቱን እንዲቋቋምና ነገሮችን እንዳዲስ በመጀመር ወደ ክሂላ እንዲመለስ ይረዳዋል።

**የይቅርታ ብርታት፦**

“በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ፦ ጌታ ሆይ፥ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን? አለው። ኢየሱስ እንዲህ አለው፦ እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም።” (ማቴ18፥21-22)

“ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ወንድምህ ቢበድልህ ገሥጸው፥ ቢጸጸትም ይቅር በለው። በቀንም ሰባት ጊዜ እንኳ ቢበድልህ በቀንም ሰባት ጊዜ፦ ተጸጸትሁ እያለ ወደ አንተ ቢመለስ፥ ይቅር በለው።” (ሉቃ17፥3-4)

እየሱስ የሚያስተምረን መጀመሪያ የጎዱንን ሰዎች ለመገሠጽ እንድንሞክር፣ ለጉዳታችን እልባት እንድንሰጥ፣ ከጎዳን ሰው መልስ እንድንሻ፣ የተፈጠረውን ቀውስ ለማጣራት እንድንሞክርና ለለውጥ፣ ለእርቅና ለካሣ ዕድል ፈንታ እንድንሰጥ ነው። ቀጥሎ ያለው ነገርም ጎጂው ተግሣጽን ተቀብሎ መንገዱ ቢያቀናም ባያቀናም ይቅርታ ማድረግ ነው።
የይቅርታን ባሕሪይ እየሱስ አመንዝራይቱን ሴት ይቅር ካለበት ሁኔታ አንጻር መለካት ይቻላል፤ ብዙዎቹ በማመንዘር ድርጊቷ ሊወግሯት ዝተውባት ምላሹን ያዩ ዘንድ ወደ እየሱስ ፊት አመጧት (ዮሐ8፥3-10)። እየሱስ ግን ሴትዮይቱ አልኮነናትም፤ ወደ ኀጢአት ሥራ እንድትመለስም አልፈቀደ
ላትም። ይቅርታ ማለት ሰው እንደ ድሮው በኀጢአቱ እንዲቀጥልበት መፍቀድ ማለት አይደለም። ይልቁንም ይቅር ማለት ትርጒሙ የጎዳንን ሰው ካለፈው ኀጢአቱ ነጻ በማድረግ የኀጢአትን ዑደት እንዲያቆም ማስቻል ማለት ነው።

በሌላ አባባል ይቅርታ በጥቃት ስንዘራ፣ በእንግልትና በጉዳት ሁኔታ ውስጥ መቅረት ማለት አይደለም፤ የተጎዳውንም ሰው ቢሆን በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዲቀር መጠየቅ ብሎ ነገር የለም። የይቅርታ ትርጉም ይህ አይደለምና። ለምሳሌ ያህል በቤተሰብ ውስጥ ባለ ጥቃት ስንዘራ ላይ ቱግ የማለትና መልሶ የመታረቅ ዑደት ያለ ነው፣ ባል ሚስቱን ይመታና ቆይቶ ስለ ሁኔታው ያዝናል፤ አሁንም መልሶ ይማታና ደግሞ ስለ ሁኔታው ያዝናል፤ እየሱስ እንግልት የሚደርስበት ሰው ጥቃቱን ተቀብሎት በቀን ሰባት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ እንደተደበደበ ይኑር ማለቱ አለመሆኑን ግልጽ ነው። ይቅር የማለት ትርጉሙ ይህ አይደለም። ይቅርታ ርካሽ ምህረት አይደለም። ይቅርታ የተጎጂ ልብ መንፈሳዊና ስሜታዊ ዝንባሌ ሁኔታ ነው። ተጎጂው ይቅር ይል ዘንድ ማስገደድም ሆነ በእርሱ ላይ ምንም ዐይነት ጫና ማሳደር አይቻልም። ይቅርታ በተጎጂውና በእግዚአብሔር መካከል ያለ ጉዳይ ሲሆን ተጎጂው ለተጎጂው የሚያደርገው የምህረት መገለጫ ነው። ይህም በእግዚአብሔር ፊት የተጎጂው የብቻው ምርጫ ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ይቅርታ ወደ መታደስ ለማምጣ፣ ከጉዳት ቀንበር ለማላቀቅ፣ የጉዳት የጥቃትና የቅጣት ዑደቶችን ለመስበር ያለውን ኀይል ለተጎጂው በሁነኛው ጊዜ መግለጽም ጠቃሚ ነው።

---

---

## የእንክብካቤና የመልሶ መቋቋም መንገዶች

የምክክር ስብሰባዎች አንዱ ዐላማ በቤተሰብ ውስጥ ያሉት እያንዳንዳቸው እንክብካቤና ተሃድሶ የሚያገኙበትን መንገዶች መወሰን ነው። በጥቃት ስንዘራና በእንግልት የሚሠቃዩ ቤተሰቦች የተለያዩ በመሆናቸው የሚደረገው ሕክምና በበየቤተሰቡ ችግሮችና ድካሞች ላይ ያነጣጠሩ መሆን አለባቸው።

ከቤተሰቡ አንዱ ተደራራቢ ችግር (በጥቃት ስንዘራ ላይ በሱሰኝነት፣ የአእምሮ በሽተኝነትና/ ወይም ፔዶፊሊያነት) ሲኖርበት በማጓደን ማከምናና /ወይም በቅድሚያ ተደራቢውን ችግር ማከም ያስፈልግ ይሆናል።

በአብዛኛውን ጊዜ ለተጎጂውም ሆነ ለጎጂው በግል ኀላፊነትን መውሰዱ ለመታደስ አስተማማኝ መንገድ ነው። በተጎጂዎቹ በኩል ኀላፊነትን መውሰድ ማለት፣ የገዛ ዋጋቸውን በማወቅ ለራሳቸው የሚጠነቀቁና ሁኔታውንም የሚለውጡ ናቸው ማለት ነው። በጎጂዎቹ በኩል የሚሆነው ኀላፊነትን መውሰድ ማለት ደግሞ በንስሐ መመለስ፣ ሌሎችን በሚያደርሱት ሥቃይና በድርጊታቸው መዘዝ ጥፋተኛ ማድረጋቸውን ማቆም ማለት ነው።

የተለያዩ የእንክብካቤ ዘዴዎች ጎጂዎቹንና ተጎጂዎቹን ኀላፊነት እንዲወስዱና ቤተሰባዊው ተሃድሶ ተስፋ እንዲኖረው ይረዳሉ።

---

---

## በጥቃት ስንዘራ ለተጎዱ ሴቶች የሚደረግ እንክብካቤ

የሴት ልጅ ከጥቃት ስንዘራ ዑደት ውስጥ የመውጣቱ ሂደት የረዥም ጊዜ የአእምሮ ፈውስ ሲሆን የሚከናወነውም ነጻ ፈቃድ እንዳላት ግለሰብ አድርጎ የሴቲቱን ክብር የሚጠብቅ አፋጣኝና አጠቃላይ የሆነ ስሜታዊና ተግባራዊ ድጋፍ በማድረግ ነው።

የሥነ ልቦናዊ ሰቀቀን ሕይወት ያሳለፈች ተደብዳቢ ሴት ኀይሏን የተነጣችና ከአካባቢዋ የተነጠለች ናት። በመሆኑም ማገገሚ መመሠረት ያለበት ሥነ ልቦናዊ ብቃትን ማለት መሠረታዊ እምነት፣ በጎጂው ወይም በጥቃት ሰንዛሪው አማካይነት የተጎዱትን ነጻነቷንና ተነሣሽነቷን፣ አዳዲስና ገንቢ የሆኑ ግንኙነቶችን የመፍጠር ብቃቷን መልሶ በሚያስገኝ መንገድ ነው።

### የግል እንክብካቤ / ሕክምና፦

- በግንኙነት ማዕቀፍ ውስጥ በሆነ የጥቃት ሴስንዘራ ሰቀቀን ለተጎዱ ሴቶች እንክብካቤያዊው ግንኙነት የተቀላቀለ የስሜት ድባብ ስለሚቀሰቅስ በግል እንክብካቤ ሂደት ውስጥ መተማመንን ከማስፈን ረገድ ከፍተኛ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል።
- በጥቃት ስንዘራ ለተጎዱት የሚደረጉ እንክብካቤዎች የሚፈረጁት ሴቲቱ ካለፈችው የጥቃት ሕይወት አንጻር በተለያዩ የአመለካከት ገጽታዎች በኩል ገቢራዊ፣ አእምሯዊ፣ ባሕሪያዊና መስተጋብራዊ ክፍሎች ላይ አትኩሮት በማድረግ ነው።
- በተጨማሪም እንክብካቤው የአብሮነትና የመለያየት ጥያቄዎችንም የሚያነሣ ነው፤ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ በጥቃት ሴስንዘራ የተጎዱ ሴቶች ጥቃት ያየለበትንና ዐደጋ ዐዘል የሆነውን ግንኙነት እንዳይጋፈጡትና እንዳይሰማቸው ለማድረግ ይችሉ ዘንድ ከተጨባጩ ሁኔታ የሚለዩበትን ዘዴ በውስጣቸ ያዳብራሉ።

### የቡድን እንክብካቤ / ሕክምና፦

- አብዛኞቹ ተደብዳቤ ሴቶች ከነችግራቸው ብቻቸውን የቀሩ እንደሆኑ ይሰማቸዋል። በቡድን በሚደረገው ሕክምና ላይ ሴቶቹ እነርሱ በሚሠቃዩበት ሥቃይ የሚሠቃዩ ሌሎች ሴቶችን ያገኛሉ። የቡድኑ ስብሰባ ለተሳታፊዎቹ ብዙ ጉልበትና ድጋፍ ብሎም በሁኔታቸውም ጥፋተኛ አለመሆናቸውን ግንዛቤ ያስጨብጣቸዋል።

- በቡድኑ ውስጥ ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ ሴቲቱ ታሪኳን መተረክና ከባዱን ስሜቷን ማጋራት ትችላለች፣ ለማገገም ዋነኛ የሆነውን ነገር እነርሱም ሳይፈርዱባት ሊረዷት የመቻላቸው ስሜት ይኖራታል።
- ቡድኑ የሴቲቱን የተሳሳተ እምነቷን እንድትተውና ጥቃት የዕድሏ ጉዳይ እንዳልሆነና፣ በሽብርና ስጋት ውስጥ መኖርን መቀበል እንደሌለባት መገንዘብን እንድትማር ይረዳታል።
- በቡድኑ ውስጥ ሴቲቱ በቤተሰብ ውስጥ ባለ የጥቃት ስንዘራ ዑደት ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪ ስለሆኑ ዘዴዎች ሞያዊ መረጃ ታገኛለች። ዑደቱንም ለይቶ ማወቅና ድግግሞሹን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ትማራለች።

**በጥቃት ስንዘራ ለተጎዱ ሴቶች የሚሰጥ የወላጅነት ልምድ ማጠናከሪያ፡-**

በሁሉም ዘርፍ በጥቃት ስንዘራ የተጎዱ ሴቶች እናትነታቸው ማለትም ሴት ልጅ ለልጆቿ ያላት አዘኔታ፣ አጽናኝነትና መተማመኛነቷ፣ የእናትነቷ ሚና ወዘተ ይጎዳል።

በወላጅነት ልምድ ማጠናከሪያ ላይ ያተኮረ እንክብካቤ እናትነታቸውን ባስመለከተ ያላቸውን የጫጫ ስሜት በመቀነስ የተዋጣለት የእናትነት ችሎታቸውን ዋጋ እንዲሰጡት ያግዛቸዋል።

---

---

## በጥቃት ስንዘራና በእንግልት ለተጎዱ ልጆች የሚደረግ እንክብካቤ

የተጎዱ ልጆች ሰፋ ያለና ሊሠቃዩ የሚችሉባቸው ስሜታዊና ፀባይ ነክ መዘዞችን ያካለለ እንክብካቤ ያሻቸዋል።

አብዛኛውን ጊዜ የወጣት ልጆች አእምሯዊ ሕክምና በርካታ ጣልቃ ገብነትን ይጠይቃል፤ ከተቻለ ቢያንስ ከወላጆች ያንዱን። በመሆኑም በቤተሰባዊው ሕክምና ወይም በቤተሰብ ረዳትነት በኩል በግሉ ሕክምና ሊጠቀሙ ይችላሉ።

ጎልማሶቹ ግን ራሳቸውን የመቻል ዝንባሌ ስላላቸው በግል ወይም በቡድን ሕክምና ሊጠቀሙ ይችላሉ። በቡድን የሚደረገው ሕክምና ወደ ኋላ ላይ ለሚደረገው የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና ጠቃሚነት ይኖረዋል።

**የግል ሕክምና፦**

- ለልጅ የሚደረገው የግል እንክብካቤ የሕመሙን ስሜት ለማስከን ዕድል ይፈጥርለታል፤ ጭንቀትን የሚቆጣጠርበት ዘዴዎችንም ይለግሠዋል፤ የቁጣ ምልክቶችን ቀደሞ ለመለየትና እነዚህን የመሳሰሉ ልምዶችን እንዲያገኝ ያደርገዋል።
- በጥቃት ስንዘራ የተጎዳ ልጅ እንደሚከተሉት ያሉትን የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን ሊያዳብር ይችላል፦ ሰው ቁጣውን ዕምቅ አድርጎ መያዝ አለበት ያለበለዚያ ግን ከቁጥጥር ውጪ ይሆናል፣ በጥቃት ስንዘራ የተጎዳ ልጅ ጥፋተኛ እንደሆነ፣ ሌሎችን የሚጎዱ ሰዎች በድርጊታቸው ጠንቅ የማይጠላለፉ እንደሆኑ፣ ጥቃት ስንዘራና ዛቻ ያለሙትን እንደሚያገኙ፣ ለማሸነፍና ችግሮችን ለመፍታት እንደሚረዳ፣ የሆነ ሰው ስለሚወደው ብቻ ለጊዜው ሊያንገላታው እንደሚችል፣ በብርቱዎችና በደካሞች መካከል ያለው መበላለጥ ተቀባይነት ያለው ነገር ነው ብሎ እንዲያስብ፣ ሴቶች ደካሞች፣ ምዝብሮችና ቂሎች ናቸው ብሎ እንዲያስብ ያደርደዋል።
- ለልጅ የሚደረገው የግል እንክብካቤ እነዚህና ሌሎች ግንኙነቶችን፣ ቤተሰብን፣ ማኅበረሰብን፣ ስሜትንና ግብረገብን ባስመለከተ የተሳሳቱ ግንዛቤዎቹን እንዲያስተካክል ይረዳዋል።

**የቡድን ሕክምና፦**

- ለልጅ የሚደረገው የቡድን እንክብካቤ ሌሎችም እንደ እርሱ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኙና ብቻውን እንዳልሆነ ይረዳ ዘንድ ያግዘዋል። የቡድን እንክብካቤው ለልጁ በራስ መተማመንን በማጠናከርና ዳግም በቤተሰዘመዶቹም ሆነ በሰዎች ከመታመን ረገድ ይረዳዋል።
- የቡድን እንክብካቤው ልጁ ማኅበረሰባዊ ብቃትን እንዲያገኝ፣ ከሌሎች ልጆች ጋር አዎንታዊ መስተጋብር እንዲኖረው፣ ለችግሩ መፍትሔ እንዲያገኝ፣ የውጥረት ሁኔታዎችን ወይም አስቸጋሪ ማኅበረሰባዊ ሁኔታዎችን እንዴት መቋቋም እንዳለበት እንዲያውቅ ይረዳዋል።

**ቴራፒዎች፣ የተለያዩ እንክብካቤዎች / ሕክምናዎች፦**

ብዙውን ጊዜ ልጆች ራሳቸው በቃላት ለመግለጽ ስለሚቸገሩ በግል እንክብካቤ ወቅት ያሉትን ተግዳሮቶችና ተቃውሞዎች ወደ ጎን ትተው ስሜታቸውን እንዲገልጹ የሚያስችለው ንግግር አልባው ሕክምና የበለጠ ይጠቅማቸዋል። የተለያዩ ቴራፒዎችም ልጅ በራሱ ልዩ መሆኑንና ችሎታውን እንዲያዳብር በዚህም ለራሱ የሚኖረውን ዋጋ እንዲያጎለብት ይረዳሉ።

- በእንቅስቃሴ አማካይነት የሚደረግ ሕክምና፦ የተለያዩ እንቅስቃሴያዊ ልምምዶችን እያሰናሰለ ስሜታዊ፣ አካላዊ፣ ማኅበረሰባዊና አእምሯዊ መስተጋብርን ያሻሽላል።

- በእንስሳት አማካይነት የሚደረግ ሕክምና፦ የገዛ ራስ ትግበራን፥ ሙከራንና የልምምድ ምልክታዊ ግንዛቤን ያራምዳል፤ የቅርበት እና/ወይም ለእንስሳት ያለው የሥጋት ስሜት መነሣሣትም የመቋቋሚያ፣ የብቃት፣ የግንኙነት፣ የማኅበረሰብን መንገዶች ለመመርመርና ለማሻሻል ያስችላል።
- በኪነ ጥበብ አማካይነት የሚደረግ ሕክምና፦የሚታወቁና የማይታወቁ ሐሳቦችንና ስሜቶችን ለመግለጽ ያስችላል።
- በጨዋታ አማካይነት የሚደረግ ሕክምና፦ የማሰቢያ ጨዋታዎች፣ በዐይነ ኅሊና ማየት፣ ቀፎ፣ ኮምፒዩተር፣ ስፖርትና የመሳሰሉ ሁሉ ልጅ ራሱንና ችግሮቹን እንዲገልጥባቸው የሚያስችሉት የመግለጫና የግንኙነት ቁሶች ናቸው።
- በድራማ አማካይነት የሚደረግ ሕክምና፦ ልጅ በተግባሩ ወይም በርዕሱ በኩል በራሱ ላይ ትኩረት አድርጎ፣ ራሱን አስቸጋሪ ወይም ግትር እንደሆነ በማድረግ ("ይህ እኔ ሳልሆን ገጸ ባሕሪዬ ነው በሚል መልኩ") ራሱን ወይም ሌላውን "እንዲተውን" ያስችለዋል። እንዲህም እውነተኛው ነገር እንዲሰማውና እንዲያብላላው ይሆናል። እንዲህ በማድረግም በዕለት ዕለት ኑሮው ልዩ ልዩ ተግባራትንና አኳኋኖችን ማስተሳሰር ይችላል።
- በሙዚቃ አማካይነት የሚደረግ ሕክምና፦ የማድመጥና ትኩረት የመስጠት ችሎታን ለማሻሻል ያግዛል፤ የአስተሳሰብን ይዘት ለማሻሻልና ለመቀየር፣ ቋንቋንና ግንኙነትን ለማደስና ለማዳበር ይረዳል።
- (የሕይወት ታሪክን) በመተረክ የሚደረግ ሕክምና፦ በገዛ እጅ ወይም በረዳት አማካይነት ለልጅ የሚነበብ ልዩ ልዩ ስሜቶችን ቀስቃሽ የሆነ ንባብ ልጅ ራሱን እንዲረዳ፣ አእምሯዊ በሽታንም እንዲያስወግድና አእምሯዊውንም ሆነ ማኅበራዊውን ችግር እንዲፈታ ይረዳዋል።

---

## ለጥቃት ሰንዛሪ ወንዶች የሚደረግ ዕገዛ

የወንድ ወደ ሕክምና የመምጣት ችግር የሚመነጨው፣ የገዛ ሁኔታውን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ካለው ፍላጎት የተነሣና በደካሞችና ርዳታ በሚያስፈልጋቸው ቦታ ለመገኘት በመቸገሩ ነው። ይህም የሕክምናው ሂደት ራሱን በራሱ መቆጣጠሩን ስለሚነሣውና በአካሚው እንዲረዳ ስለሚያደርገው ነው።

አብዛኛውን ጊዜ ጥቃት ሰንዛሪ ወንዶች ወደ ሕክምና የሚመጡት በሕክምናው ጊዜ ከሚፈጠርባቸው የመደፈር ስሜት ይልቅ፣ የበለጠ እጦት የሚያደርስባቸው የምር ዛቻና ጫና (ራስን የመቆጣጠር እጦት፣ የመልካም ስም መጉደፍ ወዘተ) ሲፈጠርባቸው ነው። ከዚህ የተነሣ (አቤቱታ እንዳይቀርብባቸው) ለጥቅማቸው ሲሉ እንጂ በፈቃዳቸው ወደ ሕክምና የማይመጡ ጥቃት ሰንዛሪ ወንዶች ጥቂት አይደሉም፤ ያሰቡትንም ባሳኩ ጊዜ ብዙዎች ከሕክምናው ማዕቀፍ ይንጠባጠባሉ።

ስለሆነም አንዳንዱ በሰውዬው ፍላጎት ላይ ብቻ የተመሠረተ የሕክምና ፕሮግራም፣ ልክ በሕግ አስገዳጅነት ላይ ተመሥርቶ የሚሰጠው ሕክምና የሚያደርገውን ዐይነት ግዴታ የሰፈነበት ሕክምና ለማከናወን አያስችልም።

**ለጥቃት ሰንዛሪ ወንዶች የሚሰጠው ሕክምና ዋና ዐላማዎቹ፦**

- የቤተሰቦቻቸውና የራሳቸውን አኳኋን ተፅዕኖዎች መረዳትና ወደ ውስጣቸው ማስረጽ።
- አሉታዊ አኳኋንን ማወቅ፦ (በግልጽ የሚያየውን) የጥቃት ስንዘራን ፀባይ ብቻ ሳይሆን ሥነ ልቦናዊ እንግልትንና ሌሎች አሉታዊ ፀባዮችንም ማወቅ።
- ለሥነ ልቦናዊ፣ ለአእምሯዊና ለሁኔታዊ ፍንጮች ንቃተ ኅሊናን በማሳደግ ወደ ጥቃት ስንዘራን የሚያመሩትንና ጥቃት ስንዘራ ከመከሰቱ በፊት የሚያስጠነቅቁትን ተከታታይ ድርጊቶች ለይቶ ማወቅ።
- ጥቃት ስንዘራ የሌለባቸውን ሰፊና ልዩ ልዩ አኳኋኖችን መማር፦ የጥቃት ስንዘራን ፀባይ ፍንጮችን ጥቃት ስንዘራ አልባ ወደ ሆኑ ፀባዮች መቀየርን፣ ከነይለኛ የጥቃት ስንዘራ ዐደጋ ሁኔታ መላቀቅን መማር።

**የቡድን ሕክምና፦**

- በአሁኑ ወቅት ለጥቃት ሰንዛሪ ወንዶች፣ ወሲባዊ እንግልት የሚያደርሱትን አባቶች ጨምሮ የሚመረጠው ሕክምና የቡድን ሕክምና ነው።
- የጥቃት ሰንዛሪን ሰው የብቸኝነት ስሜት በመቀነስ የጋራ መተጋገዝንና መመሳሰልን ያሰፍናል።
- በግልና በማኅበረሰብ ዘንድ ለሚሆነው ለውጥ መስማሚያዎችን ለማዳበር በማገዝ ለጥቃት ሰንዛሪው ሰው ልዩ ልዩ የመታነጫ ግብዐቶችንና የአስተሳሰብ ለውጦችን መቅሰሚያ ምሳሌዎችን ያመላክታል።
- ጥቃት ሰንዛሪው ሰው ሌሎችን እንዲረዳና እንዲደግፍ ዕድል ይሰጠዋል። ሌሎችን መርዳት፣ መደግፍና ማስተማርም ብቻ ሳይሆን ለግሉ መማርን እንዲያጠናክር አጋጣሚም ይፈጥርለታል።
- ጥቃት ሰንዛሪው ሰው ከቢጤዎቹ ጋር ተቀምጦ መወያየቱ፣ ድርጊቱን እንዳይክድ ወይም ደግሞ ለድርጊቱ የሚወስደውን ኀላፊነት አሳንሶ እንዳያይ ያደርገዋል።
- ስለ ፀባዩ ኀላፊነት በመውሰድ ለመለወጥ ዐቅም ማግኘት እንዲችል የጥቃት ሰንዛሪውን ሰው ሃፍረት ይቀንሰዋል።

- በተሳታፊዎቹ መካከል የሚፈጠረው ግንኙነት ሰውዬው ከስሜት ረገድ የሚያስፈልገኝን ሁሉ እርሷ ታድርገዋለች ብሎ በሚስቱ ላይ የሚኖረውን ጥገኝነት ይቀንሰዋል።

**የግል ሕክምና፦**

- ለጥቃት ሰንዛሪ ሰው የሚደረጉ አብዛኛዎቹ የጣልቃ ገብነት ሕክምና ፕሮግራሞች የግሉን ሕክምና ከቡድኑ ሕክምና ጋር ባጓደኑ መልኩ ነው።
- አብዛኛውን ጊዜም የግል ንግግሮቹ ይዘት ትኩረት የሚያደርገው በቡድን ሕክምናው ላይ በሚቀርበው ርዕስ ላይ ነው። ግለሰቡም በቡድን ከሚገኘው ትኩረት ይልቅ በግል ሕክምናው ጊዜ የሚያገኘው ትኩረት የበለጠ ነው።
- በሌሎች ሁኔታዎች ደግሞ የግል ሕክምና ማድረግ ይቻላል፣ ምክንያቱም ወሲባዊ ጥቃት/ እንግልት የሚመጡት ከስብእና ቀውስ አለያም ከቀድሞ የሰቀቀን ልምምዶች ነውና።

## በጥንድ የሚደረግ ሕክምና

**ይህ በዋናነት ተያያዥነት ያለው በትዳር አጋሮች መካከል ካለ ጥቃት ስንዘራ ጋር ነው፦**

- በትዳር አጋር ላይ የሚሰነዘር ጥቃት እያለ እና/ወይም ጥቃት ሰንዛሪ ባል ይህ ችግር እንዳለበት የማይቀበል፣ ለመለወጥ ምንም ዐይነት የግል ተነሣሽነት የሌለውና በገዛ ሁኔታውም ሚስቱን እና/ወይም ሌሎቹን ጥፋተኛ የሚያደርግ ከሆነ ጥንድ ተሁኖ የሚደረገው ሕክምና ተስማሚ አይሆንም።
- ብዙውን ጊዜ ጥንድ ተሁኖ የሚደረገው ሕክምና ለእያንዳንዳቸው እንዳስፈላጊነቱ በተለያዩ ጊዜያት የሚደረገውን የተናጠል ሕክምናም ያካትታል።
- ጥበቃ እየተደረገ ከሴት የትዳር አጋር ጋር በመሆን፣ በጥንድነት የሚደረገው ሕክምና ጥቃት ስንዘራን ለመከላከል የሚያስችሉ ዘዴዎችንና መላዎችን ለመለማመድ ያስችላል።
- ሚስቶች ስለ ባሎቻቸው ጥብቅ የሆኑ ርዕሶችን ለማንሣት ወይም ሁኔታው ሊያስከትል የሚችለውን ብድራት ለመጋፈጥ በመፍራት ለመናገር የማይፈልጉ ሲሆን በጥንድነት የሚደረገው ሕክምና ዐደጋኛና የማይስማማ ይሆናል።
- በጥንድነት በሚደረገው ሕክምና ላይ ባልና ሚስቱ በሚያነሡት የሐሳብ አለመግባባት አካሚው የሚኖረ ዐቋም ገለልተኛነት ነው። የትዳር አጋር ጥቃት ሰንዛሪ በሚሆንበት ሁኔታ ግን ይህ የገለልተኛነት ዐቋም ባልና ሚስቱ ለጥቃት ስንዘራው እኩል ኀላፊነት አለባቸው የሚል መልእክት ሊያስተላልፍ ይችላል። የጥቃት ስንዘራው ቀጣይነት የሕክምናው ውጤት እስከ ሆነ ድረስ ሚስትዬው አማራጭ ልትሆን አትችልም።

- ብዙውን ጊዜ በጥንድነት የሚደረገውን ሕክምና እንዲጀመር የሚመከረው ተደባዳቢው ወንድ የሕክምና ሂደት ካለፈና አካላዊ ጥቃት ስንዘራውን ካቆመ በኋላ ብቻ ነው። ለማንኛውም አብረው በመገኘታቸው ሁኔታ ሚስትዬው የእርግጠኝነት ስሜት ይሰማታል ወይ የሚለውን ማጣራትም ይበጃል።

---

---

## ለጥቃት ሰንዛሪ ወላጆች የሚደረግ ዕገዛ

ወላጅነት ባስመለከተ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት፥ ጥቃት ሰንዛሪው ወላጅን ልጆቹን፣ ፍላጎታቸውንና ጉዳታቸውን እንዲረዳ ያግዘዋል። ይህ ሂደት ጥቃት ተኮር አስተሳሰቡን እንዲያስወግድ ኀይል ይሰጠዋል፤ ያበረታታውማል።

**ለጥቃት ሰንዛሪና/ ለአንገላች ወላጆች የሚደረግ ሕክምና ዐላማዎች፡-**

- የወላጆች በገዛ ራስ ላይ ትኩረት የማድረጉን ችሎታ ከፍ ማድረግ፤
- ወላጆች ለልጆቻቸው ስሜት ያላቸውን አዘኔታ ላቅ እንዲል ማድረግ፤
- በልጆች ላይ የሚሰነዘረው ጥቃት ያለውን ተፅዕኖ ለወላጆች በማስገንዘብ መረዳታቸውን ማሳደግ፤
- ወላጆች በልጆች ሕይወትና ዘይቤዎች ውስጥ ያላቸውን ጣልቃ ገብነት ማዳበር፤
- ለወላጆች የወላጅነትን ልምድ መቅሰሚያ ምሳሌዎች ከፍ ማድረግ፤
- ወላጆች የወላጅነትን ክህሎታቸውን የሚገመግሙበት መሻሻል፤

**የጣልቃ ገብነቱ ምሳሌዎች፡-**

- ቁጣን የመቆጣጠር ዘዴዎችን መማር (የወላጅ የመቋቋሚያ መላዎችን ማሻሻል፤ ለምላሽ ከመቃጣት በፊት የቁጣ ስሜትን ለይቶ ማወቅ፣ ወዘተ)። ይህ ቁጣቸውን በተገቢው መንገድ የመግታት ችግር ላለባቸው ወላጆች የሚስማማ ነው።
- በጥሞና ማዳመጥ፣ ግልጥና ወጥነት ያለው ግንኙነት፣ ሥርዐት ለማስያዝ ጥቃት አልባ ዘዴዎችን መጠቀም፣ ወዘተ የመሳሰሉትን ተግባራዊ የሆኑ ልምዶችን መለገሥ። ይህ የሚበጁ የወላጅነትን ዘዴዎች ዕውቀት ለሌላቸው ወላጆች የሚስማማ ነው።
- በገንዘብ ነክ ችግሮች፣ ከግለሰቦች ጋር ባሉ ችግሮች፣ በትዳር ቀውስ፣ በአእምሮ መታወክ፣ በአእምሮ በሽታ ወይም የአደንዛዥ ዕፅና የአልኮል ሱሰኝነት በመሳሰሉ በውጫዊ ውጥረቶች የሚሠቃዩትን ወላጆች ከሕክምና ሰጪ እና/ወይም ማኅበራዊ አካላት ጋር ማገናኘት።

## ቤተሰባዊ ሕክምና

ቤተሰባዊው ሕክምና መሠረት የሚያደርገው የቤተሰብን ስሜታዊና እንቅስቃሴያዊ ሂደት ሳይነጣጥል በቤተሰባዊው ማዕቀፍ ውስጥ የሚካሄደውን የሰውን ትግበራ በሚመረምሩ የተለያዩ ሥነ መለኮታዊ ቲዎሪዎችን ነው። የአጭር ጊዜ ሕክምና፣ ዐላማ ላይ ያነጣጠረ ሕክምና፣ የረዥም ጊዜ ሕክምና፣ ጥምር ሕክምና የሚባሉ የተለያዩ ዐይነቶች ቤተሰባዊው ሕክምናዎች አሉ።

የቤተሰባዊውን ሕክምና አስፈላጊነት በተመለከተ በተቻለ መጠን ሰፋ ያለና እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ሊሳተፍ የሚገደድበት ቤተሰባዊ ስምምነትን ማግኘት ያስፈልጋል። እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በሕክምናው ሂደት የሚጠየቀውን አእምሯዊ ግብዐት፣ መደረግ ያለበትን ጥረት ሁሉ ስልቶችን ጨምሮ አንዳንዴም ለሕክምናው ለመዘጋጀት ሲባል ከሥራ ቀደም ተብሎ መውጣት ቢያስፈልግም ይህን ማድረግ መቻል አለበት።

ቤተሰባዊው ሕክምና ቤተሰቡ በቤተሰባዊ ማዕቀፍ ውስጥ ለውይይት ማንሣት የሚቸገርባቸውን ርዕሶች በቀላሉ ለመቋቋም ያስችላል። ቤተሰባዊው ሕክምና ማንኛውም ዐይነቶች ስሜቶችና ሐሳቦች ሊነሡ የሚችልበትን ድባብ ሊፈጥር ይችላል። ሕክምናው የቤተሰቡ አባል አዲስ፣ ባህላዊና ራስን መግታት ያለበትን ውይይት እንዲማር ይረዳዋል።

በቤተሰባዊው ሕክምና ውስጥ ግለሰብ በቤተሰባዊው ዐውድ ውስጥ እንዳለ ይሆንና፣ ቤተሰቡ ሁሉ እንደ አንድ ሙሉ የሕክምና ዒላማ አካል ተደርጎ ነው የሚወሰደው። ዐላማውም በቤተሰብ ውስጥ ያሉትን ችግሮች ተረድቶ፥ በግል ፍልሚያ ሳይሆን እንደ ቤተሰብ መፍትሔዎችን ማግኘት ነው።

ቤተሰባዊው በሕክምና ግለሰቡን የሚያየው ከሌሎች የቤተሰብ አባላት አንጻር በትግበራ ረገድ የሚመለከተውን ነገር ለመማር እንደሚሞክር እንደ ለውጥ ወኪል አድርጎ ነው። አካሚውም በግለሰቡ ውስጥ ታምቆ ያለውን ዐቅም በማግኘት ግለሰቡ በሚገኝበት የሕይወት ድባብ ሳቢያ ወደ ሥራ ሊተረጉማቸው ያልቻላቸውን ልዩ ልዩ አኳኋኖች እንዲተገበሩ ይፈልጋል። ዐላማው በሕክምናው ሂደት ውስጥ በሚደረገው ለውጥ እያንዳንዱ ኀላፊነት እንዲኖረው ለመቀስቀስ ነው።

በሕክምናው ሂደት ውስጥ ቤተሰባዊ ግጭቶች እንደሚነሣሡ ሁሉ እንዲሁም ጉዳዩን ዳግም መነካካቱም በግጭት ውስጥ የነበረውን (ድጋፊ፣ ፊዋሽና ወንጀይ የመሳሰሉት) የቤተሰቡ አባላት ሚናን ለመለየት ያግዛል። እንዲህም የቤተሰቡ አባል አንዱ ለሌላው ያለውን የግንኙነት ዐቋም በማየት ቤተሰባዊ ባሕሪይውን፣ በመካከላቸው ያለውን ተሳትፎ፣ ቤተሰቡ የሚፈታባቸው ወይም የማይፈታባቸው መንገዶችንና ግልጽ ወይም ውስን ግጭቶችን መመርመር ይቻላል።

አንዳንዴም በቤተሰቡ መካከል ላለው ግንኙነት ለውጥ ሲባል በጣልቃ ገብነት ማዕቀፍ ውስጥ በስብሰባው ጊዜና ከዚያም ውጪ ቤተሰቡ ስለሚሠሩት ሥራ መመሪያ ይሰጣቸዋል፦ በቤተሰብ ውስጥ ድርድር የማድረግ፣ ስምምነቶችና ውሎች፣ የቁጥጥር ዘዴዎችና የብድራት አመላለስ ለውጦች፣ በጋራ ግንኙነት ጉዳይ ላይ የሚሠራ ሥራ(በወላጅና በልጅ፣ በባልና ሚስት) ስለ ወደፊቱ ሁኔታ የቤተሰቡ ሐሳብ፣ የቤተሰብ ድባብና የሕይወት ይዘት ለውጥ፣ ግልጽ የሆኑ ቤተሰባዊ ደንቦችን በመፈጸም የሚደረግ ዕገዛ፣ በተበላሸ ቤተሰባዊ ስሜት ነክ ግንኙነት ላይ ስለሚሠሩት ሥራ መመሪያ ይሰጣቸዋል።

በቤተሰብ ውስጥ ያለን ዐቅም ፈልጎ በማግኘት ቤተሰቡን በሚኖርበት ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ወደሚኖረው አዲስ የትግበራ መሰናዶ መምራት።

ጥቃት ሰንዛራ ባለበት እና/ወይም ጥቃት ሰንዛሪ ጎጂው ይህ ችግር እንዳለበት የማይቀበል፤ ለመለወጥ ምንም ዐይነት የግል ተነሣሽነት የሌለውና በገዛ ሁኔታውም ቤተሰቡን እና/ወይም ሌሎቹን ጥፋተኛ የሚያደርግ ከሆነ ቤተሰባዊው ሕክምና ተስማሚ አይሆንም።

ይህ ሕክምና እንዲጀመር የሚመከረው ጎጂው የሕክምና ሂደት ካለፈና አካላዊ ጥቃት ሰንዛራውን ካቆመ በኋላ ብቻ ነው። ለማንኛውም ከሌሎች ተሳታፊዎች ጋር አብረው በመገኘታቸው ተጎጂዎቹ የእርግጠኝነት ስሜት ይሰማቸው ይሆን ወይም አይሆን የሚለውን ማጣራት ይበጃል።

## በቀውስ ውስጥ ላሉ ቤተሰቦች የሚደረግ ገንዘብ ነክ ዕገዛ

ጥቃት ሰንዛሪ ወላጅ በባለሥልጣናት አማካይነትና/ወይም በሚደረግለት እንክብካቤ ሂደት ሳቢያ ከቤተሰቡ መካከል ሲወጣ ቤተሰቡ ለማስተዳደር አይችል ይሆናል ይህ ደግሞ ቤተሰቡን ያለ ዋና ወይም ሁለተኛ መተዳደሪያ ገቢ መስተዳደርን እንዲማር ያስገድደዋል።

---

### የሚመከሩ የመቋቋሚያ መንገዶች

- **ለቤተሰብ የሚሰጥ ገንዘብ ነክ ምክርን ማግኘት፦** እንዲህ ያለው ምክር ቤተሰብ የወጪ አወጣጥ ልምዱን እንዲመረምርና ብልህነት የተላበሰን የገንዘብ አያያዝ መንገድ ይማር ዘንድ ይረዳዋል።
- **ሕግ ነክ ምክርን ማግኘት፦** እንዲህ ያለው ምክር ቤተሰብ በሕጉ መሠረት (በማኅበራዊ ጉዳይ ረገድ፣ በብሔራዊ ዋስትና በመኖሪያ ረገድ) መብቱ የሚፈቅድለትን ርዳታዎች እንዲገነዘብና እንዴት ማግኘት እንደሚችል እንዲረዳ ያግዘዋል።
- **የጋራ ጥረት፦** የቤተሰቡ አባል የሆነ ሁሉ ዕድሜውንና ክህሎቱን በሚመጥን መልኩ ለቤተሰባዊው የገንዘብ ማግኛ ጥረት አስተዋጽኦ ለማድረግ መሞከር አለበት።
- **ከጉባኤ የሚደረግ ዕገዛ፦** አንድ ክሂላ ለቤተሰብ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች (ቀለብ፣ መጠለያ፣ ትምህርትና አልባሳት) መሟላታቸው የማረጋገጥ ኀላፊነት አለባት። በክሂላዋም ውስጥ ያሉ ቤተሰቦች ሁሉ በቀውስ ውስጥ የሚገኘውን ቤተሰብ ለመርዳት አንድ መሆንና ዐቅማቸው የፈቀደውን ያህል መለገሥ አለባቸው። በተለይም ደግሞ የቤተሰቡ ዋነኛ የገቢ ምንጭ ክሂላዋ ከሆነች፣ ቤተሰቡ ገንዘብ ነክ ጉዳይን ባስመለከተ ለክሂላዋ የሚኖረው ግልጽነት ከፍተኛ ጥቅም አለው።
- ከቅርብ ቤተሰብ ዘንድ የሚጠየቅ ርዳታ።
- ከርዳታ ድርጅቶች ዘንድ የሚጠየቅ ርዳታ።

## ፍትሕ በመቅዱሳን መጻሕፍት

ፍትሕ ከሁሉ በፊት የሚመለከተው በእግዚአብሔር፣ በሰውና በክፂላ መከከል ያለውን ግንኙነት ነው፤ ፍትሕ ማለት የግንኙነት ማዕቀፍ መሻቶችንና ግዴታዎችን ማሟላትና ይህ እንደሚገባ ያልተሟላባቸውን የግንኙነት ማዕቀፎች ማገገም ነው።

በቀድሞ ዘመናት እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ቃል ገብቷል፦ "እንግዲህ ቃየንን የገደለ ሁሉ ሰባት እጥፍ በቀል ይደርስበታል።" (ዘፍ4፥15) ከዚህም በተጨማሪ ሌላን ሰው የገደለው ሌሜሕም ይህንኑ ሐሳብ "ቃየንን ሰባት እጥፍ ይበቀሉታል፤ ሌሜኽን ግን ሰባ ሰባት እጥፍ።" ሲል ከፍ አድርጎ አውጆታል። (ዘፍ4፥24) ቃየንን ሰባት እጥፍ ይበቀሉታል፤ ሌሜኽን ግን ሰባ ሰባት እጥፍ። ማለትም ከበቀሉ የሚወጣው ቅጣት የበቀሉን ሰባት ዕጥፍና ሰባ ሰባት ዕጥፍ ነው ማለት ነው።

በኋላም ዘግይቶ በሕጉ የቅጣቱ ብድራት ድርጊቱን የሚመጥን ሆነ፦

> "ሰውም ባልንጀራውን ቢጐዳ፥ እርሱ እንዳደረገ እንዲሁ ይደረግበት። ስብራት በስብራት ፋንታ፥ ዓይን በዓይን ፋንታ፥ ጥርስ በጥርስ ፋንታ፥ ሰውን እንደ ጐዳ እንዲሁ ይደረግበት።" (ዘፍ24፥19-20)

ከዚያም በኋላ ነቢያትና ነገሥታት በጊዜያቸው ስለ እግዚአብሔር ፍትሕ፣ ጽድቅ፣ እውነትና ፍርድም ይሁን ስለ ጸጋ፣ ፍቅር፣ ምህረትና ሰላም ተናግረውበታል። በዘካ8፥16 እንደጻፈው "በበር አደባባያችሁም የእውነትንና የሰላምን ፍርድ ፍረዱ፤"

እየሱስ የዘፍጥረትንና የኦሪትን ደንብ፣ ከበቀል የተነሣ የሚሆነውን ቅጣት ፍትሕ ማድረግ እንደሆነ ተደርጎ አይቆጠርም ሲል ገልጿል። እየሱስ ፍቅርና ጸጋ የጥቃት ስንዘራን፣ የቂጣና የበቀል ዑደት መስበር የሚችሉ ኀይሎች መሆናቸውንም አጽንኦት ሰጥቶበታል።

ከብዙ ሺህ ዓመታት በኋላ እየሱስ እንደ ጸጋ መጠን እናደርግ ዘንድ፦

> "እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም።" ሲል አበረታትቶናል። (ማቴ18፥22)

በመቀጠልም እየሱስ እንዲህ አለ፦

> “ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለ ጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ክፉውን አትቃወሙ፤ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት።” (ማቴ5፥38-39)

እየሱስ ስለ ኀጢአታችን በመሞቱ ፍትሕና ሰላምን፤ ጸጋንና እውነትን አገናኘ። በሁለቱ ጎራዎች መካከል (በፍትሕና ምህረት) ያለውን ውጥረትና ተቃርኖ ለማቀራረብ ቻለ። እየሱስ ምህረትን ፍትሕ የማስገኛ መንገድ እንዲሆን አደረገው። የደካማው ሰብአዊ ክህሎት ሙሉ ምህረትን መቀበል ፍትሕን ለማግኘትና በመነመነው ግንኙነት ላይ ነፍስ ለመዝራት ሁነኛ ነገር መሆኑንም አስተምሮናል።

በአብዛኛው ሲታይ ዓለም እስካሁን እየሠራ ያለው በዘፍጥረቱ የአስተሳሰብ መንገድ ነው። ማኅበረሰቡ ከማገገም ይልቅ መቅጣትን ለራሱ ግብ አድርጎ አስቀምጦታል። ወንጀልና ጥቃት ስንዘራን ያስወግዳል አለያም በኅብረተሰብ ውስጥ ሥርዐትን ያሰፍናል በሚል እምነት ብድራትና በቀል በወንጀለኛ ቅጣት ዘዴ ሁሉ ውስጥ ይገኛሉ። ዳሰሳዊው ጥናት የሚያሳየው ግን የወንጀል ነኩን ማዕቀፍ ውድቀት ነው ምክንያቱም ብድራትን በመመለስ የሚሆነው ሰብአዊው፣ ሰብአዊውን ችግር የማይፈታው በመሆኑ ነው። ኅብረተሰቡ ጉዳት አድራሹን ሰው የሚሰይመው ከሁኔታ፣ ከድርጊት ወይም ከተከታታይ ድርጊቶች በመነሣት ነው። እየሱስ የሚያስተምረን ሰውን እንድ ንወደው ድርጊቱን ግን እንድናወግዝ ሆኖ ሳለ “እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ክፉውን አትቃወሙ፤” (ማቴ5፥39) በእርግጥ ወንድማችንን “ገንዘብ በማድረግ” ወደ እግዚአብሔርና ወደ ክሂላ ለመመለስ በማሰብ ክፉውን መቃወም ያስፈልጋል።

የማኅበረሰቡ ሰብአዊ መዋቅር የሚያበረታታው ሰው ስለ ድርጊቱ ኀላፊነት እንዳይወስድ ነው። ለዚህም በዚህ ዘዴ ምስክሮች መጥራትና ትንታኔዎች መስጠት፣ ደግሞም በወንጀል ክህደት ውስጥ “አላደረግሁም” ሳይሆን “አድረገሃል ካላችሁ አረጋግጡልኝ” ማለቱ የፍርድ ታክቲክ ሆኑ።

እየሱስ እነዚህ ነጻና ወንጀለኛ የሚባሉትን ሁለት ተቀባይነት ያላቸውን ፈርጆች የሚናዘዙ ኀጢአተኞችና የሚክዱ ኀጢአተኞች ብሎ በይዘታቸው በተለዩ በእነዚህ ሁለት ፈርጆች ቀየራቸው። እየሱስ የሚያበረታታው ሰው ስለ ድርጊቱ ኀላፊነት እንዲወስድና መልስ እንዲሰጥበት ነው። እንደ እየሱስ መንገድ ከክህደት ከሚገኘው ጥቅም ይልቅ በመናዘዝና በንስሐ በመመለስ የሚገኘው ጥቅም ታላቅ ነውና።

ሰብአዊው ዘዴ የሚያራምደው ሕገኝነትን ነው። የጎጂውንና የተጎጂውን ድምፅ አምክኖና ግጭታቸው “ሰርቆ” ባለ ቂጥር ፋይል ወደ መሆን ያደርሳቸዋል። ተጎጂው ከጨዋታው ውጪ ይሆናል፤ ማኅበረሰቡ ደግሞ (ለክፉም ይሁን ለደጉ) ፋይዳ የሌለውን ተፅዕኖ አሳዳሪ ሲሆን ጎጂውም የሥርዐቱ ሰለባ ይሆናል፤ ጥቃት ስንዘራ ዑደቱም ይቀጥላል።

ሕጉና ማኅበረሰብአዊው የፍርድ መዋቅር በተለያዩ ሁኔታዎች ሊጠቅሙ ይችላሉ። ለምሳሌ አንድ ሰው የሆነን ድርጊት፣ በእውነትም እርሱ ያላደረገው በመሆኑ የተደረገውን ድርጊት አምኖ ባለመቀበል ከድርጊቱ ነጻ መሆኑ ለማስረገጥ ይጠቅመዋል። በአንጻሩም ሰው በንስሓ ለመመለስ ዝግጁ ባለመሆኑ የተደረገውን ድርጊት ሳይቀበል ሲቀር እግዚአብሔር ሕግንና ማኅበረሰብአዊው የፍርድ መዋቅር ተጠቅሞ የሰውየውን ልብ በመግራት በሰውየው ልብ ውስጥ ለሕይወት ለውጥና ለተስፋ ቦታ እንዲኖር ያደርግበታል።

እየሱስ እንድንወሰደው የሚያበረታታን እርምጃ አዋጭ መንገድ ይመስላል። ምክንያቱም መንገዱ ከውስን መመሪያዎች ጋር ሳይያያዝና ለጠብ ባልሆነ መልኩ ሂስን ለማዋዋጥና ለመደጋገፍ ግጭቱን ወደ ተጋጩቱና ወደ ክሂላ ይመልሰዋልና። ሂደቱ የተጋጩትን ወገኖች የማገናኘት ሙከራን ያካተተ ነው፤ ግንኙነቱም እውነተኛ የሆነ ልባዊ ለውጥ እንዲኖር ስሜቶችን ለመግለጽ የሚያስችል ፍርድ ነክ የሆኑ የማጣሪያ ትንታኔዎች አልባ ነው።

የእየሱስ ትኩረት የሰው ልብ ሁኔታና የደረሰው ጥፋት ላይ እንጂ በተጣሱት ሕጎች ላይ አይደለም። የደረሰውም ጥፋት ሕግን የመተላለፍ ወንጀል ተብሎ አይበየነም፤ ይልቁንም ከእግዚአብሔር፣ ከሰውና ከክሂላ ጋር ያለውን ግንኙነት እንደ መጉዳት ተደርጎ ይወሰዳል እንጂ። ሂደቱን የሚያነሣሣውም ራሱ የተጎዳው ነው፤ የተጎዳውን ጉዳት በገዛ ቃሉ ይበይነውና ማኅበረሰቡ በድርጊቱ ላይ ለሚኖረው ምላሽ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ያሳርፋል። ጌታ እየሱስ እንዲህ በማድረጋችን በጎጂው፣ በተጎጂው፣ በክሂላና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት መልሶ እንዲያንሠራራና ፈውስ እንዲያገኝ ይመክረናል።

## በቤተሰብ ውስጥ ያለን ጥቃትና እንግልትን ባስመለከተ
## የጉባኤ ቃለ ስምምነት

ከሰብአዊነት፣ ከሥነ ምግባር፣ ከመንፈሳዊነትና ኅብረተሰብ እሴት ረገድ በቤተሰብ ውስጥ የሚሆን ጥቃት ስንዘራና እንግልት እጅግ ታላቅ የሆኑ የማኅበረሰብ ውድቀት አካል ናቸው።

በቤተሰብ ውስጥ በሚሆን ጥቃት ስንዘራና እንግልት ላይ እርምጃ የመውሰድና ሁኔታውን የመቋቋም ነገር የክሂላ ኀላፊነት ነው።

**በዚህ መሠረት እኛ እንደ ክሂላ የሚከተለውን ቃል እንገባለን፦**

- በቤተሰብ የእግዚአሔር ፍጥረት አክሊል ነው።
- የቤተሰብ ሙሉነት ማለት የቤተሰብ ሰላም ነው።
- በክሂላችን ያሉ የቤተሰቦች በጎነት ጉዳይ የእኛ ኀላፊነት ነው።
- በቤተሰብ ውስጥ የሚሆኑ ጥቃት ስንዘራና እንግልት ተቀባይነት የላቸውም፤ መቼም ቢሆን ትክክል አይሆኑም።

**ከላይ በገባነው ቃል መሠረት የሚከተለውን ለማሟላት እንገደዳለን፦**

- የክሂላ አባል በሆኑት ቤተሰቦች ዘንድ የሚታይን ጥቃት ስንዘራና/ወይም/ እንግልት አለመታገሥ።
- ለክሂላችን ልጆችና ቤተሰቦች አስተማማኝ ቦታዎችን ለማግኘት መጣር።
- በክሂላችን ውስጥ በቤተሰብ ዘንድ በሚሆኑ የጥቃት ስንዘራ ሁኔታዎች ላይ ኀላፊነት መውሰድ።
- ሁኔታውን አይቶ እንዳላዩ አለማለፍና የተጎጂዎቹን እሮሮ መስማት።
- ጎጂውና ተጎጂው የደረሰባቸውን የቀውስ ሁኔታ ለማሳወቅ ዕገዛ ለማግኘት የሚረዱ መንገዶች ማመቻቸት።
- በቤተሰብ ውስጥ ለሚሆኑ የጥቃት ስንዘራና የእንግልት ሁኔታዎችን ለመቋቋም ይችል ዘንድ ኮሚቴያችን ብቃት እንዲያገኝና መልስ መስጠት መቻሉን ማረጋገጥ።
- በዚህ የጥቃት ስንዘራ ለተጎዱ ልጆች ሴቶችና ወንዶችን መከላከል።

- ኀጂውን ለሠራው ነገር መልስ እንዲሰጥበት ማድረግና ለተጎዳው ወገን ድጋፍ ማድረግ።
- ለተጎዳው ወገን በሕጉ መሠረት የሚደርሰውን ዕገዛ ማድረግ።
- ለተጎዱት መንግሥታዊ ደንቦችን ማሳወቅ።
- በጥቃት ሰንዘራ የሚሠቃዩ ቤተሰቦች ተገቢውን እንክብካቤ ያገኙ ዘንድ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ድርጅቶችና አካላትን መተባበር።
- በቤተሰብ ውስጥ ስለሚሆኑ የጥቃት ሰንዘራና የእንግልትን በመጻረር መሰበክ።

## ዋቢ መጻሕፍት


1. הרמן, ג. ל. (1992). טראומה והחלמה. תל אביב : עם עובד.

2. וילצ'יק-אביעד י., מזא"ה י. (עורכים). (2014). אלימות אילמת-גברים כקורבנות. הוצאת אוניברסיטת אריאל שבשומרון.

3. יאלום א., לשץ' מ. (2006). טיפול קבוצתי תיאוריה ומעשה. ירושלים : כנרת, מאגנס.

4. הרמל י., נחשון-גליק צ. (2002). תופעת האלימות במשפחה, מאפיינים ומענים טיפוליים בישראל. רפואה ומשפט, גליון 26.

5. יסעור בורוכוביץ, ד. (2003). אלימות אינטימית : עולמם הרגשי של גברים מכים. תל אביב : רסלינג.

6. קירשנבאום, א. (2009) ויקטימולוגיה והמשפט העיברי : התמקדות בקורבן ובנפגע העבירה. משפט ועסקים י', 147-182.

7. שפירא, ר. (2006). ילדים בסיכון-ענישה, התעללות נפשית וגופנית והגבול שביניהם, הסנגור 5,111.

8. Enns E., Myers C. (2009). Ambassadors of reconciliation volume 2: Diverse Christian practices of restorative justice and peacemaking. Maryknoll: Orbis Books.

9. Fortune M., Marshall J. (2002). Forgiveness and Abuse: Jewish and Christian Reflections. Issue of the Journal of Religion and Abuse, Vol 4, Number 4. Haworth Pastoral Press.

10. Johnstone, G. (2001) Restorative Justice: Ideas, Values, Debates, Devon, UK: Willan Publishing.

11. Justpeace Center for Mediation and Conflict Transformation (2005). Just Resolution and Restorative Justice Principles: Understanding the Change to the Complaint Procedure in the Discipline. Washington, DC: JUSTPEACE Center for Mediation and Conflict Transformation, United Methodist Church.

12. Kay P., Barry S., Wedge M. (2003). Peacebuilding Circles: From Crime to Community. St. Paul, MN: Living Justice Press.

13. Malina R. (2011). A Biblical Response to the Abused Wife. A research paper submitted to Dr. Steven Tracy, Phoenix Seminary, T 506, Contemporary Moral Issues.

14. Maricopa Association of Governments Regional Domestic Violence Council. (2001). Domestic Violence Resource Guide for Faith Leaders. Online PDF Manual: http://www.azmag.gov/archive/DV/Resources/RDVC_2011-04-04_Domestic-Violence-Resource-Guide-for-Faith-Leaders.pdf

15. Marshall, C. (2001) Beyond Retribution: A New Testament Vision for Justice, Crime and Punishment. Grand Rapids, MI: Eerdmans.

16. McElrea, F. (1995). Accountability in the Community: Talking Responsibility for Offending. Paper prepared for the Legal Research Foundation's Conference, Rethinking Criminal Justice: a Conference on New Initiatives in Criminal Justice, Auckland, New Zealand.

17. McElre F. (2001) A Christian Approach to Conflict Resolutions. A contribution to the seminar "What does the Lord require of Christians in conflict?" Australasian Christian Legal Convention, Melbourne.

18. Roberts, B. (2008). Not under bondage: Biblical divorce for abuse, adultery & desertion. Ballarat, Victoria, Australia: Maschil Press.

19. Tracy, S. R. (2005). Mending the soul: Understanding and healing abuse. Grand Rapids, MI: Zondervan.

20. Tracy, S. R. (2007). Clergy responses to domestic violence. Priscilla Papers, 21(2). Retrieved from http://www.mendingthesoul.org/2007/04/clergy-responses-to-domestic-violence/

21. Tracy, S. R. (2011). Domestic violence: How should the church respond? Retrieved from http://courses.ps.edu/filr.php/206/DVConf3ChurchRespHO.pdf

22. Tutu, D. (2000). No Future Without Forgivness. NY: Doubleday, 2000.

23. Zehr, H. (1990) Changing Lenses: A New Focus for Crime and Justice. Scottsdale, PA:Herald.

24. Zehr, H. (2002). The Little Book of Restorative Justice. Intercourse, PA: Good Books.

25. Zehr, H., Barb T. (2004). Critical Issues in Restorative Justice. Monsey, NY: Criminal Justice Press.